**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሑፍ(አማርኛ)ትምህርት ክፍል**

# በደቡብ ክልል ካፋ ዞን በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትንተና

**በ**

**ገነት ከበደ**

**በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ(አማርኛ)ትምህርት ክፍል**

**ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት**

**2011 ዓ.ም**

**ጅማ**

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

በማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሑፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

# የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትንተና

በ

ገነት ከበደ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት

አማካሪ

ምህረት ሳዳም (ዶ/ር)

2011 ዓ.ም

ጅማ

## ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ እዚህ እስክደርስ በሰላምናጤና ጠብቆ ላቆየኝ ለልኡል እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው በመቀጠል ለዚህ ጥናት መጠናቀቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ምህረት ሳዳሞ ምስጋናዬ የላቀ ነው::

በተጨማሪም ለጥናት ስራዬ አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ ላደረጉልኝ የስራ ባልደረቦቼ እና በማንኛውም ሁኔታ ላልተለዩኝ ቤተሰቦቼ ለባለቤቴ ለአቶ ተሾመ ዘለቀ፣ ለአባቴ ለአቶ ከበደ ገብሬ፣ ለእናቴ ወ/ሮ ለተብርሃን ካሳዬ ፣ ለወንድሜ ሳሙኤል ከበደ እንዲሁም ለልጄ በሚካኤል ተሾመ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው::

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት የተካሄደው  በካፋ ዞን በሚገኙ ሶስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ በከፍኛ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች  በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች አይነቶችና የስህተቶቹን ምንጮች በመመርመር ለችግሩ መፍትሄ ለመሻት  ነው፡፡ አላማውን ለማሳካት በካፋ ዞን በሚገኙ ዴቻ ፣ ጊምቦ (ወረዳዎች) እናቦንጋ(የከተማ አስተዳደር) ከሚገኙ በዓላማተኮር ናሙና አመራረጥ ስልት በተመረጡ  ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምርት ቤቶች(አውራዳ ፣ጊምቦና ግራዝማችጳውሎስ) በ2011ዓ.ም ከሚገኙ በከፍኛ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ በቀላል ዕጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ በመጠቀም የተመረጡ 15% የካፍኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች  በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት  እንዲፅፉ ተደርጓል:: ከድርሰቶቹ በተጨማሪም በተማሪዎች የተሞሉ የጽሁፍ መጠይቆች አገልግሎት ላይ ውለዋል::እነዚህን መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች እና በተለያዩ ምሁራን የተፃፉ ፅሁፎችን መሰረት በማድረግም ለጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ተሞክሯል:: ከድርሰት እርማት በተገኘው ውጤት መሰረት የስህተት አይነቶች በደረጃ ሲገለፁ አንደኛ የቋንቋ አጠቃቀም ፣ ሁለተኛ የቋንቋ አወቃቀር፣ ሶስተኛ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ፣ አራተኛ የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ፣ አምስተኛ መለየት ያልተቻሉ ናቸው :: እያንዳንዱ አቢይ የስህተት አይነትም በስሩ ዝርዝር የስህተት አይነቶችን አካቷል:: በተጠኚ ተማሪዎች በተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ  ለተገኙ ስህተቶች ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የታመኑት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት እንዲሁም ስነልቦናዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ከድርሰቱ በተጨማሪ በተማሪዎች በተሞሉ የጽሁፍ መጠይቆችም ጎናዊ ፍተሻ ተደርጓል:: በመጨረሻም ማጠቃለያና የተከሰቱትን ስህተቶች ለመቅረፍ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል::*

**ማውጫ**

**ርዕስ** **ገፅ**

ምስጋና ....................................................................................................I

አጠቃሎ ....................................................................................................II

ማውጫ

....................................................................................................II
I

ሰንጠረዥ ማውጫ

....................................................................................................
VII

**ምዕራፍ አንድ**

1.1 የጥናቱ ዳራ ....................................................................................1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ..........................................................4
1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች................................................................4
1.4 የጥናቱ ዓላማ.................................................................................5
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ............................................................................5
1.6 የጥናቱ ወሰን ..................................................................................6

**ምዕራፍ ሁለት**

2. ክለሳ ድርሳን
2.1 የመጻፍ ክሂል ምንነት
....................................................................................................1
0

2.2.1 የመጻፍ ክሂል ባህርያት ....................................................................................................................1
1

2.2 የስህተት ምንነትና ዓይነቶች ............................................................................................................1
2

2.2.1 የስህተት ምንነት ..............................................................................................1
2

2.2.2 የስህተት ዓይነቶች ..............................................................................................1
4

2.3 የስህተት ትንተና ምንነት ..........................................................................................................1
5

III

2.3.1 የስህተት ትንተና ጠቀሜታዎች ..............................................................................................1
6

2.3.2 የስህተት ምንጮች ..............................................................................................1
8

2.4.2.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ...........................................................................................................1
8

2.4.2.2 ውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ ...............................................................................................................................2
1

2.4.2.3. የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና የማስተማሪያ ዘዴዎች

ድክመት

..............................................................................................................................2

4

2.4.2.4 ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች

..............................................................................................................................2

6

2.5 የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት

..............................................................................................................................2

8

**ምዕራፍ ሦስት**

**የጥናቱ ዘዴ**

3.1 የጥናቱ ዓይነት

..............................................................................................................................3

2

3.2 የጥናቱ አካላይ

..............................................................................................................................3

2

3.3 ናሙና አመራረጥ ዘዴ

..............................................................................................................................3

3

3.3.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

..............................................................................................................................3

3

3.3.2 ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ..........................................................................................................3
3

3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ..........................................................................................................3
4

3.4.1. በተማሪዎች የተፃፉ ድርሰቶች ..........................................................................................................3
4

3.4.1.1 የርዕሶች አመራረጥ ..........................................................................................................3
4

3.4.1.2 የድርሰት አጻጻፍ መመሪያ ..........................................................................................................3
4

3.4.2 ለተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ..........................................................................................................3
5..........................................................................................................

3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ ..........................................................................................................3
6

**ምዕራፍ አራት**

የመረጃ ትንተና ..........................................................................................................3
7

4.1 በድርሰቶች ውስጥ የታዩ አጠቃላይ ስህተቶች ........................................................................................................3
7

4.2 በድርሰቶች ውስጥ የታዩ ዋና ዋና የስህተት አይነት ምድቦች ........................................................................................................3
8

4.2.1 በቋንቋ አጠቃቀም ላይ የታዩ ዝርዝር ስህተቶች ........................................................................................................4
1

4.2.1.1 በፊደል አጻጻፍ ላይ የታዩ ስህተቶች ........................................................................................................4
3

4.2.1.2 በቃላት አመራረጥ ላይ የታዩ ስህተቶች ........................................................................................................4
5

4.2.1.3 በማያስፈልጉ ድግግሞሽ የተነሳ የተፈጸሙ ስህተቶች ........................................................................................................4
9

4.2.1.4 በግድፈት ምክንያት የተፈጸሙ ስህተቶች ........................................................................................................5
1

4.2.1.5 ለቦታው የማያስፈልጉ ቃላት በመግባታቸው ምክንያት የተፈጸሙ ስህተቶች ........................................................................................................5
2

4.2.1.6 ኢ-መደበኛ ቃላትን በመጠቀም የተፈጸሙ ስህተቶች ......................................................................................................................5
3

4.2.2 በቋንቋ አወቃቀር የታዩ ስህተቶች ......................................................................................................................5
5

4.2.2.1 በዓ.ነገር ስምምነት ላይ የተፈጸሙ ስህተቶች ......................................................................................................................5
8

4.2.2.2 በመስተዋድድ አገባብ ላይ የታዩ ስህተቶች ......................................................................................................................6
1

4.2.2.3 የቃላት አወቃቀር ቅደም ተከተልን ባለመጠበቅ

የተፈጸሙ ስህተቶች ......................................................................................................................6
4

4.2.2.4 በአያያዦች አገባብ ላይ የታዩ ስህተቶች ......................................................................................................................6
5

4.2.3 በስርአተ ነጥቦች አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች ....................................
66

4.2.3.1በአራት ነጥብ አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች ......................................................................................................................6
9

4.2.3.2 በነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች ...........................................................................................................................7
2

4.2.3.3 በጥያቄ ምልክት አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች ................................................................ V .............................................7
3

4.2.3.4 በትምህርተ አንክሮ አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች ...........................................................................................................................7
4

4.2.3.5 በትምህርተ ጥቅስ አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች ...........................................................................................................................7
4

4.2.4 በጽንህ ሀሳብ ግንዛቤ ላይ የታዩ ስህተቶች ...........................................................................................................................7
6

4.3 ለተማሪዎች የቀረቡ የጽሁፍ መጠይቅ መረጃ ትንተና ...........................................................................................................................7
9

**ምዕራፍ አምስት**

**ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ** ...........................................................................................................................9
0

5.1 **ማጠቃለያ** ...........................................................................................................................9
0

5.2 የመፍትሔ ሀሳብ ...........................................................................................................................9
3
ዋቢ መጽሀፍት
አባሪዎች

VI
የሰ' ዜ

**ማውጫ** **ገጽ**

ሰንጠረዥ 1 በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች ብዛት፣ የስህተቶችአማካይ እና የስህተት ድግግሞሽ መጠን………………………………………………….37

ሰንጠረዥ 2 በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ በየስህተት አይነት ምድቡ የተፈጸሙ ስህተቶች ብዛት፣ የስህተት ብዛት በመቶኛ፣ አማካይ ስህተት እና የስህተት ድግግሞሽ………………………………………………………. 39

ሰንጠረዥ 3 በቋንቋ አጠቃቀም(ሰዋስው) ስር የታዩ ዝርዝር ስህተቶች…………..…..42

ሰንጠረዥ 4 በቋንቋ አወቃቀር (ሰዋስው) ስር የታዩ ዝርዝር ስህተቶች ………………..57

ሰንጠረዥ 5 በስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ስር የታዩ ስህተቶች ……………..……....68

ሰንጠረዥ 6 በጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ላይ የታዩ ስህተቶች ………………………..………77

ሰንጠረዥ 7 ተማሪዎች በተደጋጋሚ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች በተማሪዎች የቀረበ ምክንያት…………………………………………………79

ሰንጠረዥ 8 ተማሪዎች በተደጋጋሚ ስህተት የሚፈጽሙባቸው ሁኔታዎች…………..….80

ሰንጠረዥ 9 ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች የመምህራን የእርማት አሰጣጥ…..82

ሰንጠረዥ 10 በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት በቂ የጽህፈት ልምምድ የማድረግ ሁኔታ……..83

ሰንጠረዥ 11 በት/ቤት በተቋቋሙ አጋዥ የቋንቋ ክሂል ማበልጸጊያዎች

እንዲሳተፉ የማድረግ ሁኔታ…………………………………………………………84

ሰንጠረዥ 12 የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ለጽህፈት ክሂል መዳበር ያላቸው አመቺነት………………………………………………………………85

ሰንጠረዥ 13:- በአማርኛ ቋንቋ የመማር ፍላጎት……………………………………………86

ሰንጠረዥ 14:- በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሆህያት አጻጻፍ ሁኔታ…………………88

ሰንጠረዥ 15:-በአማርኛ ቋንቋ ሃሳብን የመግለጽ ሁኔታ…………………………………...88



**የፈተና**

**የአማካሪ ስም** **ፊርማ**

___________________________

__________________________

___________________________

___________________________

**የፈታኝ ስም**

___________________________

___________________________

___________________________

__________________________

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስምና ፊርማዬን ያስቀመጥኩኝ የድህረ ምረቃ ተማሪ ገነት ከበደ ይህ በከፍኛ አፈ-ፊት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና በሚል የተዘጋጀ ጥናት በጅማ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሑፍ(አማርኛ) ትምህርት ክፍል አማርኛን በማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ ሟሟያነት ያቀረብኩት የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን እንዲሁም በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ፅሁፎችና ምንጮች በትክክል ዋቢ የተደረጉ ስለመሆናቸውና ጂማ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ስም ገነት ከበደ

ፊርማ ___________________

የመታወቂያ ቁጥር ___________________

ቀን ___________________

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የተጠናቀቀ በመሆኑ ለፈተና እንዲቀርብ ተስማምቻለሁ፡፡

የአማካሪ ስም ___________________

ፊርማ ___________________

ቀን ___________________

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ባጠቃላይ አራቱ ክህሎት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ሁለቱን እውቀቶች የስነ ልሳንና የስነ-ጽሁፍ እውቀትን በማዳበር ተግባቦትን ማሳለጥ ነው፡፡አማርኛ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርትነት ከሚሰጥባቸው አጠቃላይ አላማዎች አንዱ ተማሪው የቋንቋውን ሥርዓት ጠብቆ ሀሳቡን በጽሑፍ መግለጽ ማስቻል እንደሆነ ተስፋዬ(1981፣59) ገልጸዋል፡፡

ጽህፈት እንደማዳመጥና መናገር ክሂሎች ለቋንቋ ተጋላጭ በመሆን ብቻ የሚገኝ ካለመሆኑም በላይ አፍ-ፈት ተናጋሪዎችም ሆኑ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተናጋሪዎች በሚያደርጉት ተደጋጋሚ ልምምድና ትምህርት ብቻ ይዳብራል፡፡ በዚህም የተነሣ የጽህፈት ክሂልን የሚማሩ ተማሪዎች በርካታ ስህተቶችን መፈፀማቸው አይቀርም፡፡

የሰው ልጅ የአፍ መፍቻ ቋንቋውንም ሆነ የአፍ መፍቻ ያልሆነውን ቋንቋ ለመግባቢያነት የሚያውለው የቋንቋውን ሥርዓት ጠንቅቆ ሲያውቅ ነው፡፡ ስርዓት ጠብቆ በቋንቋ እንዲግባባም በቋንቋ ትምህርት የሰዋሰው ትምህርት ይሰጣል፡፡ ስለሆነም የቋንቋ ትምህርት በክህሎት ላይ ብቻ ሳይሆን በቋንቋ ስርዓትም ላይ

ያተኮረ መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡ የሰዋሰው ስርዓት ችግር የክህሎትን ችግር እንደሚያስከትል ተክሌ (1989፣ 5)የጽሕፈት ክሂልን አስመልክቶ ተማሪዎች የሰዋሰው ትምህርትን ስርዓት ካልተረዱ ክሂሎችን ሊረዱና ሊተገብሩ ያዳግታል በማለት ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በዚህ ክሂል ሐሳብን ለማስተላለፍ ሲታሰብ በፊደልና ሥርዓተ ነጥብ የተዋቀረ መልዕክትን ማድረስ እንጂ እንደ መናገርና ማዳመጥ ክሂሎች አጋዥ ስሜታዊና አካላዊ መግለጫዎችን (ፈገግታ፣ ቁጣ፣ ሐዘን፣ ንግግር፣ ድግግሞሽ ፣ የድምጽ ቅላፄና የመሳሰሉት ነገሮች) መጠቀም አይቻልም፡፡በዚህም ምክንያት ጽህፈት ለቋንቋ ከሚኖር ተጋላጭነት ባሻገር በትምህርት የሚገኝና በልምምድ የሚዳብር በመሆኑ የአፍ-ፈትነት ማህበራዊ መነሻ አይወስነውም (Allwright እና Baily 1991)፡፡ በጽህፈት አማካይነት የሚደረግ የቋንቋ ግንኙነትም በዋነኛነት የትምህርት ውጤት በመሆኑ ከፊደል አጣጣል ጀምሮ የቃልን፣ የሐረግን፣ የዐረፍተ ነገርን፣ የአንቀጽን እና የድርሰትን አወቃቀር በየደረጃው መማር ክሂሉን ጠንቅቆ ለመረዳት አስፈላጊ ነው፡፡

በኢትዮጵያ በ1944 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በተቀረጸው የአንደኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ አማርኛ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ተካቶ እናገኛለን፡፡ ይህ ሥርዓተ ትምህርት በ1951 ዓ.ም ተሻሽሎ ሲወጣ የትምህርት አይነቶቹ በውስጣቸው ሊይዟቸው የሚገቡ ይዘቶችን አካቶ ነበር፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከተካተቱትይዘቶችአንዱደግሞ የድርሰት ትምህርት ስለመሆኑ በትምህርት ሚኒስቴር( 1979፣1981፣) የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት ከ9ኛ እስከ 10ኛ ክፍል በአማርኛ ዋና ቡድን ከተዘጋጁ ጽሑፎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

አማርኛ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርትነት ከሚሰጥባቸው አጠቃላይ አላማዎች አንዱ ተማሪው የቋንቋውን ሥርዓት ጠብቆ ሀሳቡን በጽሑፍ መግለጽ ማስቻል እንደሆነ ተስፋዬ(1981፣59) ገልጸዋል፡፡

ይሁን እንጂ የመጻፍን ክሂል ማስተማር በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ልምድ ቢኖርም እስካሁን የታለመለት ግብ በሚጠበቀው መጠን ተሳክቶ አይታይም፡፡ለዚህም የሀገራችን የዘርፉ አጥኚዎች አሉታዊ አስተያየቶችን ሲሰነዝሩ ይታያል፡፡የመጻፍ

ክሂል በተማሪዎች ዘንድ እስከ ዩኒቨርሲቲደረጃ በጣም አስቸጋሪ እና ከስህተት ያልጸዳ መሆኑን ባየ(1987)፣ተስፋዬ(1981)ገልጸዋል::

Rechards(1974፣100)በዩኒቨርሲቲደረጃእንኳንብዙዎቹተማሪዎች በሁለተኛደረጃ በተማሩትመሰረት ጥሩ ጽሑፍ ሲጽፉ አይታይም፤ቁጥራቸውይህ ነውየማይባል ተማሪዎች ለጽሑፍ ፍራቻ እና ጭንቀት ይታይባቸዋልሲሉይገልጻሉ፡፡ይህ ችግር እስካሁን እስከ ዩኒቨርሲቲ ዘልቆ ለመከሰቱበርካታ ምክንያቶች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡ከችግሮቹም ዋና ዋና የሚባሉት መምህራኑ የሚከተሉት የማስተማር ስልት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት፣ የተማሪዎች ፍላጎት ማጣት፣ የክፍለ ጊዜ እጥረት እና የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ናቸው፡፡

ተስፋዬ (1986፣ 9-10) በአንደኛም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ድርሰት ሳንጽፍ ከትምህርት ቤት የምንወጣ ቁጥራችን ጥቂት አይደለም:: በተለይ ከአስርና አስራ አምስት አመታት ወዲህ በተማሪዎች ቁጥር መብዛት በትምህርት ክፍለጊዜ መብዛትና በመሳሳሉት ምክንያቶች እየተሳበበ የሚጻፈው ሳይታረም ይቀራል:: የተጻፈው ካልታረመ ደግሞ ስህተት ወይም ትክክል መሆን አለመሆኑ ስለማይታወቅ ካለመጻፍ ብዙም አይለይም፡፡

ከዚህ ሀሳብ መረዳትየሚቻለውይህ ችግር በአንድ አከባቢ ብቻ ያለ ችግር አለመሆኑን እና ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማት ድረስ ያለ ችግር መሆኑን ነው፡፡

እንደcorder (1982 ፣271) አገላለጽ የስህተት ትንተና ጥናት ግብ ከጥናቱ በሚገኙ መረጃዎች በመርኮዝ የቋንቋ መማር ማስተማር ችግርን ለማስወገድ የሚያስችሉ ዘዴዎችን በመተለም የቋንቋ ትምህርት አላማን ማሳካት ነው፡፡ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመለየትና ለማስወገድ ከሚረዱ የጥናት ዘርፎች አንዱ የድርሰት ስህተትት ትንተና ጥናት ነው፡፡በዚህም መሰረት በዋናነት በ9ኛ ክፍል ያሉ የካፊኖኖ ቋንቋ አፈፊት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚያጋጥማቸውንችግሮች ለመመርመር እና የችግሮችን ምንጭ ለመተንተን ተማሪዎቹ በጽህፈት የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርኣት የሚተገብሩበትን አቅጣጫ ለመጠቆም ይህን ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖል፡፡

### 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

አንድ የቋንቋ ተማሪ አንድን የቋንቋ ትምህርት ከተማረ በኋላ የቋንቋውን ስርአት ጠብቆ መናገር፣ ማንበብ፣ መፃፍና ማዳመጥ ይጠበቅበታል፡፡ተማሪዎች የቋንቋውን ክሂል ተማሩ የሚባሉት የቋንቋውን ስርአት ተገቢ በሆነ መንገድ ተጠቅመው ክሂሉን ተግባር ላይ ማዋል ሲችሉ ጭምር ነው፡፡

አጥኝዋ ለጥናቱ መነሻ ያደረገችው የመጀመሪያው ምክንያትከፍኛ ቋንቋ በሚነገርበት አካባቢ በሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመምህርነት በምታገለግልበት ወቅት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉያስተዋለቻቸውየፊደላት አለቦታቸው መግባት፣ አላስፈላጊ ድግግሞሽ፣ የጾታ አለመስማማት፣ የአጣማሪዎች ያለቦታቸው መግባት፣ የቁጥር አለመስማማት፣ የቃላት አለቦታቸው መግባት ወዘተ) በተደጋጋሚ ማየትነው፡፡

ሁለተኛውተማሪዎቹ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን(10ኛክፍል) ካጠናቀቁም በኋላ ክሂሉን በሚገባ መተግበር አለመቻላቸው በተለይም አጥኝዋበምታስተምርበት ትምህርት ቤት የትምህርት ማስረጃቸውን ለመውሰድ የሚመጡት የግል ማመልከቻቸውን እንኳን በተገቢው መንገድ ጽፈው አለማቅረባቸው ትኩረቷ በድርሰት አጻጻፍ ላይ እንዲሆን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

### 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ይህጥናትለሚከተሉት ዋናዋና የምርምር ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፤ እነሱም

1 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛቋንቋ ድርሰት ሲጽፉየሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንድናቸው?
2 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛቋንቋ ድርሰት ሲጽፉየሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንጭ ምንድነው?

### 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በካፋ ዞን በሚገኙ በሶስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ በተለይም በከፍኛ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ

ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶችን አይነቶችና ምንጮችን በመመርመር ለችግሩ መፍትሄ መሻት ነው፡፡

**የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች**

ጥናቱ ከላይ የተጠቀሰውን ዋናዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ዝርዝር አለማዎች ይኖሩታል፡፡እነዚህም

1. የከፍኛአፈ-ፈትየ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛቋንቋ ድርሰት ሲጽፉየሚፈፅሟቸው ስህተቶችን አይነት መለየት
2. የከፍኛ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ምንጭ ማጤን

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

የተማሪዎችን ስህተት ማጥናት ተማሪዎች ትምህርት የሚቀሰሙበትን ዘዴመረዳት እንደሆነ Corder (1981) እና Littlewood (1984) ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም በካፊኖኖ አፈ-ፈት የ9ኛክፍል ተማሪዎች የአማርኛቋንቋ ድርሰት ሲጽፉየሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትንተና በሚል የተደረገው ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል፡፡

1 በተተኳሪ የክፍልደረጃ ለሚያስተምሩ መምህራን በመጻፍ ክሂል ትግበራ ወቅት በተለይ በድርሰት አጻጻፍ የሚያጋጥሙ ችግሮችን እና የችግሩን ምንጭ በመመርመር መፍትሄ ለማግኘት በጉዳዩ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ ጥቆማ ይሰጣል፡፡

2 የአማርኛ ቋንቋ መፃህፍትዝግጅት ባለሙያዎች ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ምን ምን ነጥቦችን ማካተት እንዳለባቸው ጠቋሚ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

3 ከዚህ ጥናት በሚገኙ ፍንጮች መሰረት በተመሳሳይ ለሚያጠኑ ሌሎች አጥኚዎች የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በደቡብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በምትገኝ ካፋ ዞን በሚገኙ በተመረጡ ሶስት ወረዳዎች ዴቻ ፣ ጊምቦ እና ቦንጋ ከተማ በሚገኙ አውራዳ፣ጊምቦ እና ግራዝማች ጳውሎስበተሰኙ በናሙናነት በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኩራል ፡፡ በእነዚህ ት/ቤቶች በ2011ዓ.ምከሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከፊኛ የሆኑት ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡ ጥናቱ በድርሰት ውስጥ ከሚፈጸሙ ስህተቶች ውስጥ ከፍተኛ የተደጋጋሚነት መጠን ያላቸውን ስህተቶችን ብቻ በመተንተን ዋነኛ ናቸው ተብለው የሚገመቱ ከስህተት ምንጭ መላምቶች አንፃር በተማሪዎቹ ድርሰት ውስጥ ያሉትን የቋንቋ አወቃቀርና ከስርአተነጥብ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ስህተት ምንጮችን በማብራራት ላይ ተወስኗል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የስህተት ምንነትና ዓይነቶች

### 2.1.1 የስህተት ምንነት

Corder(1974፣ 24) ሰህተት ከተለምዶአዊው የቋንቋ አጠቃቀም ውጪ ያፈነገጠ ቢሆንም ስርዓታዊ ነው፡፡እያንዳንዱ ስህተት ለመፈጠሩ ከበስተጀርባው ስርዓታዊ ምክንያት አለ ይላሉ፡፡ በዚህ የተነሳም አንዱ የሚሳሳተውን ሌላውም ሊሳሳት ይችላል፡፡ ግድፈት ግን ስርዓታዊ ባለመሆኑ አንዱ የሚገድፈውን ሌላው ላይገድፈው ይችላል፡፡ Corder እንደሚያብራሩት በማስተዋል ችግር፣ በድካም፣ በጭንቀት ወዘተ.የተነሳ ስህተት ሊፈጸም ይችላል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚፈጸም ስህተት ግድፈት እንለዋለን፡፡ መጀመሪያ ግድፈት የፈፀመው ሰውም ቢሆን እንኳን ድጋሚ ያንን ላይፈጽም ይችላል፡፡ ስለዚህ ግድፈት ወጥነት ያለው አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ስህተት የቋንቋ አጠቃቀም ደረጃን የሚያመለክት ሲሆን፣ ግድፈት ግን የቋንቋ ዕውቀት ደረጃን ላያመለክት ይችላል (Hammerly ፣ 1991፣83)፡፡

Norish (1992፣7) ስህተት የሚባለው ከዘወትራዊው የቋንቋ አጠቃቀም በማፈንገጥ የሚቀርብ የቋንቋ ቅርፅ ነው፡፡

Dulay etal (1982፣139)ስህተት የታላሚውን ቋንቋ ስርዓት በአግባቡ ካለመረዳት ሊመነጭ ይችላል፡፡ በዚህ የተነሳም የቋንቋ ተማሪው ስርዓታዊ በሆነ ሁኔታ ሊሰሳት ይችላል፡፡ ይህም ማለት ተማሪው እስኪታረም ወይም አፍ ፈት ተናጋሪዎች እንደዚያ እንደማይሉ እስኪገነዘብ ድረስ ትክክል ነው ብሎ በስህተቱ ይቀጥላል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚፈጠረውን ስህተት እንለዋለን፡፡

Brown ( 1994፣ 254-255) አክለው እንደሚገልጹት ይህ ዓይነቱ ስህተት በቋንቋ ትምህርት ላይ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም የሕይወት ልምዳችን ውስጥም ሊያጋጥመን ይችላል በማለት የውሃ ዋና የሚለምድን ሰው በምሳሌነት ያነሳሉ፡፡ ውሃ ዋና፣ ውሃ ውስጥ እንደገቡ በቅጽበት የሚካኑት ጉዳይ ሳይሆን ጊዜን የሚጠይቅ ነው የሚሉት Brown የቋንቋ ትምህርትም እንዲሁ ጊዜ ይወስዳል፡፡በመሆኑም በዚህ ሂደት ውስጥ በተሟላ ሁኔታ የቋንቋን ህግ ሳያውቁ የሚፈጠሩ ስርዓታዊ መሳሳቶችም ስህተት ይባላሉ፡፡

Johnson (1976፣20) እንደሚያስረዱት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቢያንስ በሁለት ምክንያቶች ስህተትን ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡ አንደኛው ምክንያት ተማሪዎች በሚማሩት ቋንቋ ዙሪያ በቂ እውቀት ሊኖራቸው ባለመቻሉ ወይም የተዛባ እውቀት በመጨበጣቸው የተነሳ የሚከሰት ስህተት ሲሆን ይህንንም ስህተት (Error) ብለን እንጠራዋለን፡፡ ተማሪዎች ስህተት የሚፈጽሙበት ሌላውና ሁለተኛው ምክንያት በቋንቋው በተፈለገው ደረጃ ባለመጠቀማቸው የተነሳ በሚከሰት የልምድ ማነስ ነው፡፡ ተማሪዎች በቋንቋው በበቂ ሁኔታ አለመገልገላቸው የችሎታ ማነስ እንዲያጋጥማቸው ያደርጋል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ስህተት መኪና እንዴት መንዳት እንደሚቻል እያወቁ በአግባቡ መንዳት እንደ አለመቻል ይቆጠራል፡፡ የዚህ ስህተት መከሰት ምንጩ የእውቀት ማነስ ወይም የተዛባ እውቀት በመጨበጥ ሳይሆን የልምምድ እጥረት ነው፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚከሰትን ወይም የሚፈጠርን ስህተት ግድፈት (Mistake) ልንለው እንችላለን፡፡

Nagara (1983 ፣35) አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች አንድን ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች የለያዩ ስህተቶችን ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ስህተቶችም በተማሪዎቹ የንግግር ቋንቋ ወይም የጽህፈት ቋንቋ ላይ የሚታዩና ተማሪው በታላሚው ቋንቋ ለመናገር ወይም ለመጻፍ በሚያፈልቅበት ጊዜ ከስነድምጽ፣ ከሰዋስው፣ ከቃላትና አጻጻፍ ያፈነገጡ ሲሆን ስህተቶችም አነባበባዊ፣ ሰዋስዋዊ ፣ የአጻጻፍ ስህተቶችና የአጠቃቀም ስህተቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም አንድ አንባቢ ወይም አድማጭ እነዚህን ስህተቶች የሚገነዘባቸው ከታላሚው ቋንቋ ስነልሳናዊ ህግ የተለዩ መሆናቸውን ነው፡፡

ከዚህም የምንረዳው ስህተት ከተለመደው የቋንቋ አጠቃቀም ያፈነገጠ የቋንቋ ቅርጽ ከአፍ መፍቻ ቋንቋነት ከሚነገር ቅርጽ ያፈነገጠ ወይም የተለየ ስነ ልሳናዊ ቅርጽ እንደሆነ ወይም ስህተት ከመደበኛው የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ወጣ ያለ ቅርጽ መሆኑንና ስህተት በጽሁፍም ሆነ በንግግር ውስጥ የሚስተዋሉ ወይም የሚፈጸሙ የተሳሳቱ የቋንቋ አጠቃቀሞችን የሚመለከት ጽንሰ ሀሳብ መሆኑን ነው፡፡

### 2.1.2 የስህተት ዓይነቶች

ተማሪዎች በአንድ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት የተለያዩ ስህተቶችን ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡እነዚህ ስህተቶችም ከተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ከቅድመ ቋንቋ እውቀቱና ከመሳሰሉት ጉዳዮች ተጽእኖ አንጻር የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው ጠቅለል ባለ መልኩ ካልሆነ በቀር የስህተት ዓይነቶችን በዝርዝር መተንተን አለመቻሉን ነው፡፡ ይህንንም ሀሳብ ምሁራን እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

Tomiana (1980፣72) ከስነድምፃዊ ባህርያት አንጻር የሚመነጩ የስህተት ዓይነቶች አስፈላጊ የሆኑ ድምጾችን በመግደፍ ወይም በአላስፈላጊ ቦታ አላስፈላጊ ድምጾችን በማስፈር ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ እንደ ስነ ድምጻዊ ስህተቶች ሁሉ ስነምዕላዳዊ እና የቃላት ስህተቶችም አስፈላጊ በሚሆኑበት ቦታ በመግደፍና በማያስፈልግበት ቦታ ደግሞ በመጨመር በስህተትነት ይመዘገባሉ፡፡

Corder (1974፣ 156-261) ደግሞ የስህተት ዓይነቶች ግልጽ ስህተት እና ስውር ስህተት በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ግልጽ ስህተት የሚባለው ከሰሙ

እንደምንረዳው በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የተፈፀመን ስህተት ዐረፍተ ነገሩን በማየት ብቻ የምንለየው የስህተት ዓይነት ሲሆን፣ ስውር ስህተት የሚባለው ደግሞ እንደ ግልጽ ስህተት ዐረፍተ ነገሩን በማየት ብቻ የሚለይ ሳይሆን ስህተቱን ፈልፍሎ ለማውጣት ወይም ስህተቱን ለማወቅ አረፍተ ነገሩን በጥልቀትና በጥሞና መመርመርን የሚጠይቅ የስህተት አይነት ነው።ከተጠቀሱት ብያኔዎች መረዳት እንደሚቻለው በተማሪዎች ንግግርም ሆነ ጽሁፍ የሚፈጸሙስህተቶች ግድፈት ወይም ስህተት ተብለው እንደሚከፈሉ ነው፡፡

### 2.2 የስህተት ትንተና ምንነት

Brown (1994:206) የስህተት ትንተና ማለት የተማሪዎችን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግለጽ ሲባልበበርካታ ሰዎች ዘንድ ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የሚታዩበት፣የታዩት ስህተቶች የሚተነተኑበትና የተተነተኑትም የስህተት አይነቶች በተለያዩ ምድብ አይነቶች የሚቀመጡበትዘዴ ነው፡፡

የስህተት ትንተና የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ደረጃ የሚያሳይ መስታወት በመሆኑ፣ መምህራን በተማሪዎቻቸው የድርሰት ሥራ ላይ የስህተት ትንተና ቢያከናውኑ የመማር ማስተማር ሂደቱን ውጤታማ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም የስህተት ትንተና አቢይ ጠቀሜታውም ተማሪዎቹ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በመምህሩ ረዳትነት ተመልክተው የራሳቸውን ስህተቶች በራሳቸው፣ አልፎ ተርፎም ስህተቶቻቸውን ከቢጤዎቻቸው ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ ከዚያም ራሳቸውን ሊያርሙ የሚችሉበት ደረጃ ይደርሳሉ፡፡

Corder (1974:19 )የስህተት ትንተና ስህተትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከፋፍሎ በማጥናት የስህተት ምንጮችን ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም ስለስህተት ያለውን አሉታዊ አመለካከት በማስቀረት ስህተትን እንደ አንድ የትምህርት ሂደት ይቆጥራል፡፡ከዚህም በመነሳት ለሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ፣ ለማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት እንዲሁም ተማሪዎች ያሉበትን የእውቀት ደረጃ ለማመልከት ያገለግላል፡፡ በአሰራሩም የቋንቋ ተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም በናሙናነት በመውሰድ ስህተቶችን ለይቶ ያወጣል፤ የስህተቶቹንም አይነት ምንጫቸው ምን

ሊሆን እንደሚችል መላ ይመታል፡፡በዚህ ጥናትም የከፍኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለመመርመር ተሞክሯል፡፡

### 2.2.1 የስህተት ትንተና ጠቀሜታዎች

በተማሪዎች ድርሰት ላይ የስህተት ትንተና ማካሄድ በርካታ ጠቃሜታዎች እንዳሉት የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

Dulay etal (1982፣138) በበኩላቸው የስህተት ትንተና አጠቃላይ የሆኑ ሁለት ጠቀሜታዎች አሉት ይላሉ፡፡ የመጀመሪያው ጠቀሜታ ቋንቋን የመማር ሂደት የተመለከቱ አንዳንድ መረጃዎችን ለማግኘት የስህተት ትንተና የጐላ ጠቀሜታ እንዳለው የተገለጸበት ነው፡፡ ሁለተኛው ጠቀሜታ ደግሞ ከቋንቋ መምህራንና ከስርዓተ-ትምህርት ቀራጮች ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ የስህተት ትንተና ለእነዚህ ባለሙያዎች የትኛው የስህተት ዓይነት ተማሪዎችን እንደሚያስቸግራቸውና የትኛው ስህተት ደግሞ የተማሪዎችን ተግባበታዊ ሂደት እንደሚያሰናክል ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ባለሙያዎቹ ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚያደርጉትን ጥረት ያግዛል፡፡

Norish (1992፣ 80) ከላይ የተጠቀሱትን ሃሳቦች ባቀፈ መልኩ የስህተት ትንተና የተለያዩ ጠቀሜዎች አሉት ይላሉ፡፡ ከእነዚህ ጠቀሜታዎች አንዱ መምህራን ስለሚያጋጥሟቸው አዳዲስ ተማሪዎች ዳራዊ እውቀት ለማወቅ ማገዝ ነው፡፡ መምህራን ለማስተማር አንድ አዲስ ክፍል በገቡ ቁጥር የስህተት ትንተና ለማድረግ ከቻሉ ስለተማሪዎቻቸው ዳራዊ እውቀት መረጃዎችን በማግኘት የትኛውን ይዘት በምን ዓይነት መልኩ፣ ለምን ያህል ጊዜ ማስተማር እንዳለባቸው እንዲወስኑ ያግዛል፡፡ በዚህ የተማሪዎችን ችግር በሚፈታ መልኩ የተደራጀ የማስተማር ሂደት እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡ በሌላ መልኩ የስህተት ትንተና፣ በአንድ ክፍል ውስጥ በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ካሉ፣ በሁለተኛ ቋንቋ መማር ሂደታቸው ላይ ለየትኞቹ ተማሪዎች የትኛው የቋንቋ ክፍል አስቸጋሪ እንደሆነ ለመረዳት ይጠቅማል፡፡ በዚህ የተማሪዎችን የጋራና የተናጠል ችግር በክፍልም ሆነ በሀገር ደረጃ ለመገንዘብና ችግሮቻቸውን ለማቃለል የሚደረጉ ጥረቶችን ለማገዝ ይረዳል፡፡

ከተገለጸው ሀሳብ የምንረዳው የስህተት ትንተና የቋንቋ ትምህርቱ ከቀረበ በኋላ ብቻ የሚከናወን ጉዳይ አለመሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም በማንኛውም ጊዜ ሊካሄድ ይችላልና ነው፡፡ በዚህም መሠረት የቋንቋ መምህሩ ትምህርቱን ከመጀመሩ በፊት፣ ትምህርቱን በማስተማር ላይ እያለ አለበለዚያም የቋንቋ ትምህርቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የስህተት ትንተና በማካሄድ የትምህርቱን አቀራረብ ምን እንደሚመስል ሊመዝን፣ ማሻሻያ ሊያደርግ እና የመፍትሄ ሀሳብ ሊያፈላልግ ይችላል፡፡በተማሪዎች ድርሰት ላይ የስህተት ትንተና ማካሄድ በርካታ ስነ-ትምህርታዊ ጠቃሜታዎች እንዳሉት በተለያዩ ምሁራን እንደ ተገለጸውም በይበልጥ ለመምህራን ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ የስህተት ትንተና ስልቶችን ለመምህራን ማስጨበጥ በራሱ ጠቃሚ ሆኖ፣ በዚህ ስልት ተጠቅመው መምህራን የተማሪዎቻቸውን ስህተት መተንተን ከቻሉ ደግሞ የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ ይረዳቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት የትኞቹ ተማሪዎች ምን ዓይነት ስህተቶችን እንደፈፁሙ በመረዳት እነዚያን ስህተቶች ሊቀንሱ የሚችሉ እርምጃዎችን ለመውድ ያስችላችዋል፡፡ ተማሪዎቻቸው ስህተት የፈፀሙበትን ምክንያት በግልጽ በማሳየት፣ ተማሪዎቹም በራሳቸው ሂደት ስህተቱን የሚቀንሱበትን መንገድ ለማመቻቸት ያስችላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ የስህተት ትንተና ለመምህራን ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን፣ በዚህም የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማቃናትና ለማቀላጠፍ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

## 2.2 የስህተት ምንጮች

በስህተት ትንተና ጥናት ውስጥ የተማሪዎች ስህተት የሚመነጨው ከተለያዩ ምክንያቶች ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ያም በመሆኑ እንደሚጠኑት ቋንቋዎችና ተማሪዎች እንዲሁም እንደ አጥኚዎች አተያይ የስህተት ምንጮች በተለያዩ ክፍሎች ተመድበው ይቀርባሉ፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ አያሌ ምክንያቶች መኖራቸውን የሁለተኛ ቋንቋ መማርን በተመለከተ የተጻፉ ድርሳናት ይጠቁማሉ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም ዋና ዋና በመባል የሚታወቁት የስህተት መከሰቻ ምንጮች ተዳሰዋል፡፡ እነዚህ በአብዛኞቹ ምሁራን ጥናቶች ውስጥ ተደጋግመው የሚሰነዘሩት የስህተት መከሰቻዎች፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት

(ተጽእኖ)፣ ውስጥ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶች እና ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥም የስህተት መንስኤዎች ይሆናሉ ተብለው የሚታወቁትን የስህተት ምንጮች መሠረት በማድረግ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ለሚከሰቱት ስህተቶች በተለያዩ መልኮች የስህተት መንስኤዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ ይህ ጥናት በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ወይም የመልመድ ሂደት ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው በመስኩ ባለሙያዎች ተዘውትረው የሚጠቀሙ መላምቶችን ያካተተ ነው፡፡ እነዚህም የስህተት ምንጮች ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ንዑሳን ክፍሎች በአጭር በአጭሩ ተዳሰዋል፡፡

### 2.2.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት

ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አሉታዊ ተጽእኖ ተማሪው ለሚፈጽማቸው ስህተቶች እንደ አንድ ምክንያት ሊወሰድ እንደሚችል በርካታ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡

Dulay etal( 1982፣ 96) በአፍ መፍቻነት የዳበረ የቋንቋ ልምድ አንድን አዲስ ቋንቋ በመማር ሂደት ጣልቃ በመግባት በሚያደርሰው አሉታዊ ተጽእኖ የተነሳ ስህተት ሊፈጸም ይችላል::

Norish (1992፣ 22) ቋንቋን የመማር ሂደት የተሞክሮ (የልምድ) ስብስብ ውጤት ስለሆነ የተማረው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምድ ጣልቃ በመግባት የስህተት ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡

ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው፣ ቋንቋን እንደ ልምድ ክምችት አድርገን ከቆጠርን አዲስ ቋንቋን በምንለምድበት ጊዜ አዲስ ልምድ ማደበራችን አይቀሬ መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አሮጌው (የቀደመው) ልምድ በአዲሱ ልምድ ላይ ተጽእኖ ማድረሱ የሚጠበቅ እንደሆነ ያሳየናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ የድምጽ ዓይነቶች በሌላ ቋንቋ ውስጥ ላይኖሩ ይችላሉና ያንን ቋንቋ በምንማርበት ወይም በምንለምድበት ጊዜ ስነ ድምጻዊ ችግሮች ሊኖሩ

ይችላሉ፡፡ ከዚህም ውጪ በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያለ የአረፍተ ነገር መዋቅር በሌላ ቋንቋ ላይኖር ይችላል፡፡ ስለዚህ አንድን ሁለተኛ ቋንቋ የሚማር ተማሪ ቀደም ብሎ ያውቀው የነበረው የቋንቋ መዋቅር ተጽእኖ፣ አዲስ በሚማረው ወይም በሚለምደው ቋንቋ ላይ ያርፋል፡፡ በዚህ የተነሳም ተማሪውን ለስህተት ሊዳርገው ይችላል፡፡ ከእነዚህ ሁነቶች መረዳት የሚቻለው በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ከዋነኞቹ  የስህተት ምንጮች እንደ አንዱ ሊቆጠር እንደሚገባው ነው፡፡

አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ታለሚውን ቋንቋ በሚማሩበት የመጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚፈጽሟቸዉ ስህተቶች መንስኤያቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ እንደሆነ በበርካታ ምሁራን ተረጋግጧል፡፡ በእነዚህ የመጀመሪያ ደረጃዎች የሁለተኛ ቋንቋውን አጠቃቀምና ስርዓት ከመልመዳቸው አስቀድሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ብቸኛው ልምዳቸው ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ተማሪዎቹ አፍ ከፈቱበት ቋንቋ ሀሳብ እየወሰዱ በታላሚው ቋንቋ ውስጥ ይገለገላሉ፡፡ በሚገለገሉት ወቅት ተጽእኖው አወንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ አውንታዊ የምንለው የታላሚው ቋንቋና የተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ አንድ ዓይነት ባህርይ ሲኖረው ሲሆን በዚህን ወቅት ተማሪው ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ተጽእኖው አሉታዊ የሚሆነው ግን የተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋና ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ የተለየ መዋቅራዊ ስርዓት ይኖራቸውና ተማሪው አፍ የፈታበትን የቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት በታላሚው ቋንቋ በሚጠቀምበት ጊዜ ስርዓቱ ከታላሚው ቋንቋ ስለሚያፈነግጥበት ለስህተት ይጋለጣል፡፡ ስለሆነም አሉታዊ ተጽእኖ ለስህተት ምንጭ እንደሆነ በብዙዎቹ ይታመናል፡፡ ይህም የቀደመው ትምህርት በአዲሱ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ በአፍ መፍቻና በሁለተኛ ቋንቋ አንድ አይነት እሳቤን ለመግለጽ የተለያዩ አገላለጾችን መጠቀም የግድ ነነው፣ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው በሚማረው ቋንቋ ሀሳቡን ለመግለጽ ሲፈልግ የአፍ መፍቻ ቋንቋውን አገላለጽ ከተጠቀመ ለስህተት ይዳረጋል፡፡ ይህም ስህተት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ሳቢያ የተከሰተ ነው፡፡

ከፍ ብለው ከተጠቀሱት ሀሳቦች ባሻገር የታላሚው ቋንቋ (ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ) ትክክለኛ የሆነ ቃል ወይም ጽንሰ ሀሳብ ግር በሚልበትና

በማይታወቅበት ወቅት የአፍ መፍቻ ቋንቋን የተለያዩ ስነ ልሳናዊ ባህርያት እንዳለ ቃል በቃል በመተርጎም ለመጠቀም ሙከራ በሚደረግበት ጊዜ ስህተት ሊፈጠር እንደሚችል Norish (1992፣ 42) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም የአንድን ቋንቋ ፍጹም አቻ የሆነውን መዋቅር ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ፣ ለትምህርት የቀረበውን (ታላሚውን) ቋንቋ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጎም የስህተት ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ምንም እንኳን ጣልቃ ገብነትና ትርጉም ለስህተት መፈጠር ምክንያት ናቸው ቢባልም በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ግን ሊታወቅ ይገባዋል፡፡ ስለሆነም ጣልቃገብነት ሲባል በተማሪው አእምሮ ምንም ሳይታሰብ የሚፈጸም ሲሆን፣ ትርጉም ግን ተማሪው አማራጭ ሲያጣ የሚጠቀምበት ነው፡፡

ከተዘረዘሩት ነጥቦች መገንዘብ እንደሚቻለው ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ የተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት በቁጥር በጣም ጥቂት ለሆኑ ስህተቶች መፈጠር (መፈጸም) ምንጭ ሊሆን የሚችል እንጂ፣ ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ ለሚከሰቱ በርካታ ስህተቶች ብቸኛ የስህተት መንስኤ አለመሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ለተተኳሪው ቋንቋ የስህተት ምንጭ ሊሆን እንደሚችል ይታሰብ እንጂ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምድ ሁሉ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ብቸኛ የስህተት መንስኤ ነው ብሎ መወሰንአያስችልም፡፡

### 2.2.2 ውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ

ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም ከተተኳሪው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት የሚመነጭ ሳይሆን ተተኳሪውን ቋንቋ ለተግባበታዊ አገልግሎት ለማዋል ሙከራ ሲደርግ ለሚያጋጥሙት አዳዲስ ነገሮች ራሱ በሚፈጥረው ህግ ተጠቅሞ ለማለፍ ሲጥር የሚፈጠር ወይም የሚከሰት የስህተት ዓይነት እንደ አንድ የስህተት ምንጭ ይቆጠራል፡፡

Brown (1994፣ 203) በውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ የተነሳ (ምክንያት) የሚከሰት ስህተት የአፍ መፍቻ ቋንቋን ወይም የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት የተከተለ አይደለም፡፡ ነገር ግን ተማሪው በሁለተኛ ቋንቋ ለመግባባት ሲሞከር ራሱ በሚሰጠው የቋንቋ ህግ አማካኝነት የሚከሰት ስህተት ነው ሲሉ ይገልጹታል፡፡

Littlewood (1986፡23)፣ Norrish (1992፡31-32) እንደገለጹት የቋንቋ ተማሪዎችን ለውስጠ ቋንቋ ስህተቶች የሚያጋልጣቸው የተሳሳተ ማጠቃለያ ብቻ አይደለም፤ ያልተሟላ ትምህርት፣ የተሳሳተ ተዛምዶ እና ቃላትን አላግባብ መጠቀም በውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ለሚፈጠሩ ስህተቶች ምክንያቶች ናቸው፡፡

Negara (1983፡37-40) አገላለጽ ባልተሟላ ትምህርት የሚፈጠር ስህተት ስንል የቋንቋ ተማሪው የቋንቋውን መዋቅር፣ ቃላት፣ የአገላለጽ ስልት ወይም ሌሎች የቋንቋውንባህሪያት በከፊል በመማሩ የተነሳ የሚፈጠረውን ስህተት ማለታችን ነው፡፡ ስለዚህም ተማሪው በቋንቋ የሚገኙትን ፊሊጣዊ አነጋገሮች እና ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንዲሁም ሰዋስዋዊ ሥርዓቶች በከፊል በትክክል፣ በከፊል ደግሞ በስህተት ሲያፈልቅ ይስተዋላል፡፡

ይህም ታላሚው ቋንቋ በአብዛኛው የሚጠቀምበት የራሱ መዋቅራዊ ስርዓት ይኖረውና፣ ያ መዋቅራዊ ስርዓት ለሁሉም ቋንቋዎች የማይሠራ ከሆነ ተማሪዎች መዋቅራዊ ስርዓቱን በአጠቃላይ ለቋንቋው እንደሚሠራ አድርገው ሲቀበሉትና ሲጠቀሙበት የሚከሰተውን ስህተት ያመለክታል (Brown፣ 1994፣ 214፤ Littlewood፣ 1986፣ 23) ፡፡

ለምሳሌ ይህንን ወደ እኛ ሀገር እውነታ ወስደን ብንመለከተው በአማርኛ ቋንቋ ሰራ ብሎ ሰሪ፣ ፈራ ብሎ ፈሪ እንደሚባል የተገነዘበ (የተረዳ) አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማር ተማሪ "መታ" የሚለውን ቃል መሠረት በማድረግ "መቲ"" ቢል በተሳሳተ ማጠቃለይነት የተነሳ የፈጸመው ስህተት ነው ለማለት እንችላለን፡፡

Richards (1974፣ 174) እንደሚገልጹት በውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ የተነሳ የሚከሰቱ ስህተቶች የቋንቋውን አጠቃላይ ህግጋት ከመተግበር ጋር የሚያያዙ ስህተቶች ሲሆኑ፣ እነዚህም የተሳሳተ ማጠቃለያ፣ያልተሟሉ ህግጋትን መጠቀም (incomplete application of rules)፣ በቋሚነት የሚሰሩ ህግጋትን በሚገባ ለይቶ አለማወቅ ፣ የተሳሳተ ጽንሰ ሀሳቦችን መገልገል እና የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል፡፡

Dulay etal (1982፣ 138-139) በበኩላቸው በውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ ምክንያት የሚከሰቱ ስህተቶች የተለያዩ መገለጫዎች እንዳሏቸው በሚከተለው መልኩ ያስቀመጧቸዋል፡፡

1. በድግግሞሽ (Double marking)፡- በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ አንድን የቋንቋ ቅርጽ አንድ ጊዜ ብቻ መገልገል (መጠቀም) ሲቻል፣ ያንኑ ቅርጽ በሌላ መልኩ መድገም ለተለያዩ ስህተቶች ይዳርጋል፡፡ በማያስፈልግ ደግግሞሽ ምክንያት የሚፈጸሙ ስህተቶቸ እንዳሉ ምሁራኑ አክለው ይገልፃሉ ፡፡

2. በተሳሳተ ድምዳሜ (Faulty over generalization) ፡- የተሳሳተ ድምዳሜ ተማሪው ለትምህርት የቀረበውን (የታላሚውን) ቋንቋ ህግጋት ቀድም ሲል በለመዳቸው ህግጋት አጠቃሎ ለመጠቀም ሙከራ በሚያደርግበት ወቅት የሚከሰት ስህተት ሲሆን፣ ይህም ቋንቋን በመማር ሂደት ተማሪው ከሚጠቀምባቸው የመማር ስልቶች (Learning Styles) መካከል ግንባር ቀደሙ ነው፡፡ በመማር ሂደቱም ተማሪው የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት የጣሱ ሰዋስዋዊ መወቅሮችን ለመስራት ይችላል (Littlewood፣ 1984፣ 23)፡፡ በዚህም የተነሳ ተማሪው ተቀባይነት የጐደላቸውን (የሌላቸውን) የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት አስመስሎ በጥቅል (በጅምላ) ለመጠቀም ሙከራ ሲያደርግ ለተሳሳተ ይችላል፡፡

3. እከላ (Simple addition)፡- እከላ የማያስፈልጉ ድምጾችን፣ ቅጥያዎችን ወይም ቃላትን በመጨመር ስህተት የሚከሰትበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡

4. ግድፈት (omission) ግድፈት በስርዓት በተዋቀረ ዐረፍተ ነገር ውስጥ መገኘት የሚገባው የዐረፍተ ነገር ተዋቃሪ ካለመሟላቱ የተነሳ የቋንቋ ስርዓቱ የሚፋለሰበትና ስህተት የሚከሰትበት ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም የቋንቋ ተማሪው በቋንቋ ለመዳ ሂደት መቅረት የሌለውን የዐረፍተ ነገር ተዋቃሪ አካል ሊገድፍ ይችላል (Dulay etal፣ 1982፣ 150-155)፡፡

5. በቅደም ተከተል መፋለስ፡- በቅደም ተከተል መፋለስ የተነሳ የሚከሰቱ ስህተቶች መገለጫቸው ቅጥያዎች ወይም ቃላት ያለቦታቸው መደንቀር እንደሆነ Dulay etal (1982፣ 102) ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ የምንረዳው የቋንቋውስርዓት በማይፈቅደው መልኩ ምዕላዶችን (ቅጥያዎችን) እና ቃላትን አፋልሶ መጠቀም ለስህተት መፈጠር ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የተግባባቱን ሂደት ሊደናቅፍ ይችላል፡፡የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ ስህተት የሚያመለከተው የቋንቋ ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ በከፊል በመረዳቱ የተነሳና በታላሚው ቋንቋ ውስብስብ ባህርይ የተነሳ የሚፈጽማቸውን ስህተቶች ነው፡፡ የስህተት ምንጩም የታላሚው ቋንቋ ውስብስብ ባህርይ ነው እንበል እንጂ ዝርዝር ምክንያትቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ እነዚህን ስህተቶች ሊፈጥሩ ከሚችሉ በርካታ ምክንያቶች ውስጥም የቋንቋ መምህሩ የቋንቋ ይዘቶችን ለተማሪዎች የሚያቀርብበት ስልት፣ የመማሪያ መጻህፍት የትምህርት ይዘቶችን የሚያደራጁበት ሁኔታ እና ተማሪዎች እንዲሰሯቸው የሚደረጉ መልመጃዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህና ከመሰል ጉዳዮች በመነጩ ሁኔታዎች ተማሪዎች ከላይ ለቀረቡት ስህተቶች ሊዳርጉ ይችላሉ (Norish፣ 1992፣ 32)፡፡ ስለዚህ የውስጠ ቋንቋ ስህተቶች በተሳሳተ ድምዳሜ፣ የታላሚውን ቋንቋ ስርዓት (ህግ) ባልተሟላ መልኩ በመተግበር፣ በሰነ ትርጉማዊና በስነ አገባባዊ ስህተቶች ምክንያት ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡

### 2.2.3 የማስተማሪያ መሣሪያዎች እና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት

ከተለያዩ ጥናቶች መገንዘብ እንደሚቻለው ተማሪው ለሚያዳብረው የተሳሳተ የቋንቋ አጠቃቀምና የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ሰበብ ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል ዋናዋቹ በማስተማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶች አመራረጥ፣ አቀራረብ፣ አደራጃጀትና መምህራን የሚከተሏቸው የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

Richards (1974፣ 190) ይህን አስመልክተው እንደሚገልጹት የቋንቋ መጻህፍትን በአግባቡ አለማደራጀትና ትክክለኛ ይዘቶችን ይዞ ያለመገኘት ሁኔት ተማሪዎችን ለስህተት ሊዳርግ ይችላል፡፡ ከዚህ አኳያ የማስተማሪያ መጻህፍት አደራጃጀትና አወቃቀር እንዲሁም መልመጃዎችን ያቀረቡባቸው ስልቶች የስህተት ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም መምህሩ የሚከተለው የማስተማር ዘዴና ክፍል

ውስጥ የሚያቀርባቸው መልመጃዎች የስህተት ምንጮች ሆነው ሊገኙ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ባልተሟላ መልኩ ከቀረቡም ወደ ስህተት ሊመሯቸው እንደሚችሉ ከፍ ብለው የተጠቀሱት ምሁር ያስረዳሉ፡፡ ቋንቋ ለማስተማር የሚዘጋጁ የማስተማሪያመሣሪያዎች(መጻህፍት፣መርሃ ትምህርት ወዘተ.) እና መምህራን የሚከተሏቸው የማስተማር ዘዴዎችም የስህተት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ በስህተት ዙሪያ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች እንደ ስህተት ምንጭ አድርገን መውሰዳችን ትክክለኛና ተገቢ ነገር ነው የሚሉት Norish (1992፣ 14-15) በዋነኛነት መምህሩ የሚያስተምረውና ተማሪው የሚቀበለው ይዘት የተለያዩ የሚሆኑበት አጋጣሚ መኖሩን ለሚያጤን ሰው፣ እነዚህ ጉዳዮች የስህተት ምንጮች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይረዳል ይላሉ፡፡ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ሁሌም መምህሩ ለተማሪው ማስረዳትና ማስጨበጥ የፈለገውን ይዘት በትክክለኛ መንገድ ላያስተላልፍ ይችላል፡፡ ከዚህ ይልቅ መምህሩ ለማለት የፈለገውን ሳይሆን ያላለውን ይዘት ተማሪዎቹ ሊቀበሉ ይችላሉ፡፡ ይህ አይነቱን ሁኔታ መምህሩም ሆነ ተማሪው ፈልገው የሚያወጡት አይደለም፡፡ የዚህ መንስኤ በዋነኛነት የመማር ማስተማሩ ሂደት በአግባቡ ባልተደራጀ የማስተማሪያ ስልት በመቅረቡ የሚፈጠር ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ዓይነት ክፍተት የተነሳ ተማሪዎቹ ስህተት ሊፈጽሙ የሚችሉ ሲሆን፣ Norish እንደሚሉትም ይህንን ሁኔታ በአግባቡ ማጥናት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በተጨማሪም የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎቹን ስህተት ሊቀንስ የሚችለው ተማሪዎች የሚጽፉትን እንዲከልሱት በማድረግና ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ነው፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት ለጽሁፍ እርማት መሰጠት ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለመቀነስ ያስችላል፡፡ ነገር ግን እርማት የማይሰጥ ከሆነ ስህተቱን ከትክክሉ ለይተው ማወቅ ስለማይችሉ ስህተቱን እንደ ትክክል በመያዝ ከራሳቸው ጋር ሊያዋህዱት ይችላሉ፡፡

white (1994፣ 109) ይህን አስመልክተው እንደገለጹት፣ ልምምድ ብቻውን የቋንቋ ችሎታን አያሳድግም፡፡ ስህተት እየተተነተነ የማይታይ፣ ለስህተቱም እርማት የማይሰጥ ከሆነ የተማሪው የጽሁፍ ስህተት ወደ ስር ሰደድነት ከፍ ሊል

ይችላል፡፡ስህተት መታረም አለበት ሲባል መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ስህተት ቃል በቃል እየነቀሰ በማውጣት ማረም አለበት ለማለት አይደለም፡፡ ሆኖም የስህተት እርማት ብዙውን ጊዜ መካሄድ ያለበት በራሱ በተማሪው ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪው የራሱን ስህተት በራሱ ነቅሶ ካወጣና ማስተካከያ ከሰጠ ቋንቋውን በተገቢ ሁኔታ ተገንዝቦታል ማለት ያስችላል፡፡ ስለዚህ መምህሩ የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሞ ተማሪው የሰራውን ስህተት እራሱ እንዲያርመው ቢያደርግ የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደቱን ውጤታማ ያደርገዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ

Raimes (1983፣22)ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች እርስ በርሳቸው ማረም እንዲችሉ መምህሩ እድል መስጠት እንዳለበትና ስህተቱ ሊፈጽሙ የቻሉበትን ምክንያት እንዲያውቁ መርዳት እንደሆነ ይገልጸሉ፡፡

ስለሆነም በቋንቋ ተስተምህሮ ሂደት ውሰጥ የመምህሩ የማስተማር ችሎታ ሊለካባቸው ከሚችልባቸው መስፈርቶች መካከል የቋንቋ ትምህርትን ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብና የሚጠቀምባቸው የማስተማሪያ ዘዴዎቹ ውጤታማነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከፍ ሲል ከተገለጸው ሀሳብ የምንረዳው ስህተቶች ከመማር ማስተማር ድክመት፣ ከመርሃ ትምህርት የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ሊከሰቱ የሚችሉ መሆናቸውን ነው፡፡ የመምህሩ ማስተማር ብቃት የቋንቋ ትምህርቱን በተሳካ መልኩ ለማቅረብና የተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለመቅረፍ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን ቋንቋን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ዘዴ በመማር ማስተማሩ ሂደት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ገጽታ እንዳለው ያመለክታል፡፡

### 2.2.3 ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች

በሁለተኛ ቋንቋ መማር ሂደት ላይ ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ ያለው በጎ አመለካከት ትምህርቱን በሚገባ እንዲከታተል የመረዳቱን ያህል፣ በቋንቋው እና በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ላይ አሉታዊ አመለካከት ካደረበት ደግሞ ለመማር ያለው መነቃቃትይቀንሳል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪው ትምህርቱን በአግባቡ እንዳይከታተልና በቋንቋው ያለው ችሎታ ዝቅተኛ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

በዚህም የተነሳ ተማሪው ወደ ስህተት የሚሄድበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ የሚኖራቸው ማህበራዊና ስነልቦናዊ ሁኔታ ከቤተሰባቸው፣ ከአካባቢያቸው፣ ከጓደኞቻቸውና ከተለያዩ አንጻር የሚፈጠር ሊሆን ይችላል፡፡

Norish (1992፣ 19) የስህተት ምንጮች በተጨማሪ ተማሪዎች የተለያዩ ስህተቶችን እንዲፈጽሙ የሚያደርጓቸው ስነ ልቦናዊ ምክንያቶች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡አክለውም ስነ ልቦናዊ ጉዳይ ሲባል የሚያያዘው ከተማሪዎች የግል ጉዳዮች ጋር ሲሆን፣ ይህም ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ስላለው ሁኔታ በአእምሮአቸው ውስጥ ይዘውት የሚመጡት ጉዳይ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በአግባቡ እንዳይከታተሉ ስለሚያደርጋቸው ነው ይላሉ፡፡ አንድ ተማሪ ለሚማረው ቋንቋ በጎ ያልሆነ አመለካከት እንዲያድርበት የሚያደርጉት በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ በተለያዩ ሞህራን ይገለጻሉ፡፡ ለምሳሌ ተማሪው ቋንቋውን ከተማረ በኋላ ምንም ዓይነት ተጨባጭ የሆነ ጥቅም እንደማያገኝ ከተገነዘበ፣ ለቋንቋው ያለው አመለካከት ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቤተሰቡና የሚኖርበት ማህበረሰብ ለሚማረው ቋንቋ ያለው አመለካከት ጥሩ ካልሆነ፣ ይህ ሁኔታ ወደ ተማሪው በመጋባት ለቋንቋው ያለው አመለካከት ዝቅ ሊያደርገው ስለሚችልና ለቋንቋው ብዙ ትኩረት ስለማይሰጥ ስህተቶችን ይፈጽማል (Norish፣ 1992፣ 18)፡፡ እኚህ ሞሁር አክለው እንደሚገልጹት በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ችግሮችም የተማሪውን የመማር ፍላጎት በማዳከም በቋንቋ መማር ሂደቱ ላይ ስነ ልቦናዊ ጫና ሊያሳድሩ (ሊያደርሱ) ይችላሉ፡፡ የተማሪው መማሪያ መጻህፍ ሳቢና ማራኪ አለመሆን፣ መምህሩ በክፍል ውስጥ የሚከተለው የማስተማሪያ ስልት አሰልቺ መሆን፣ ከላይ የተጠቀሰውን የመማር ፍላጎት ማጣትን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ይህም ተማሪውን ወደ ስህተት ከሚገፋፉ ሁኔታዎች አንዱ በመሆኑ፣ ስነልቦናዊ ሁኔታ ከስህተት መከሰቻ ምንጮች እንደ አንዱ አድርገን እንወስደዋለን፡፡

በአጠቃላይ አንድን ለትምህርት የቀረበን ቋንቋ የሚማር ተማሪ ሀሳቡን በጽሑፍ ለመግለጽ ሲሞክር ከስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ስህተት ሊፈጽም እንደሚችል በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚስተዋለው የተነሳሽነት ማነስ፣ ተማሪው በታላሚው ቋንቋ የሚኖረው አመለካከት አሉታዊ መሆን፣ ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ እና በሁለተኛ ቋንቋ

ተማሪው መካከል በሚኖረው የባህል ግጭት ምክንያት በሚፈጠር ማህበረሰባዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች አለመጣጣም እና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

## 2.5 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

በዚህ ክፍል ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ፅሑፎች የሚቃኙበት ነው፡፡አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በተመለከተ በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ከእነዚህምጥናታዊ ጽሁፎች እመቤት (2008)፣ህይወት (2009) ፣ ደብሬ(1990)፣ምህረት (1998)፣ ተክሌ(1989) እንደሚከተለው ተቃኝተዋል፡፡

እመቤት በቀለ (2008) ‹‹በኢሉባቦር ዞን በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የሰዋሰሰው ትምህርት ይዘት ሲማሩ የሚስተዋልባቸው ተግዳሮት መፈተሽ›› በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

አድርገው የሚማሩ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ በሚማሩበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች ለይቶ በማውጣት መተንተን ነው፡፡ አጥኝዋ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ዓይነታዊ የአጠናን ዘዴ ተግብራለች፡፡ በዚህ ዓላማ መነሻነትም ለተማሪዎች የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ እና ለመምህራን የቀረበው ቃለ መጠይቅ እንደሚያመላክተው በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በርካታ ሰዋሰዋዊ ስህተቶችን ለመፈጸም የሚያስችሉ ምክንያቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የመማርማስተማር ድክመቶች እና የስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

ይህ ጥናትተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉበሚፈጽሟቸው ስህተቶች ላይ በማተኮሩና አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ማተኮሩ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በተጠኚ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ እና በቦታም የተለየ ነው፡፡ጥናቱ የተደረገው በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ግን አፋቸውን ከፍኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ላይ መሆኑ ነው፡፡

ህይወት ሎሃ (2009) ‹‹በወላይትኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የድርሰተት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህቶች ትንተና›› በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ዋና ዓላማው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚጋጥሟቸው ትምህርት ዓይነቶች ትንተና ላይ ያተኮረ ሲሆን አጥኚዋ ዓላማውን ከግብ ለማድረስም ዓይነታዊ የአጠናን ዘዴ ተግብራለች፡፡ በዚህ ዓላማ መነሻነትም ለተማሪዎች የቀረበው የድርሰት አፃፃፍ ፈተና ጽሑፍ መጠይቅ ለምሁራንም የቀረበ ቃለ መጠይቅ እንደሚያመለክተው ተማሪዎች ደርሰት ሲጽፉ ከሚያጋጥሟቸው ስህተቶች የቋንቋ አጠቃቀም እና የስርዓተተ ነጥብ አጠቃቀም የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ማተኮሩና አይነታዊ የአጠናን ዘዴ መተግበሩ ነው፡፡ ይህ ጥናት በጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የአፍመፍቻ ቋንቋ የጥናት ቦታ አመራረጥ የተሳታፊ ተማሪዎች ብዛት የተለየ ነው፡፡

ምህረት ሳዳሞ (1998) “በዋቻሞ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሀድይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው

ስህተቶች ትንተና" በሚል ርዕስ በሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸው በተማሪዎች ድርሰቶች ውስጥ የታዩ ስህተቶችን የቋንቋ አጠቃቅም ስህተቶች፣ የቋንቋ አወቃቅር ስህተቶች፣የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች በሚል ፈርጀዋቸዋል፡፡ በተደረገው ትንታኔ መሠረት ለስህተቶች መፈጠር በምክንያትነት የተዘረዘሩት የስህተት ምንጮችም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የውስጠ ቋንቁ ተጽእኖ፣ የመማርማስተማር ድክመቶች እና የስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ተጽእኖ ናቸው፡፡ይህ ጥናት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ስህተቶች ላይ በማተኮሩና አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ማተኮሩ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በተጠኚ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ እና በቦታም የተለየ ነው፡፡ጥናቱ የተደረገው በሀድይኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የዋቻሞ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ግን በካፋዞን በሚገኙ  አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ በፈቱ ተማሪዎች ላይ  ነው፡፡

ተክሌ አስፋው (1989) "በቡታጅራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በመስቃንኛ ቋንቋ የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች" በሚል ርዕስ ላይ ጥናታቸውን አካሂደዋል፡፡ በዚህ ጥናት በተማሪዎች ድርሰት የተከሰቱ ስህተቶች ተጠቃለው ሲቀርቡ፣ ለአንድ ጽንሰ -ሀሳብ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ቃላትን መጠቀም፣አንድን ቃል ለብዙ ጽንሰ-ሀሳብ መግለጫነት መጠቀም እና የመሰቃንኛውን ቃል እንደወረደ (እንዳለ) ወደ አማርኛ ተርጉሞ መጠቀም የሚሉ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በርካት ያሉ ሰዋስዋዊ ስህተቶች የተስተዋሉ መሆናቸውን ጥናቱ ያመለክታል፡፡ በውጤቱም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የማስተማር ዘዴ ድክመት እና የተማሪዎች የመማር ባህርይ ልዩነቶች ለተፈጸሙት ስህተትቶች መንስኤዎች እንዲሆኑ አመልክተዋል፡፡ይህ ጥናት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ስህተቶች ላይ በማተኮሩና አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ማተኮሩ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በተጠኚ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ እና በቦታም የተለየ ነው፡፡ጥናቱ የተደረገው በመስቃንኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የቡታጅራ ት/ቤት ላይ  ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ግን አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ በፈቱ የሶስት ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡

ሌላው ደብሬ ተሰማ ( 1990) "በኦሮሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ በተማሪዎች ተከሰቱ ተብለው የሰፈሩት የስህተት ዓይነቶች በሌሎች ጥናት ከተገለጹት ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በጥናቱም መሠረት የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ችግር መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ ለስህተቶቹ መከሰት ምክንያት ይሆናሉ ተብለው ከሰፈሩት ውስጥ ውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት፣ የመማር ማስተማር ዝንባሌ፣ የመማሪያ መጻህፍት ብቃት ማነስ፣ በቂ የሆነ ልምምድ አለመኖር እና የተሳሳተ የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤዎች መሆናቸውን በቅኝቱ ለማስተዋል ተችሏል፡፡ይህ ጥናት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ስህተቶች ላይ በማተኮሩና አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ማተኮሩ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በተጠኚ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ በክፍል ደረጃ እና በቦታም የተለየ ነው፡፡ጥናቱ የተደረገው በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ግን አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ በፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡

በአጠቃላይ የተቃኙት ሥራዎች ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚሳሳቷቸው የስህተቶቻቸው ዓይነቶች ምን ምን እንደሆኑ፣እንዲሁም የስህተቶቹን ምንጮች ለመለየት ጠቃሚ የመነሻ ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡ ይህ ጥናት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ስህተቶች እንዲሁም በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ በማተኮሩ ከላይ ከተጠቀሱት ቀደምት ጥናቶች ጋር ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት በተጠኝዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣በጥናቱ የቦታ አመራረጥ፣ በትኩረቱና በተጠኝዎች ከሌሎች ይለያል፡፡ በአጠቃላይ ጥናቱ በከፋ ዞን በሚገኙ በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የከፍኛ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የድርሰት ስህተት እና መንስኤዎቻቸውን በመመርመር የመፍትሄ ሀሳብ ለማቅረብ ተሞክሯል፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ክፍል ጥናቱ የሚከተለውን ጥናት አይነት፣የጥናቱ አካባይ፣ የመረጃመሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የናሙና አመራረጥዘዴና የመረጃ አተናተን ዘዴለመግለጽ ይሞከራል፡፡

### 3.1 የጥናቱ ዓይነት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በካፋዞን ባሉ በተመረጡ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በከፍኛ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ሰዋሰዋዊ ስህተቶችን ዓይነትና የስህተቶችን ምንጭ ተንትኖ ለማሳየትና ከውጤቱ በመነሳት የበኩሉን የመፍትሄ ሀሳብ ለመሰንዘር ነው፡፡ ጥናቱ

አይነታዊ እና መጠናዊ ምርምርን በማጣመር ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በጽሑፋቸው ላይ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች አይነት በትረካዊ ገለፃ እየተብራሩ የሚተነተኑ በመሆናቸው ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የሚከተል ሲሆን፡ በተማሪዎቹ ጽሑፎች ላይ የሚታዩት የስህተቶቹን ብዛት እና የድግግሞሽ መጠን ለመለየት መጠናዊ የምርምር ሂደትን ይከተላል፡፡

## 3.2 የጥናቱ አካላይ

ይህጥናት በደቡብ ክልል በካፋዞን ባሉ ጊምቦ፤ግራዝማች ጳውሎስ እናአውራዳ በተሰኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥየሚገኙ የከፍኛ አፈ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚያጠቃልል ነው፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

### 3.3.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጡት በካፋዞን ከሚገኙ ሶስት ወረዳዎች የሚገኙ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቶቹም አውራዳ ጊምቦ እና ግራዝማችጳውሎስ የተሰኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችናቸው፡፡ት/ቤቶቹ በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ የተመረጡ ሲሆኑትምህርት ቤቶቹን ለመምረጥ መስፈርት ከሆነው ነገር አንዱከተለያዩ ሶስት ወረዳዎች የሚወሰዱ ናሙናዎች መረጃዎችን በጥልቀትለማግኘት እና በሶስቱም ትምህርት ቤቶች ያሉ የከፍኛ አፈ-ፈት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በብዛት በመገኛ ቦታቸው ማግኘት መቻሉ ነው፡፡

### 3.3.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደውከመማር ማስተማር ልምድ በመነሳት የሚፈለገውን መረጃ በስፋት ለማግኘት እና ጥናቱን በጥልቀት ለማካሄድ የመረጃ ምንጭ ለመሆን ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው በ2011ዓ.ም በትምህርት ገበታ ከሚገኙ ከጊምቦ ት/ቤት በ4 መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 95 ወንድ እና 135 ሴት በድምሩ230 ተማሪዎች ተገኝተዋል፡፡ከአውራዳ ት/ቤት በ9መማሪያ ክፍሎች ውስጥ 288 ወንድ እና325 ሴትበድምሩ 613 ተማሪዎች ተገኝተዋል፡፡ከግራዝማችጳውሎስ ት/ቤት በ8

መማሪያ ክፍሎች 256ወንድ እና 271ሴትበድምሩ527 ተማሪዎች የተገኙ ሲሆን በድምሩ በሶስቱ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ 21 የዘጠነኛ ክፍል መማሪያክፍሎች ከሚገኙ639ወንድና 731ሴት ተማሪዎች መካከል በሶስቱም ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ 420ወንድና500ሴት ተማሪዎች በድምሩ 920 የከፍኛ ተማሪዎች ተለይተዋል፡፡ይሁንእንጂ እነዚህን ተማሪዎች በአጠቃላይ ተጠኚ ማድረግ ከአቅም በላይ በመሆኑ ስማቸውን በቅደም ተከተል በመመዝገብከ920 ተጠኚ ተማሪዎች መካከል ከየት/ቤቱ15% ተማሪበቀላልእጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ እጣ በማውጣት ከጊምቦ 9 ወንድና 15 ሴት ድምር 23 ከግራዝማች 24 ወንድና 23 ሴት ድምር 47 አውራዳ 30 ወንድና 37 ሴትድምር 67 ባጠቃላይ 63 ወንድና 75 ሴት በድምሩ 138 በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ በከፍኛ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ወካይ ተማሪዎችን በናሙናነት በመምረጥ የተካሄደ ነው፡፡

### 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ከላይ የተጠቀሰውን የጥናቱን ዋና ዓላማ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለጥናቱ በዋናነት ጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የስህተት አይነት ለይቶ ሊያሳዩ የሚችሉ በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶችና ለተማሪዎች የቀረቡ የጽሁፍ መጠይቆች ናቸው፡፡

### 3.4.1 በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች

የጥናቱን ዋና ዓላማ ለማሳካት በዋናነት የመረጃ መሰብሰቢያ በመሆን ያገለገለው ተማሪዎች የሚጽፉት የአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ነው፡፡ አጥኝዋ ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ የተመረጠችበት ምክንያት ጥናቱ በከፍኛ አፈፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትንተና የሚያተኩርበመሆኑሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶችን በዋናነት ለመልቀም(ለመለየት) የሚያስችል መረጃ መሰብሰቢያ በመሆኑ ነው፡፡ጥናቱን ለማካሄድ በናሙናነት በተመረጡ በ2011 ዓ.ም በካፋ ዞንባሉ በተተኳሪ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪ ተማሪዎች ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመተንተን በጥናቱ የተመረጡ ተማሪዎች ድርሰት በክፍል ውስጥ እንዲጽፉ

ተደርጓል፡፡ድርሰቶችን በተደጋጋሚ ማስጻፍ ያስፈለገበት ምክንያት የስህተቶቹን ተደጋጋሚነት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ነው፡፡

ድርሰቶች በክፍል ውስጥ እንዲጻፉ የተደረገበት ምክንያት ከክፍል ውጭ የሚጻፉ ድርሰቶች የሌላ ሰው እጅ ሊኖርባቸው ስለሚችል ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ከክፍል ውጭ በቤታቸው የሚጽፏቸው ድርሰቶች የስህተት መጠናቸው ሊቀንሱና ትክክለኛ ችግሮቻቸውን ላያሳዩ ይችላሉ ከሚል ሀሳብ በመነሳት ነው፡፡ ይህን በተመለከተ kroll (1990: 50) በጥናት ሥራቸው ላይ እንዳረጋገጡት፣ ጊዜ ተሰጥቶት ከክፍል ውጭ የተጻፈ ድርሰት የስህተት መጠኑ ከክፍል ውሰጥ ከተጻፈው ድርሰት ቀንሶ ተገኝቷል በማለት የገለጹትን ሀሳብ መነሻ በማድረግ ነው፡፡

### 3.4.1.1 የርዕሶች አመራረጥ

ተማሪዎቹ ድርሰቱን እንዲጽፉ በአጥኚዋ ተዘጋጅተው እና በሌሎች የአማርኛ መምህራን ተገምግመው የቀረቡ፤የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ ባህላዊ እና አከባቢያዊ ዳራ መሰረት ያደረጉአስር አማራጭ ርዕሶች ቀርበውላቸዋል፡፡

### 3.4.1.2 የድርሰት አፃፃፍ መመሪያ

በአማራጭነት ከተሰጧቸው ርዕሶች መካከል ብዙ ያስጽፈኛል ብለው በሚያምኑበትን አንዱን ርዕስ ብቻ ከመቶ እስከ መቶ ሃምሳ በሚደርሱ ቃላት እንዲጽፉ፣ ስለሚፅፏቸው ድርሰቶች በተሰጧቸው የመፃፊያ ወረቀቶች ላይ እንዴት ማስፈር እንዳለባቸው፣ የሚጽፉትም ጽሁፍ የድርሰት አፃፃፍ ስርዓትን የተከተለና ተያያዥነት ያላቸው አንቀፆች እንዲሆኑ፣ የሚያስገነዝብ መመሪያ ከተሰጣቸው በኋላ ርዕሶችም በተጠኚ ተማሪዎች ቁጥር ልክ ተባዝቶ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚያም የድርሰቱን አጻጻፍ በተመለከተ ገለጻ ተደርጓላቸዋል፡፡ ድርሰቶቹን ነፃ የአጻጻፍ ዘዴን (Free writing System) ተከትለው በሁለት ዙሮች በክፍል ውስጥ እንዲጽፉ ተደርገዋል፡፡ ድርሰቱን አንድ ጊዜ ብቻ አስጽፎ የታዩትን ስህተቶች የተመሪዎች ስህተቶች አድርጎ መቀበሉ የሚያስቸግር በመሆኑ ድርሰት አንድ ከተፃፈ ከአንድ ሳምንት በኋላ ሁለተኛ ዙር እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡

በመጀመሪያ ዙር 138 ድርሰቶች በሁለተኛ ዙር 138 ድርሰቶች በድምሩ 276 ድርሰቶች በክፍል ውስጥ ተጽፈዋል፡፡ድርሰቶችን ሁለት ጊዜ ማስጻፍ ያስፈለገበት ምክንያት የስህተቶቹን ተደጋጋሚነት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ነው፡፡ ምክንያቱም የስህተት ትንተና በአንድ ድርሰት ወይም በተወሰነ የክንውን ጊዜ ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ ጽሑፎች አማካኝነት ሊተነተን ይገባል (Omaggio Hadley፣ 1993፤ Widdowson፣ 1990)፡፡ ድርሰቶችን የማስጻፍ ሂደት የተከናወነው በተመረጡ ት/ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በአጥኚዋ ነው፡፡

### 3.4.2 ለጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

ይህ የመረጃ ማሰባሰቢያ ስልት የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በሁለት ዙር ከጻፏቸው ድርሰቶች በተጨማሪ ለጥናቱ የሚያስልገውን መረጃ በጽሁፍ እንዲሰጡ በማድረግ መረጃ የማሰባሰብ ስልት ነው፡፡ ዋና ዓላማውም ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ለሚፈጠረው ስህተት ምክንያቱ ምን እንደሆነ በጽሁፍ በመግለጽ የሰጡትን መረጃ ከድርሰቶቻቸው ከተገኘው ጋር በማስተያየት የመረጃውን ትክክለኛነት በጎናዊ ፍተሻ ለማረጋገጥ እንዲያስችል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው በስህተት ትንተና ዙሪያ ጥናት ባካሄዱ እነ (Brown 1994፣ Littlewood 1986፣ Norrish 1993፣ Dulay1982) ጠቅሰው እንደገለፁት የስህተት ምንጮች ተብለው የተጠቀሱትን የመማር ማስተማር ችግር ፣ የስነ-ልቦና ችግር እና የውስጠቋንቋተጽእኖ የተባሉት ችግሮች ምን ያክል በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ተጽእኖ እያሳደሩ እንዳሉ ለመፈተሽ ይረዳል፡፡ ስለሆነም አጥኚዋ የጥናቱ ተተኳሪ 138 ተማሪዎችን አምስት ዝግና አራት ክፍት ጥያቄዎችን  በድምሩ ዘጠኝየጽሁፍ መጠይቆችን አዘጋጅታ በማስሞላት  የተሰበሰበውንም መረጃ  በቅደም ተከተሉ መሰረት በምዕራፍ አራት በዝርዝር ተተንትኗል፡፡

### 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ጥናቱ በካፋዞን ባሉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በከፍኛ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጥሯቸውን ሰዋሰዋዊ ስህተቶችን ዓይነትና የስህተቶችን ምንጭ ለመመርመርየስህተት ትንተናን ለማድረግ ከሚጠቅሙት ሁለት አበይት ዘዴዎች Norish (1992፣80) ውስጥ  አስቀድሞ

በተከፈለ ምድብ ውስጥ የተማሪዎችን ስህተቶች መመደብን (making pre categories and coding) ተግባራዊ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት በተጠኚ ተማሪዎች ድርሰቶች ውስጥ የተገኙት ስህተቶች በየስህተት አይነቶቹ የተከፋፈሉት ወይም በየምድባቸው የተቀመጡት ቀደም ሲል በተመረጡና በታወቁ የስህተት አይነቶች ምድብ ስር መሆናቸውን በሌላ አገላለጽ ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የአከፋፈል ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

በድርሰቱ ውስጥ ስህተቶቹን በአይነት ለመመደብ ስህተቶቹንም ለመቁጠርና ድግግሞሻቸውንም ለማወቅ የNorish (1992፣103 -104) የስህተት አተናተንን ስልት በመጠቀም ለጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎች(ከተማሪዎች ድርሰት) በዓይነታዊ እና መጠናዊ ድብልቅ የምርምር መረጃ አተናተን ዘዴ ተተንትኗል፡፡(አባሪ ሁለትን ይመልከቱ)

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት አላማ ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚታዩትን የተለያዩ ስህተቶች መተንተን ሲሆን ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድረሰቶች ውስጥ የተፈጸሙት የስህተት አይነቶች የትኞቹ ናቸው? የስህተቶቹስ ብዛት ምን ያህል ነው? ድግግሞሻቸውስ ምን ያህል ነው? የሚለውንመሰረታዊ የጥናት ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉ ትንተናዎች የተደረገበት ነው:: በትንተናው ሂደት ተጠኚ ተማሪዎች በጻፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ የፈፀሟቸው ስህተቶች በአይነት በአይነታቸው የተመደቡ ሲሆን የስህተት ብዛታቸው መቶኛ፣ አማካይ የስህተተ

ብዛት፣ አማካይ እና የስህተት ድግግሞሽ ተተንትኗል:: የስህተት ምንጮች ምን ምንድ ናቸው? ለሚሉ መሰረታዊ የጥናት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠትም ተማሪዎች ከጻፏቸው ድርሰቶች የተገኙ መረጃዎች በዚህ ምዕራፍ ተተንትነዋል::

**4.1. በድርሰቶች ውስጥ የታዩ አጠቃላይ የስህተቶች ብዛት**

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዚህ ንዑስ ክፍል የተለያዩ ስህተቶች በዝርዝር የሚታዩበት በመሆኑ፣ ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች መሰረት አጠቃላይ የሆነው የስህተት ብዛት፣ የቃላት ብዛትና የስህተት ድግግሞሽ በተከታዩ ሁኔታ ቀርቧል::

**ሰንጠረዥ 1:-በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች ብዛት፣ የስህተቶችአማካይ እና የ ስህተት ድግግሞሽ መጠን የሚያሳይሰንጠረዥ**

| የድርሰቱ ፈተና አይነት | የድርሰቶች ብዛት | ድርሰቶች የተጻፉበት የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድርሰት አንድ | 138 | 11392 | 82.55 | 5275 | 53.45 | 38.23 | 46.31 |
| ድርሰት ሁለት | 138 | 12077 | 87.52 | 4594 | 46.55 | 33.29 | 38.04 |
| ድርሰት አንድ እና ሁለት | 276 | 23469 | 85.04 | 9869 | 100 | 35.78 | 42.06 |

ከሰንጠረዥ አንድ መረዳት እንደሚቻለው ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ድርሰቶች በሁለት የተለያዩ ዙሮች ተጽፈዋል:: ስህተቶቹም የተቆጠሩት ተጠኚ ተማሪዎች ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ነው:: እነዚህ ድርሰቶች የተጻፉበት አጠቃላይ የቃላት ብዛት ሲቆጠር 23469 ሲሆን ይህንን አጠቃላይ የቃላት ብዛት በመውሰድ እያንዳንዱ ድርሰት የተጻፈበት አማካይ የቃላት ብዛት 85.04 መሆኑ ከቀረበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል:: በሁለቱም ደርሰቶች 9869 የተለያዩ ስህተቶች ሲፈጽሙ፣ በእያንዳንዱ ድርሰት ወስጥ የተገኘው ወይም የተቆጠረው አማካይ የስህተት ብዛት 35.78 ነው:: ይህ ማለት በ85.04 ቃላት ውስጥ 35.78 የተለያዩ ስህተቶች መገኘታቸውን ያመለክታል:: በ85.04 አማካይ ቃላት ውስጥ የተፈጸመው የስህተት ድግግሞሽ ብዛት ደግሞ 42.06 ነው::

**4.2. በድርሰቶች ውስጥ የታዩ ዋና ዋና የስህተት አይነቶች**

በምዕራፍ ሶስት የድርሰት አተናተንን በተመለከተ እንደተገለጸው ስህተቶች በአይነት የተለዩትና የተመደቡት በቅድመ ምድብ የስህተት አይነት ምድቦች አማካይነት ነው:: በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የተተኮረባቸው የሰህተት አይነቶች የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የሰርአተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ እና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ናቸው:: በእነዚህ የስህተት አይነት ምድቦች ውስጥ የተቆጠረ የስህተት ብዛት፣ መቶኛ፣ አማካይ የስህተት ብዛት፣ አማካይ እና የስህተት ድግግሞሽ እንደሚከተለው በቅድም ተከተል ለመዳሰስ ተሞክሯል:: ዝርዝሩን በቀጣዩ ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል::

**ሰንጠረዥ 2:-በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ በየስህተት አይነት ምድቡ የተፈጸሙ ስህተቶች ብዛት፣ የስህተት ብዛት በመቶኛ፣ አማካይ ስህተት እና የስህተት ድግግሞሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስህተቶቹ አይነት | የስህተቶች ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተቶች ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተቶች ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
| የቋንቋ አጠቃቀም | 2271 | 43.07 | 16.46 | 19.94 | 2116 | 46.06 | 15.34 | 17.52 | 4387 | 44.45 | 15.89 | 18.69 |
| የቋንቋ አወቃቀር | 1372 | 26.01 | 9.94 | 12.04 | 1199 | 26.10 | 8.69 | 9.93 | 2571 | 26.06 | 9.32 | 10.95 |
| የሰርዓተ ነጥብ አጠቃቀም | 1243 | 23.56 | 9.01 | 10.91 | 932 | 20.28 | 6.76 | 7.72 | 2175 | 22.04 | 7.88 | 9.27 |
| የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ | 126 | 5.05 | 1.93 | 2.34 | 218 | 4.75 | 1.58 | 1.81 | 485 | 4.91 | 1.76 | 2.07 |
| መለየት ያልተቻሉ | 122 | 2.31 | 0.88 | 1.07 | 129 | 2.81 | 0.93 | 1.07 | 251 | 2.54 | 0.91 | 1.07 |
| ድምር | 5275 | 100 | 38.25 | 46.30 | 4594 | 100 | 33.30 | 33.05 | 9869 | 100 | 35.76 | 42.05 |

ከፍ ሲል ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች በሁለቱም ዙሮች በፃፏቸው ድረሰቶች ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ስህተቶች የተፈፀሙት በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት አይነት ምድብ ውስጥ ነው:: በሁሉም የስህተት አይነት ምድቦች ከተቆጠሩት 9869 ስህተቶች መካከል የተፈጸመው የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ብዛት 4387 (44.45%) ነው:: የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት አማካይ የስህተት ብዛት 15.89 ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 18.69 መሆኑን መረጃው ያመለክታል:: ስለሆነም በተገኙት መረጃዎች መሰረት የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ከፍተኛውን ቦታ ይዟል::

ከቋንቋ አጠቃቀም ቀጥሎ (በሁለተኛ ደረጃ) በርካታ ቁጥር ያላቸው ስህተቶች የተቆጠሩት በቋንቋ አወቃቀር (የአረፍተ ነገር አወቃቀር) የስህተት ምድብ ውስጥ ነው:: በሁለቱም ዙሮች ተማሪዎች በፃፏቸው የደርሰት መልመጃዎች ከተቆጠሩት 9869 አጠቃላይ ስህተቶች መካከል 2571 (26.06%) ያህል ስህተቶች የተገኙበት ሲሆን፣ አማካይ የስህተት ብዛት 9.32 ነው:: አማካይ የስህተት ድግግሞሽ ደገሞ 10.95 ሊሆን ችሏል::

በሶስተኛ ደረጃ ከፍተኛ ስህተት የተመዘገበው በስርዓት ነጥቦች አጠቃቀም ዙሪያ ነው:: ተማሪዎቹ በሁለት ዙሮች ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ከስርዓት ነጥብ አጠቃቀም ጉድለት የተነሳ በርካታ ስህተቶች እንደተፈጸሙ ከቀረበው መረጃ መመልከት ይቻላል:: በአጠቃላይ በስህተትነት ከተቆጠሩት 9869 ስህተቶች መካል 2175 (22.04%) ያህሉ በዚሁ የስርዓት ነጥብ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ውስጥ የሚጠቀስ ነው:: አማካይ የስህተት ብዛት 7.88 ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 9.27 ሆኗል::

አራተኛውን ደረጃ የያዘው የስህተት ምድብ የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተት ሲሆን ብዛቱም 485 (4.91%) ያህሉን ሊሸፍን ችሏል:: አማካይ የስህተት ብዛቱም 1.76 ነው:: በመቶ ቃላት ውስጥ የተገኘው አማካይ የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 2.07 ነው፡፡

በመጨረሻ ደረጃ የተቆጠረው የስህተት አይነት ምድብ መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ተብለው የተሰየሙትን የሚያካትት ነው:: የስህተት ብዛቱ 251 (2.54%)

ሲሆን፣ አማካይ የስህተት ብዛቱ ደግሞ 0.91 ነው፡፡ የስህተት ድግግሞሹም 1.07 ሆኗል፡፡ ለእዚህም ምክንያት የመጨረሻውን ደረጃ ሊይዝ ችሏል፡፡

### 4.2.1. በቋንቋ አጠቃቀም (ስዋስው) የታዩ ስህተቶች

የአንድን ቋንቋ የአጠቃቀም ስርዓት ጠብቆ ሃሳብን ማስተላለፍ የፅሁፍ ቋንቋ መሰረታዊ ባህርይ መሆኑን በርካታ የቋንቋ ምሁራን ይጠቁማሉ፡፡ ከመደበኛ የጽህፈት ስርዓት ውጪ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ሀሳብን በተገቢው መልኩ ለተደራሲያን ለማስተላለፍ የሚገታ ብቻ ሳይሆን የመግባባት ሂደትንም የሚያደናቅፍ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ መግባባትን ሊደናቅፉ (ሊያግዱ) ይችላሉ ተብለው የተገኙ ዋና ዋና የስህተት አይነቶችና በእርነሱ ስር ያሉ ንዑሳን ስህተቶች ብዛት በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

## ሰንጠረዥ 3:- በቋንቋ አጠቃቀም(ስዋስው) ስር የታዩ ዝርዝር ስህተቶች

| | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስህተቶቹ አይነት | የስህተቶች ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተቶች ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተቶች ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
| የቃላት አመራረጥ | 665 | 12.61 | 4.82 | 5.84 | 590 | 12.84 | 4.28 | 20.47 | 1255 | 12.72 | 4.55 | 5.35 |
| ድግግሞሽ | 238 | 4.51 | 1.72 | 2.09 | 204 | 4.44 | 0.48 | 59.20 | 442 | 4.48 | 1.60 | 1.88 |
| ግድፈት | 167 | 3.17 | 1.21 | 1.47 | 121 | 2.63 | 0.88 | 99.81 | 288 | 2.92 | 1.04 | 1.23 |
| ለቦታው የማያስፈልጉ ቃላት | 147 | 2.75 | 1.07 | 1.29 | 158 | 3.44 | 1.14 | 76.44 | 305 | 3.09 | 1.11 | 1.30 |
| ኢ-መደበኛ ቃላት | 118 | 2.24 | 0.86 | 1.04 | 105 | 2.29 | 0.76 | 115.02 | 223 | 2.26 | 0.81 | 0.95 |
| የፊደላት አጻጻፍ | 936 | 17.74 | 6.78 | 8.22 | 938 | 20.42 | 6.80 | 12.88 | 1874 | 18.99 | 6.79 | 7.99 |
| ድምር | 2271 | 43.02 | 16.46 | 19.95 | 2116 | 46.06 | 14.34 | 5.71 | 4387 | 44.45 | 15.90 | 18.70 |

ከፍ ሲል ከቀረበው ሰንጠረዥ መገንዘብ እንደሚቻለው በዋናው የስህተት አይነት ምድብ (በቋንቋ አጠቃቀም) ስር ከተፈጸሙት የስህተት አይነቶች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው የፊደላት አጻጻፍ ስህተት ነው:: የጥናቱ ተተኳሪ የካፊኛ አፊ-ፊት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ በፊደላት አጻጻፍ የሳድስናሳልስ መለዋወጥ የመሳሰሉት ችግሮች ይታያሉ፡፡ በዚህም ዋና የስህተት አይነት ምድብ ውስጥ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ አላስፈላጊ ድግግሞሽ፣ ግድፈት፣ ለቦታው የማያስፈልጉ ቃላት እና የኢ-መደበኛ ቃላትና ሐረጋት አጠቃቀም ስህተቶች በቅደም ተከተል ቀጣዩቹን ደረጃ ይዘው ይገኛሉ::

#### 4.2.1.1. በፊደላት አጻጻፍ ላይ የታዩ ስህተቶች

ሀሳብን በጽሁፍ ለማስተላለፍ ሲታሰብ የቋንቋው ድምጸ ልሳናት የሚወከሉትን ፊደላት በትክክል ለይቶ ማወቅና መጠቀም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: ይህንን አስመልክተው Byrene (1988፣1) እንደሚሉት የቋንቋው ተናጋሪዎች ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉ የንግግር ድምጾችን የሚወክሉ ሆሄያት (ፊደላት) ስርዓት ባለው መልኩ ተሰድረው (ተገጣጥመው) ቃላትን እንደሚመሰርቱና ሀሳብን በግልጽ ሊያስተላልፉ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ:: ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መገንዘብ የሚቻለው ተገቢ የሆኑ ፊደላት በተገቢ ቦታቸው መጠቀም የጽሁፍ ቋንቋ አቢይ ባህርይ መሆኑን ነው:: ስለዚህ የፊዳላትን ቅርጽ ለይቶ አለማወቅና በተገቢ ቦታቸው አለመጠቀም ሊተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ሊቀይረው ከመቻሉም  በላይ ቃላቱ ትርጉም አልባ የፊደላት ስብስብ ብቻ እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል::

ተጠኚ ተማሪዎች በጻፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ ቃላቱ የተገነቡባቸውን ድምፀ ልሳናት የሚወክሉ ፊደላትን አስተካክሎ ካለመጻፍ የተነሳ በረካታ ስህተቶች የተፈጸሙ መሆናቸውን ከተገኙት መረጃዎች ለማየት ተችሏል::

ከላይ በሰንጠረዥ በቀረበው መረጃ መሰረት የሆሄያትን ቅርጽ በትክክል ካለመለየት (ካለማወቅ) የተነሳ የተፈፀሙ ስህተቶች ከፍተኛውን ደረጃ ይዘው ይገኛሉ:: ተማሪዎች በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በአጠቃላይ ከተፈፀሙት 9869 (ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ስልሳ ዘጠኝ) ስህተቶች መካከል 1874 ያህሉን የሸፈነው የፊደላት አጻጻፍና አጠቃቀም ስህተት ነው:: ይህም በመቶኛ ሰላሳ 18.99 ሲሆን

አማካይ የስህተት ብዛቱም 6.79 ነው:: አማካይ የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 7.99 ሲሆን፣ የትክክለኛነት ተዛማጅነቱም 12.52 ነው:: ይህ ማለት ደግሞ በየ 12.52 ቃላት ወይም ሀረጋት ወስጥ አንድ የሆሄያት አጻጻፍ ስህተት ተፈጽሟል ማለት ነው:: ተማሪዎቹ ከጻፏቸው ድርሰቶች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የተለያዩ ድርሰቶችን በሚጽፉበት ጊዜ ግዕዙን ከሃምስ ፊደል ሳልሱን ከሳድሱ ፊደል ጋር እያደባለቁ እንደሚጠቀሙባቸው ነው:: በዚህ መልክ ከተፈፀሙት ስህተቶች መካከል ለምሳሌ

- የሰው ልጅ ደን ከለለ ልኖር አይችልም ::
- ለበዓል በተሰቦቻቸው ዘንድ ይሜጣሉ:
- ወደፍት የካፋ ፕሬዝዳንት  ሆናሎ
- ምን አሌቤት ወንድሜ ጫማ ብገዛ::
- እንደኔ ከሆኔ መጀመሪያ ትሚርት መጨረስ ፊልጋሎ::
- እያንዳንዱ ዜጋ በእንክብካብእንድጠብቅእንድይዝማስተማሪ ያስፈልገናል::
- … ስለዝህየተማሪናያልተማሬምብሆን ወጣት ሸማግለ ሳይል… ለልማት እንነሳ::

ከፍ ሲል በዝርዝር ከቀረቡት አስረጅዎች መገንዘብ የሚቻለው የቋንቋው ድምጾች የሚወከሉትን ሆሄያት በትክክል ለይቶ አለመጻፍ በተማሪዎች ድርሰቶች ውስጥ በሰፊው የተስተዋሉ ችግሮች ናቸው:: ተማሪዎቹ የቋንቋውን ድምጾች የሚወክሉ ፊደላትን በትክክል መጻፍ አለመቻል በጽሁፍ አማካይነት ሀሳብን ለማስተላለፍ የሚደረገውን ሙከራ ያሰናክለዋል:: በዚህም የተግባቦቱ ሂደት ሊደናቀፍ ይችላል:: በቀረቡትም ምሳሌዎች ውስጥ ተመሳሳይ ስህተቶች ተስተውለዋል::በዚህም ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የፊደላት አጻጻፍና አጠቃቀም ወጥነት የሌለው እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል:: በአጠቃላይ ሲታይ ተጠኚ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋን ፊደላት ቅርጽ በትክክል ለይቶ የመጻፍ ችግር ጎልቶ ይታይባቸዋል:: በተለይም ግዕዙን ከሀምሱ፣ ሀምሱን ከግዕዙ፣ ሳድሱን ከሳልሱ፣

ሳልሱን ደግሞ ከሳድሱ ጋር እያምታቱ እንደሚጠቀሙ የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል:: ይህ ስህተት የተከሰተው በአፍ መፍቻ ቋንቋ አሉታዊ ሽግግር ሳይሆን እንደማይቀር ተገምቷል:: የፊደላት ለውጡ የሚከተለውን ይመስላል::

| የተጻፈው ቃል | ለመጻፍ የተፈለገው ቃል | ንበት | ለውጥ |
|---|---|---|---|
| አሌቤት | አለበት | አልልአብኧት | ኧ ⟶ ኤ |
| ወደፍት | ወደፊት | ውእድእፍኢት | ኢ ⟶ እ |
| ብገዛ | ቢገዛ | ብኢግግኧዝአ | እ ⟶ ኢ |

በዚህ ምሳሌ የታየው በቃል መጨረሻ ላይ ያለውን አናባቢ (ኧ) ድምጽ በአናባቢ (ኤ) ድምጽ መለወጥ ነው:: አንዱን በሌላው የመለወጥ ሂደት በ (ኧ) እና በ (ኤ) መካከል ብቻ የተከሰተ ሳይሆን በሌሎችም አናባቢ ደምፆች ላይ ታይቷል:: ለምሳሌ ያህል ከላይ እንደተመለከተው (ኢ)ን በ (እ) የመተካት ሁኔታ በሰፊው ተስተውሏል::

ከፍ ሲል ከቀረቡት አስረጂዎች መመልከት እንደሚቻለው በከፍኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተጠኝ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የ (ኧ) እና የ(እ) አናባቢዎች የአጠቃቀም ስህተቶች ያሉባቸው መሆናቸውን ነው:: ስለሆነም እነዚህ አናባቢ ድምፆች በሌሎች አናባቢዎች ተክተው ሲጠቀሙ ተስተውለዋል:: በከፍኛ ቋንቋ ውስጥ (ኧ) እና (እ) አናባቢዎች የሉም :: ስለሆነም በቋንቋው ውስጥ የሌሉትን አናባቢ ድምፆች በተለያዩ ድምፆች በመተካት ስህተት ሲፈፅሙ ይስተዋላሉ:: (ኧ) በሚገባበት ቦታ (ኤ)ን ሲጠቀሙ ታይተዋል:: ስህተቶችም በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ የተነሳ በተሳሳተ መንገድ ሌላውን አናባቢ ቀይሮ ለመጠቀም ሲሞከር መሆኑን ለመገመት ተችሏል::

### 4.2.1.2. በቃላት አመራረጥ ላይ የታዩ ስህተቶች

እንደሚታወቀው ቃላት የሀሳብ ማስተላለፊያ መሳሪያዎች በመሆናቸው በአረፍተ ነገር ውስጥ ተገቢ ቃላትን በተገቢ ቦታ መጠቀም አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም:: ይህንን በተመለከተ Raimes (1991፣7) እንደሚያስረዱት አንድ ፀሐፊ የቋንቋውን ቃላት በተገቢው ቦታ ካልተጠቀመ ሊተላለፍ የተፈለገው ሀሳብ

ተድበስብሶ ሊቀር ይችላል:: ምክንያቱም አንባቢው በሂደት የሚገጥመውን ግልጽ ያልሆነ ሃሳብ ከፀሀፊው ጠይቆ ምላሽ ሊያገኝ አይችልም::

ከላይ በሰንጠረዥ ሶስት ላይ ከሰፈረው መረጃ መገንዘብ የተቻለው ተጠኚ ተማሪዎች በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ትክክለኛና ተገቢ ቃላትን ባለመጠቀማቸው የተነሳ የተለያዩ ስህተቶች መፈጸማቸውን ነው:: ተማሪዎቹ በጻፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ በአጠቃላይ ከተፈጸሙት 9869 ስህተቶች መካከል 1255 ያህሉ በቃላት አመራረጥ ላይ የታዩ ስህተቶች ናቸው:: ስህተቱ በመቶኛ ሲሰላ 12.72 ሲሆን አማካይ የስህተት ብዛት 4.55 ሊሆን ችሏል:: አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 5.35 መሆኑ ተረጋግጧል::

ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በቃላት አመራረጥ ሂደት የተፈጸሙ ስህተቶች አብዛኞቹ ተገቢ ቃላትን ባለመጠቀም፣ በአማርኛ ቋንቋ መድበለ ቃላት እውቅና ያላገኙ አህጽሮተ ቃላትን በመጠቀም እና ቃላትን በተሳሳተ መንገድ በመጠቀም የተፈጸሙ ናቸው:: እያንዳንዳቸውን በሚከተለው መልኩ ለመቃኘት ተሞክሯል::

### 1. ተገቢ ቃላትን ካለመጠቀም የተነሳ የተፈጸሙ ስህተቶች

ተማሪዎቹ ሀሳባቸውን በቀጥታ ለማስተላለፍ የሚያስችሏቸውን ተገቢና ትክክለኛ ቃላትን ካለመጠቀም የተነሳ የተለያዩ ስህተቶችን ፈጽመዋል:: ይህም ሀሳባቸውን በሌላ ቃል ወይም ሐረግ ለማብራራት ሲሞክሩ ከአረፍተ ነገሩ አውድ ጋር የማይዛመድ ቃል በመጠቀማቸው የተነሳ የተፈጸሙ ስህተቶች በደርሰቶቻቸው ላይ በስፋት ተስተውለዋል:: የሚከተሉትን ምሳሌዎች በናሙናነት ወስዶ መመልከት ይቻላል::

- ደን የተለያየ <u>ጠቀሜታዎችን</u> ለማግኘት በጣም ያስፈልጋል::
- ከቤተሰብ ርቆ መኖር ብዙ <u>እውቀቶችና ለውጦች</u> ያሳያል::
- በካፋ ቆሎ ለብዙ ነገር <u>ጥቅም አለው</u>::

- እኔም እንደሌሎች ከራስ በመትረፍ ወላጆቼንና ዘመዶቼን በከፍተኛ ደረጃ አየዋለሁ::

ከላይ በናሙናነት የተዘረዘሩትን አረፍተ ነገሮች ስንመለከት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቀጥታ ለመግለፅ የሚያስችሉ ቃላትን ለመጠቀም ካለመቻላቸው የተነሳ የተፈፀሙ ስህተቶች ናቸው:: በመጀመሪያው አረፍተ ነገር ጠቀሜታዎችን የሚለው አገላለፅ ጥቅም በሚለው ቃል ቢተካ የተሻለ ይሆን ነበር:: በተመሳሳይ ሁኔታ በሁለተኛው አረፍተ ነገር ውስጥ "እውቀቶችና ለውጦች" የሚሉትን ቃላት "ውጣ ውረዶች" በሚሉት ቃላት ተክቶ መጠቀም ቢቻል የተሻለ ይሆን ነበር:: ምክንያቱም ከቤተሰብ ርቆ መኖር ብዙ እውቀቶችንና ለውጦችን ያስገኛል ብሎ መደምደም የሚቻል ካለመሆኑም በላይ "እወቀት" በአብዥ ምዕላድ የሚገለጽ ቃል አይደለም:: የአረፍተ ነገሩን ሃሳብም የተድበሰበሰ ያደርጉታል:: በሶስተኛው አረፍተ ነገር "ጥቅም አለው" ተብሎ የተገለጸውን "ይጠቅማል" በሚል ቃል ተክቶ አረፍተ ነገሩን ለማዋቀር ቢሞከር የበለጠ የተሻለ ይሆን ነበር:: በመጨረሻው አረፍተ ነገር ከስራቸው የተሰመረባቸው ቃላት ሲመረመሩ ተገቢ ቦታቸውን ይዘው አልተዋቀሩም:: ይህም "ከራስ በመትረፍ ወላጆችንና ዘመዶችን በከፍተኛ ደረጃ አየዋለሁ" የሚለው ብዙ ሰዎች እራሳቸውን አሻሽለው ለወግ ማዕረግ ሲደረሱ ወይም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ከራሳቸው አልፈው ወላጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን የመርዳት ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ለመግለፅ የታሰበ ይመስላል:: ስለዚህ ሊተላለፍ የተፈለገው ሀሳብ ይህ ከሆነ "እኔም እራሴን አሻሽዬ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ስደርስ ከራሴ አልፎ ወላጆቼንና ዘመዶቼን ለመርዳት ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ" ተብሎ ቢስተካከል የተሻለ ይሆናል::

## 2. ለቃላት የተሳሳቱ ትርጉሞች በመስጠት የተፈጸሙ ስህተቶች

ተጠኚ ተማሪዎች በፃፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ ለቃላት የተሳሳቱ ትርጉሞች በመስጠታቸው የተነሳ የተፈፀሙ ስህተቶች መገኘታቸው መረጃዎች ያመለክታሉ:: ለአብነት ያህል የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች መመልከት ይቻላል::

-የቀበሌያችን ችግር መንግስት በአእምሮ ውስጥ በማስገባት መፍትሄ እንድሰጥ ነው፡፡

- ዘመድ ለዘመድ መምረጥ ደካማ ጎሳ በደካማነቱ እንድኖር ከማለት ባሻገር መላ የለውም::

- መጥፎ አርአያላለመፈጸም ከቤተሰብ ርቆ መኖር እንደሚሻል ተገንዝቢያለሁ::

- ደን መኖሩ ህይወት ያላቸው ነገሮች በጣም ጥሩ ምሳሌ ሆኖ ይታያል::

- ለወደፍት ዶክቴር ሌመሆን እመኛለሁ::

በመጀመሪያው አረፍተ ነገር ወስጥ የተሰመረበት ሀረግ ትርጉም ከአረፍተ ነገሩ ሀሳብ ጋር አብሮ የሚኻዝ ባለመሆኑ አንባቢው ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት በአግባቡ እንዳይረዳ እንቅፋት ፈጥሮበታል:: ስለዚህ ጸሀፊው በተሰመረበት ሀረግ ምትክ “ከግምት ውስጥ ወይም ከግንዛቤ ውስጥ” የሚሉ ሀረጋትን ቢጠቀም የተሻለ ይሆን ነበር:: በሁለተኛው አረፍተ ነገር ውስጥ እንዲሁም “መምረጥ” “ከማለት” “ባሻገር” እና “መላ” የሚሉትን ቃላት ባህርይ ስንመለከት በተሳሳተ መንገድ የገቡ ናቸው:: ስለዚህ “መመረጥ” የሚለው ቃል “መረዳዳት” “ከማለት” የሚለው ቃል “ከማድረግ” “ባሻገር” የሚለው ቃል “ውጭ” እና “መላ” የሚለው ቃል “መፍትሄ” በሚሉ አገላለጾች ቢተኩ አረፍተ ነገሩ በተወሰነ ደረጃ የተቃና ይሆን ነበር:: በአራተኛው አረፍተ ነገር “መጥፎ አርአያ” የሚለው ሀሳብ በዚህ አረፍተ ነገር ውሰጥ ያለቦታው የተገለጸ ነው:: ስለዚህ አረፍተ ነገሩ የተቃናና የተፈለገውን መልዕክት በአግባቡ ለማስተላለፍ እንዲቻል “መጥፎ ድርጊት” በሚለው ሀረግ ተካቶ መጠቀም ቢቻል ኖሮ የተሻለ ይሆን ነበር:: “ ለወደፍት ዶክቴር ሌመሆን እመኛለሁ” በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ከሆሄያት ጀምሮ በርካታ ስህተቶች አሉበት:: ስለዚህ ይህ አረፍተ ነገር “ዶክተር መሆን እመኛለሁ” በሚል ቢስተካከል የተሻለ ይሆናል::

### 3. እውቅና ያላገኙ አህጽሮተ ቃላትን በመጠቀም የተፈጸሙ ስህተቶች

በአማርኛ ቋንቋ መድብለ ቃላት ውስጥ እውቅናን ያላገኙና ያልተዛወተሩ አህጽሮተ ቃላትን የመጠቀም ጉዳይ ሌላው በድርሰቶቻቸው ላይ የታየ ስህተት ነው:: ተጠኚ ተማሪዎቹ አህጽሮተ ቃላትን ፈጥረው ቢጠቀሙም እንኳን በአንባቢው ዘንድ ያልተለመዱና ያልተዘወተሩ በመሆናቸው በጽሁፍ የመግባባት ሂደቱን ማገዳቸው

አልቀረም:: በዚህ መልክ የተፈጸሙ ስህተቶችን ለአብነት በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ማየት ይቻላል::

- ከዚህ ትምህርት ቤት እ/ር ብሎልኝ ጨርሼ ከወጣሁኝ በኋላ ደህና ዶክቴር ሆኜ መ/ት መስራት እመኛለሁ::
- ለት/ቴ ብዬ መለየቱ ግድ ብሆንብኝም....
- ለወደፊት የምመኘው ትምህርቴን ማሻሻል ነው::
- የደን ጥቅም ወ/ም አገልግሎት ይህ ብቻ አይደለም

እነዚህ ከላይ የሰፈሩት መረጃዎች በሚታዩበት ጊዜ ተደራሲያን ለምህፃረ ቃላቱ የተለያዩ ፍቺዎችን ሊሰጡ ይችላሉ:: ምንም እንኳ ከአውዱ ለመረዳት ወይም ለመገመት ባያስቸግሩም ከአጠቃቀም ትክክለኛነት አኳያ አህፅሮተ ቃላቱ ትርጉም እንደሚከተለው በተሳሳተ መንገድ ሊተረጎሙ ይችላሉ::

- እ/ር ለሚለው እስር፣ እግዚአብሔር፣ .... ሊባል ይችላል
- መ/ት ለሚለው መሳሪያ ቤት፣ መሰረተ ትምህርት፣ መኝታ ቤት፣ መንግስት፣ መዝናኛ ቤት፣ መምህርት ተብሎ ሊነበብ ይችላል:: አንዳንዶቹን በምንመለከትበት ወቅት ደግሞ በቀላሉ ለመረዳት አስቸጋሪ ሆነው እናገኛቸዋለን:: ለምሳሌ ያህል ወ/ም እና በጥቂቱ ተጠቃሾች ናቸው:: ስለዚህ ተደራሲ እንደነዚህ አይነት ምህፃረ ቃላት በሚገጥሙት ጊዜ ፍቻቸውን ባለማወቁና ከተለመደው የአህጽሮተ ቃላት አጠቃቀም ውጭ በመሆናቸው የአረፍተ ነገሩን ሀሳብ በቀላሉ ላይረዳ ይችላል::

### 4.2.1.3. በማያስፈልጉ ድግግሞሾች የተነሳ የተፈጸሙ ስህተቶች

ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ከተቆጠሩት አጠቃላይ ስህተቶች መካከል 442 ያህሉ ስህተት የተመዘገበው በዚሁ ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ ነው:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 4.48% ያህሉን ሸፍኗል:: አማካይ ስህተቱ 1.60 የሚሆነውን የሸፈነ ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 1.88 ሊሆን ችሏል::

ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በአላስፈላጊ ድግግሞሽ ምክንያት ከተፈፀሙት ስህተቶች መካከል ለአብነት ያህል የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ሊጠቀሱ ችለዋል::

- አንድ ልጅ ከቤተሰቦቹ ዘንድሳይለይ የትምህርት ህይወቱን እዛው ከቤተሰቦቹ ጋር ሆኖ ከቤተሰቦቹ ተለይቶ ብዙ ከተማረ በኋላ ጥሩ ውጤት በማምጣት ወደ ሌላ ሀገር ምርጥ ዩኒቨርሲቲ ወይም ኮሌጅ ወደ አለበት ይሄዳል::
- በመጀመሪያ የደን ሀብት የሰው ልጅ ሆነ ህይወት ያላቸው ነገሮችየሚጠቀሙበት በጣም ለሰው ልጅምጥቅም በመስጠት የታወቀ በመሆኑ ይታወቃል::
- አንደኛደረጃየተማርኩበት ትምህርት ቤት ወይም ትምህርቴን የጀመርኩበት ትምህርት ቤት ቅርብ ነበር::
- የወደፊት ምኞቴ እግዚአብሔር ምኞቴን ካሳካልኝ ብዙ ምኞት አለኝ::
- የደን ሀብት ጥቅም ሲንል ተቆጥሮ የማያልቅ ጥቅም ነው::
- እዚህ ትምህርት ቤትከገባሁበት ቀን ጀምሮእስከ አሁን እስካለሁበት ሰዓት ድረስ የምማረው ትምህርት ጥሩ ሆኖ እያለ በአንዳንድ ችግሮች ትምህርትቤቱን እንድጠላ አድርጎኛል::
- የትምርት ህይወትማለት ለእኔ በጣሙን ደስ የሚያሰኝ ህይወቴ ማለት ነው:

ከፍ ሲል የቀረቡት መረጃዎች የሚያመለክቱት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸውን ቃላት በመደጋገም ስህተቶች የተፈጸሙ መሆናቸውን ነው:: ሆኖም አረፍተ ነገሮችን እንደገና በማቀናጀትና የተለያዩ አያያዦችን በመጠቀም ድግግሞሹን ለማስወገድ ይቻላል:: ስለዚህ በድግግሞሹ ምክንያት በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የተፈፀሙት ስህተቶች በሚከተለው መልኩ ቢስተካከሉ የተሻለ ይሆናል:: "አንደ ሰው የትምህርት ህይወቱን ከቤተሰቦቹ ጋር በመሆን ከተማረ በኋላ ጥሩ ውጤት በማምጣት ወደ ሌላ ዩኒቨርስቲ ወይም ኮሌጅ ይሄዳል:: የደን ሀብት ህይወት ላላቸው ነገሮች በርካታ ጥቅሞችን በመስጠት በቀዳሚነቱ ይታወቃል::" "ትምህርቴን የተማርኩበት ትምህርት ቤት ቅርብ ነበር:: (የተማርኩበት ትምህርት ቤት ቅርብ ነበር)" "እግዚአብሔር ካሳካልኝ ብዙ ምኞት አለኝ::" "የደን ሀብት ተቆጥሮ የማያልቅ ጥቅም አለው" "የምማርበትን ትምህርት ቤት በአንዳንድ ችግሮች ምክንያት ብጠላውም በግቢው

ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት ግን ጥሩ ሆኖ አግኝቸዋለሁ::" "የትምህርት ቤት ህይወት በጣም ደስ የሚያሰኝ ነው::"

#### 4.2.1.4 በግድፈት ምክንያት የተፈፀሙ ስህተቶች

የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ተጠኚ ተማሪዎቹ በፃፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ ጥቂት የማይባሉ ስህተቶች እንደተፈጸሙ ለማየት ተችሏል:: ድርሰቶቹን በሚፅፉበት ጊዜ መግባት የነበሩባቸውን ነገሮች (ፊደል፣ ቃል፣ ሀረግ) በመግደፋቸው የተነሳ በፅሀፈት የመግባባቱን ሂደት ሊያደናቅፈው ችሏል:: በቋንቋ አጠቃቀም ስር በሰህተት ዘርፍነት የሶስተኛነት ደረጃን ይዞ የተገኘው ግድፈት ነው:: ግድፈቱ ከድምጽ ጀምሮ እስከ ሀረግ ሊደርስ ይችላል::በመሆኑም በተጠኚ ተማሪዎቹ ከተፈፀሙት 4387 የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች መካከል 288 ያህሉ በዚህ (በግድፈት) ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ የተቆጠሩ ሲሆን ይህም በመቶኛ ሲሰላ 2.92% ነው:: አማካይ ስህተታቸውም 1.04 ሲሆን አማካይ የሰህተት ድግግሞሻቸው 1.23 ሊሆን ችሏል::

ለአብነት ያህል ተማሪዎቹ ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ተወስደዋል:: ግድፈት የታየባቸውንም ቦታዎች በቅንፍ ለማመልከት ተሞክሯል::

- በወር አበባጊዜ ያለ ባህልና ጫና ( ) ምን አይነት መገንገድ ( ) እንደሚበጅ አላውቅም::
- ( ) የሰው ልጅ ( ) ሆነ ህይወት ያላቸው ነገሮች እየተጠቀሙበት ነው::
- ኤድስ ( ) በጋራ እንከላከል!
- ብዙ አይነት እህሎች ( ) ዘርተን እየተጠቀም ( ) ነው:: ስለዚህ ብዙ ጉዳት የለ( ) ንም
- ሀ( ) ወት ያላቸው ነገሮች ( ) አይኖሩም ነበር::
- ካፋ የምትታወቀው በደን ስለሆነ ( ) ደን መኖር በጣም ያስፈልጋል::

ከላይ ከቀረቡት አስረጅዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ከአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የተለያዩ ተዋቃሪዎችና ቃላት በመገደፋቸው የተነሳ አረፍተ ነገሮቹ የተሟላ ሃሳብ ማስተላለፍ ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል:: ስለሆነም አረፍተ ነገሮቹ የጎደላቸውን የተዋቃሪ አካላትና ቃላት በመጨመር በሚከተለው መንገድ ማረም ይቻላል::

"… ይህንን ባህልና ጫና በምን አይነት መንገድ መቅረፍ (ማስወገድ) እንደሚበጅ አላውቅም::" "ደንን የሰው ልጆችም ሆኑ ህይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ እየተጠቀሙበት ነው::" "ኤድስን በጋራ እንከላከል!" "… ብዙ አይነት እህሎችን ዘርተን እየተጠቀምን ነው:: ስለዚህ ብዙ ጉዳት የለብንም:: ህይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ አይኖሩም ነበር::" "ካፋ የምትታወቀው  በደን ሀብት ስለሆነ የደን መኖር በጣም አስፈላጊ ነው::"

### 4.2.1.5. ለቦታው የማያስፈልጉ ቃላት በመግባታቸው ምክንያት የተፈጸሙ ስህተቶች

ከቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ዘርፎች ውስጥ አራተኛ ደረጃን የያዘው ጭመራ (እከላ) ነው:: በመሆኑም በዚህ ጥናት ለቦታው የማያስፈልጉ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ተማሪዎች በደርሰቶቻቸው ውስጥ ባዋቀሯቸው አረፍተ ነገሮች ውስጥ መገኘት (መካተት) የሌለባቸውን የተለያዩ ተዋቃሪዎች (ምዕላዶች ቃላት…) ተካተው በመገኘታቸው ለስህተት መከሰት ምክንያት የሚሆኑበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው:: በመሆኑም ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች በጭመራ (እከላ) ምክንያት በርካታ ስህተቶች እንደተፈጸሙ ለመረዳት ተችሏል:: በአጠቃላይ በደርሰቶቹ ወስጥ ከተፈፀሙት ሰህተቶች መካከል 305 ያህሉ በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ የተቆጠረ ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ 3.09% ነው:: አማካይ የስህተት ብዛቱ 1.11 ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 1.30 ሆኗል::

በእከላ (ጭመራ) ምክንያት የተገጸሙ ስህተቶችን ለአብነት ያህል በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ማየት ይቻላል::

- እኔ ለወደፊት የምመኘው <u>በጣም</u> ጥሩ አስተማሪ ለመሆን ነው::

- በካፋ ውስጥ በርካታ ባህሎች እና ወጎች አሉን:: ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የመስቀል አከባበር ባህል ነው:

- ከቤተሰብ ርቆ መኖር የጀመርኩት ሃይስኩል ማለትም ከ8ኛ ክፍል ወደ 9ኛ ክፍል ስዘዋወር ነው::

ከፍ ሲል በአስረጅዎቹ ላይ የተሰመረባቸው ተዋቃሪዎች፣ ቃላት እና ሀረጋት በአረፍተ ነገሮቹ ላይ በመጨመራቸው የተነሳ የተለያዩ ስህተቶች ሊፈጠሩ ችለዋል:: ስለሆነም በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ተቀጽላ ሆነው የገቡት አካላት ቢወገዱ አረፍተ ነገሮቹ የተሰተካከሉ ሊሆኑ ይችላሉ::

#### 4.2.1.6 ኢ-መደበኛ ቃላትን (ዘዬ፣ ባእድ ቃላት፣ ያልተለመደ አጠቃቀም፣ ወዘተ.) በመጠቀም የተፈጸሙ ስህተቶች

የጽሁፍ ቋንቋ ከንግግር ቋንቋ የሚለየው ስርዓቱን የጠበቀ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን መደበኛ ቃላትን (የጽሁፍ ቋንቋን) የመጠቀም ጉዳይ ጭምር እንደሆነ ምሁራን ይጠቁማሉ:: ሀሳብን በጽሁፍ አማካይነት ለማስተላለፍ ተቀባይነት ባላቸው መደበኛ ቃላትና ሀረጋት መጠቀም አስፈላጊ ነው:: ስለሆነም ኢ-መደበኛ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ሊተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ግልጽነት ያሳጣዋል::ይሁን እንጅ በጥናቱ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው ይህ አይነቱ አጠቃቀም ያለ መሆኑን ነው::

ተማሪዎቹ በጻፏቸው የተለያዩ ድረሰቶች ውስጥ ኢ-መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች ታይተዋል:: በተገኘው መረጃ መሰረት በቋንቋ አጠቃቀም ከተፈጸሙት 4387 አጠቃላይ ስህተቶች መካከል 223 ያህሉ በዚሁ ንዑስ የስህተት ምድብ (ኢ-መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም) ውስጥ ነው:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 2.26% ሆኗል:: አማካይ ስህተቱ 0.81 ሆኖ፣ አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 0.95 ነው::

በኢ-መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም የተፈፀሙ ስህተቶች አነስተኛውን ቁጥር እንደሸፈኑ ከቀረበው መረጃ መረዳት ተችሏል:: ለአብነት ያህል የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል:: (ስህተት ያሉባቸው ቦታዎችም ከስራቸው ተሰምሮባቸዋል)::

- በተቻለኝ መጠን የአስረኛ ክፍል ጨርሼ በከፍተኛ ዉጤት ወደ prip መግባት ነው::
- … በአብዛኛው ግዜ ቆጮን በአይብ መጨርገድ ነው::
- በከፋ ብሄረሰብ ዘንድ የመስቀል በዓል በኃይለኛው ይከበራል:: በዓሉም በጣም የሚያስደስት ከመሆኑ የተነሳ ወጣት ሽማግሌ ያከብረዋል::
- ጥሩ ዉጤት አምጥተን አቦ ፀዳ እንድንል ጠንክረን እናጥና ::

ከፍ ሲል በአስረጅነት በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላትና ሀረጋት ስንመለከት ከተለመደው (ከመደበኛው) የቋንቋ አጠቃቀም ያፈነገጡ ሆነው እናገኛቸዋለን:: የመጀመሪያው አረፍተ ነገር prip የመሰናዶትምህርትን ለማመልከት ሲባል የተገለጸ ይመስላል:: ሆኖም “prip” የሚለው ቃል በተለያዩ የትምህርት ተቋማት በሚገኙ ተማሪዎች ዘንድ ትክክለኛ አጠቃቀም እንደሆነ ተደርጎ የሚወሰድ ቢሆንም በሌላው አንባቢ ዘንድ ግን ቃሉ እንግዳ ነው:: ስለዚህ “በተቻለኝ መጠን ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ወደአስረአንደኛ ክፍል(መሰናዶ)መግባት ነው” ተብሎ ቢገለጽ:: በተመሳሳይ መልኩ በሁለተኛው አረፍተ ነገር “መጨርገድ” የሚለው ቃል (አገላለጽ) በመደበኛው አጠቃቀም አንድን ነገር “መቁረጥ” የሚል ትርጓሜ ያለው ነው:: በዚህም የተነሳ ስህተት ሊፈጠር ችሏል:: ስለሆነም “…. በአብዛኛው ቆጮን በአይብ መብላት (መመገብ) ነው፡፡ ” ቢባል የተሻለ ይሆን ነበር:: በተራ ቁጥር ሶስት የቀረበው አረፍተ ነገር የቋንቋ አወቃቀር ስህተትና ኢ. መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች የሚታዩበት ሲሆን የቋንቋ አወቃቀሩ ስህተት በስፍራው ሲደረስበት የሚገለጽ ይሆናል:: በአረፍተ ነገሩ አማካይነት ለመግለጽ የተፈለገው ጉዳይ በከፋ ብሄረሰብ ዘንድ የ“መስቀልበአል” በድምቀት ይከበራል ለማለት ተፈልጎ ይመስላል:: በከፋ ብሄረሰብ ዘንድ የመስቀል በአል “በኃይለኛው” ይከበራል ተብሎ የተገለፀው:: በሌሎች አረት ነገሮች ውስጥ የሚገኙት ኢ-መደበኛ ቃላትም (አቦ፣ ፀዳ …) ከላይ በዝርዝር ከተመለከትናቸው ችግሮች የተለዩ አይደሉም:: በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የእነዚህ ቃላት አጠቃቀም መደበኛና የተዘወተሩ ባለመሆናቸው የተነሳ በተግባቦት ሂደቱ ላይ የራሳቸውን ተጽእኖ ሊያሳርፉ ችለዋል:: ስለዚህ ከላይ በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የገቡት ኢ-መደበኛ ቃላት ለመደበኛው አማርኛ ቃላት ተናጋሪ ትርጉማቸውን ለመረዳት

ሊያስቸግሩ ይችላሉ:: ሆኖም ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው ስለሚጠቀሙባቸው በድርሰቶቻቸው ውስጥ በመማስገባት ስህተት እንዲፈጽሙ አስገድዷቸዋል:: ሌላው በዚህ ርዕስ ስር የተዳሰሰው በዐድ ቃላትን የመጠቀም ጉዳይ ነው:: እንደሚወቀው በማንኛውም ቋንቋ የበዐድ ቃላት ተሰግስገው የመኖራቸው እውነታ ያለ የነበረና የሚኖርም ነው:: ሆኖም በአንድ ቋንቋ ሀሳብን ሊገልፁ ወይም ሊወክሉ የሚችሉ ቃላት እስካሉ ድረስ እነዚህ ከባእድ የተወሰዱ ቃላትን መጠቀም ተመራጭነት የለውም:: በተለይ በፅሁፍ ላይ ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል:: ለምን ቢባልም ፅሁፍ መለስ ተብሎ የሚዳሰስ ስለሆነ እነዚህ ቃላት በጥንቃቄ ሊፈተሹ ይገባል::

በዚህ መረጃ ውስጥ ገን እነዚህ የባዕድ ቃላት በተማሪዎች ድርሰቶች ውስጥ ተስተናግደው ታይተዋል::

ምሳሌ:- ማቴሪያል፣ ክላስ፣ ሃይስኩል፣ ቲቶሪያል፣ ፕሪፕ፣... የሚሉት ቃላት አቻ ወይም ትክ የሆኑ የአማርኛ ቃላት ስላላቸው እነዚህን ቃላት አለመጠቀሙ ተመራጭነት አላቸው::

በርካታ ቁጥር ያላቸው ስህተቶች የተቆጠሩት በቋንቋ አወቃቀር (የአረፍተ ነገር አወቃቀር) የስህተት ምድብ ውስጥ ነው:: በሁለቱም ዙሮች ተማሪዎች በፃፏቸው የደርሰት መልመጃዎች ከተቆጠሩት 9869 አጠቃላይ ስህተቶች መካከል 2571 (26.06%) ያህል ስህተቶች የተገኙበት ሲሆን፣ አማካይ የስህተት ብዛት 9.32 ነው:: አማካይ የስህተት ድግግሞሽ ደገሞ 10.95 ሊሆን ችሏል::

በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛ ስህተት የተመዘገበው በስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ዙሪያ ነው:: ተማሪዎቹ በሁለት ዙሮች ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ጉድለት የተነሳ በርካታ ስህተቶች እንደተፈጸሙ ከቀረበው መረጃ መመልከት ይቻላል:: በአጠቃላይ በስህተትነት ከተቆጠሩት 9869 ስህተቶች መካል 2175 (22.04%) ያህሉ በዚሁ የስርዓት ነጥብ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ውስጥ የሚጠቀስ ነው:: አማካይ የስህተት ብዛት 7.88 ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 9.27 ሆኗል::

### 4.2.2 በቋንቋ አወቃቀር (ሰዋስው) ስር የታዩ ስህተቶች

ድርሰት ከአረፍተ ነገሮች የሚዋቀር በመሆኑ እያንዳንዱ አረፍተ የቋንቋውን ትክክለኛ ሰዋስዋዊ ስርዓት ጠብቆ መዋቀር አለበት::ከንግግር ቋንቋ ይልቅ በጽሁፍ የሚተላለፍ መልዕክት የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት መጠበቅ እንዳለበት በርካታ ምሁራን ይስማሙበታል:: ይህንን አስመልክቶ Widdowson (1979፣118) ሲገልጹ፣ በጽሁፍ የሚገለጽ ሀሳብ በማያሻማና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ሊተላለፍ የሚችለው ሰዋስዋዊ ስርዓቱን ጠብቆ ሲጻፍ ነው::

በሰንጠረዡ ላይ በቀረበው የጥናቱ መረጃ መሰረት በአቢይ የስህተት አይነት ከተመደቡት የተለያዩ ስህተቶች መካከል አንዱ የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ነው:: ተጠኚ ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የቋንቋውን የአወቃቀር ስርዓት (ሰዋስው) በሚገባ ካለማወቅ የተነሳ በርካታ ስህተቶች እንደተፈፀሙ ለመረዳት ተችሏል::

በአጠቃላይ በተጻፉት ድርሰቶች ውስጥ ከተፈጸሙት ስህተቶች መካከል 2571 ያህል የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች የተመዘገቡ ሲሆን፣ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 26.06 ነው::አማካይ የስህተት ብዛቱ (መጠኑ) 9.31 ሲሆን አማካይ የሰህተት ድግግሞሹ ደግሞ 10.96 ሊሆን ችሏል::

ከቋንቋ አወቃቀር ጋር በተያያዘ በደርሰቶቹ ውስጥ በዋነኛነት የተዳሰሱት የመስተዋድድ አገባብ ስህተቶች፣ የአረፍተ ነገር ስሙሙነት (በአረፍተ ነገሩ ውስጥ በሚገኙ ተዋቃሪዎች መካከል የቁጥር፣ የመደብ … ስህተቶች)፣ የአጣማሪዎች አገባብ ስህተቶች፣ በአረፍተ ነገር ውስጥ  የቅደም ተከተል ሰህተቶች ናቸው:: ዝርዝር መረጃው ከዚህ በታች በተመለከተው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቧል::

## ሰንጠረዥ 6:- በቋንቋ አወቃቀር (ሰዋስው) ስር የታዩ ዝርዝር ስህተቶች

| | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስህተቶቹ አይነት | የስህተቶች ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተቶች ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተቶች ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
| የአ.ነገር ስምምነት | 389 | 7.33 | 2.82 | 3.41 | 438 | 9.53 | 3.17 | 3.63 | 827 | 8.38 | 3.00 | 3.52 |
| የመስተዋድድ አገባብ | 504 | 9.55 | 3.65 | 4.42 | 314 | 6.84 | 2.28 | 2.60 | 818 | 8.29 | 2.69 | 3.49 |
| የቃላት አወቃቀር ቅደም ተከተል | 262 | 4.97 | 1.90 | 2.30 | 249 | 5.42 | 1.80 | 2.06 | 511 | 5.18 | 1.85 | 2.18 |
| የአያያዦች አገባብ | 217 | 4.11 | 1.57 | 1.90 | 198 | 4.31 | 1.43 | 1.64 | 415 | 4.21 | 1.50 | 1.77 |
| ጠቅላላ ድምር | 1372 | 25.96 | 9.94 | 12.03 | 1199 | 26.10 | 8.68 | 9.93 | 2571 | 26.06 | 9.31 | 10.96 |

#### 4.2.2.1 በአረፍተ ነገር ስምምነት ላይ የተፈጸሙ ስህተቶች

ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ስሙሙነቶችን በመጣስ በረካታ ስህተቶች እንደተፈጸሙ ከተገኘው መረጃ ለመመልከት ተችሏል:: ከፍ ሲል በቀረበው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው በቋንቋ አወቃቀር አቢይ የስህተት ምድብ ወስጥ ከተፈጸሙት ንዑሳን የስህተት አይነቶች መካከል በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ስህተቶች የተቆጠሩት የአረፍተ ነገር ስምሙነቶችን ካለመጠበቅ የተነሳ የተፈጸሙ ናቸው:: በደርሰቶች ውስጥ በአጠቃላይ ከተፈጸሙት 9869 ስህተቶች መካከል 827 ያህሉ የተቆጠረው በዚሁ ንዑስ የስህተት አይነት ምድብ ውስጥ ነው:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 8.38% ሲሆን፣ አማከይ የሰህተት ብዛቱ ደግሞ 3.00 ሆኖ ተገኝቷል:: የስህተት ድግግሞሹምም 3.52 ነው፡፡

በአረፍተ ነገር ስምሙነት ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ የሚነሱት ጉዳዮች የቁጥር፣ የፆታ እና የመደብ ስሙሙነት ስህተቶች ሲሆኑ፣ ለአብነት ያህል የሚከሉት ቀርበዋል::

**ሀ. በቁጥር አለመስማማት የተፈጸሙ ስህተቶች**

- ቆጮ እንሰት ተፍቆ የሚገኝና ራሱን የቻለ የምግብ <u>አይነቶች </u>ነው::
- ህይወት ያላቸው ነገሮች <u>አይኖርም</u>::
- ደን <u>የሰው ልጅም ሆነ</u> ህይወት ያላቸው ነገሮች <u>የሚጠቀምበት</u> የተፈጥሮ ሀብት ነው::
- ልጆቻቸው ከጉያቸው <u>እንዳይወጣ</u> የሚፈለጉ አንዳንድ ቤተሰቦች አሉ::
- ጎጂ ባህሎችን በብዙ <u>ቦታ</u> ከፋፍሎ ማየት ይቻላል:: እነዚህን ዘርዘር አድርገን <u>እንመልከተው</u>::
- ሽማግሌዎች አምስት ሰዎች <u>ይዞ</u> ወደ ሙሽሪት <u>ቤተሰብ ይሄዳል::</u>
- ጎጂ ባህሎች ብዙውን ጊዜ በአባቶቻችን <u>የተፈፀመ ነው::</u>

ከፍ ሲል ከቀረቡት ምሳሌዎች መገንዘብ የሚቻለው በአብዛኛው በብዙ ቁጥር መገለጽ ያለባቸው ቃላትና ሀረጋት በነጠላ ቁጥር መገለጻቸው እንዲሁም በነጠላ ቁጥር መገለፅ የነበረባቸው በብዙ ቁጥር መገለፅ አለባቸው::

እነዚህ ከላይ ለቁጥር ስሙሙነት ስህተት የቀረቡት አስረጅዎች በሚከተለው መልኩ ቢስተካከሉ የተሻሉ ሊሆኑ ይችላሉ::

"ቆጮ እንሰት ተፍቆ የሚገኝና ራሱን የቻለ የምግብ አይነት ነው "ህይወት ያላቸው ነገሮች አይኖሩም::" "ደን የሰው ልጆቹም ሆኑ ህይወት ያላቸው ነገሮች የሚጠቀሙበት የተፈጥሮ ሀብት ነው::" "ልጆቻቸው ከጉያቸው እንዳይወጡ የሚፈልጉ አንዳንድ ቤተሰቦች አሉ::" "ጎጅ ባህሎችን በብዙ ቦታዎች ከፋፍሎ ማየት ይቻላል:: እነዚህን ዘርዘር አድርገን እንመልከታቸው::" "ሽማግሌዎች አምስት ሰዎችን ይዘው ወደ ሙሽሪት ቤተሰቦች ይሄዳሉ::" "ብዙዎቹ ጎጅ ባህሎች በአባቶቻችን የተፈጸሙ ናቸው::"

### ለ. በመደብ አለመስማማት የተፈጸሙ ስህተቶች

ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ ከቁጥር አለመስማማት በተጨማሪ የመደብ አለመስማማት ስህተቶች ተስተውለዋል:: ለአብነት ያህል የሚከተሉተን አረፍተ ነገሮች መመልከት ይቻላል::

- ማህበራዊ ህይወትን <u>ከሚያውቀው</u> ነገር <u>ተነስቼ</u> ለመዘርዘር እሞክራለሁ::
- <u>ያደኩትደቻ</u> ወረዳ ስሆን <u>ከአባታቸው</u> ከአቶ ጥላሁን ወርቁ እና <u>ከእናታቸው</u> ከወይዘሮ አስካለች መሸሻ በ1992 አመት ምህረት <u>ተወለድኩ::</u>
- <u>ከቤተሰቦቹ ርቆስኖር</u> በገጠሙት ውጣውረዶች የተነሳ የሰው ሀገር አስፈላጊ አለመሆኑን ተረድቷል::

እነዚህ ከላይ የቀረቡ የመደብ ስምሙነት የሌላቸው አረፍተ ነገሮች በሚታዩበት ጊዜ ስህተቶቹ የመደብ አለመስማማት ችግር ብቻ ሳይሆን የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተትም ያለባቸው ናቸው::እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት አረፍተ ነገሮች በሚፈተሹበት ጊዜ በመጀመሪያው አረፍተ ነገር እነሱና እሱ በሚሉ አቻ ባልሆኑ

ተውላጠ ስሞች ተዋቅሯል:: በሁለተኛ አረፍተ ነገር ውስጥም እሱ በሚል ተውላጠ ስምን በሚጠቁም ቃል ጀምሮ አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር በሆነው እኔ በሚለው ተውላጠ ስም ሀሳቡን ይቀጥላል:: በሶስተኛው አረፍተ ነገርም እንዲሁ አንደኛና ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተውላጠ ስሞች መደበላለቅ ይታያል:: ከዚህም ሌላ አራተኛው አረፍተ ነገርም ተመሳሳይ ችግር ይታይበታል:: የአምስተኛው አረፍተ ነገር ባለቤት እኔ የሚል ተውላጠ ስም ቢሆንም እነሱ የሚለውን ተውላጠ ስም በሚያመለክቱ ቃላት (ከአባታቸው እና ከእናታቸው) ተዋቅሯል:: የመጨረሻው አረፍተ ነገር ደግሞ ድርሰቱ የቀረበበትን አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር የትረካ አንጻር በሚጥስ መልኩ በሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተጠቅሟል:: ስለሆነም እነዚህ አረፍተ ነገሮች በሚከተሉት መንገዶች ቢስተካከሉ የተሻሉ ሊሆኑ ይችላሉ::

- ደን ለሰው ልጆች በርካታ ጥቅም ቢሰጥም፣ ሰዎች ግን ጥቅሙን አውቀው መንከባከብና መቆጣጠር አይወዱም::
- ማህበራዊ ህይወትን ከማውቀው ነገር ተነስቼ ለመዘርዘር እሞክራለሁ
- ትምህርት ለሀገር እድገትና ብልፅግና ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ለማንኛውም እንግዳ ነገር አይደለም::

- አንድ ሰው ትምህርት ካልተማረ አንድን ነገር በአግባቡ ሊሰራ አይችልም::

- ያደኩት ዴቻ ወረዳ ሲሆን ከአባቴ ከአቶ ጥላሁን ወርቁ እና ከእናቴ ከወይዘሮ አስካለች መሸሻ በ1992 አመተ ምህረት ተወለድኩ::
- ከቤተሰቦቼ ርቆ ሲኖር ባጋጠሙት ውጣ ውረዶች የተነሳ የሰው አገር አስፈላጊ አለመሆኑን ተረድቷል::

### ሐ. በፆታ አለመስማማት የተፈጸሙ ስህተቶች

- አንቺ በሩን <u>ቆልፍ</u>
- ... <u>በጣም የምወዳት</u> ጓደኞዬ <u>ከመሆኑ</u> የተነሳ ልብሳችንን እንኳን እየተቀያየር ነው የምንለብሰው

- ያደኩበት ሰፈር መሳለሚያተብሎ የምትጠራማር የሆነች ጎጥ ናት::

ከላይ በፆታ ስሙሙነት ስህተቶች ዙሪያ በተዳሰሱት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ተጠኚ ተማሪዎቹ የአነስታይ ጾታ አመልካች ቅጥያቆዎችን በላመጠቀማቸው በጻፏቸው ድርሰቶች ላይ የሀሳብ መፋለስ ችግር ተስተውሏል:: በመሆኑም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ደርጊት ፈጻሚዎች ሴቶች ሆነው ሳለ በወንዶች እንደተፈጸሙ ተደርገዋል:: ስለዚህ ካላይ በጾታ ስሙሙነት ችግር የሰፈሩት አረፍተ ነገሮች በሚከተሉት መልኩ ቢስተካከሉ የተሻሉ ይሆናሉ::

"አንቺ በሩን ቆልፊ::" "... በጣም የምወዳት ጓደኞዬ ከመሆኗ የተነሳ ልብሳችንን እንኳን ሳይቀር እየተቀያየርን ነው የምንለብሰው::" "ያደኩባት ሰፈር መሳለሚያ ተብላ የምትጠራ ማር የሆነች ጎጥ ናት::"

#### 4.2.2.2 በመስተዋድድ አገባብ ላይ የታዩ ስህተቶች

ከፍ ሲል ከቀረበው ሰንጠረዥ መመልከት እንደሚቻለው በቋንቋ አወቃቀር (ሰዋስው) የስህተት ምድብ ውስጥ ከታዩት ንዑሳን ስህተቶች መካከል አንዱ የመስተዋድድ አገባብ ነው:: ተማሪዎቹ ከጻፏቸው ድረሰቶች ውስጥ በአጠቃላይ ከተፈጸሙት 9869 ስህቶች መካከል 818 ያህሉ የተቆጠረው በዚሁ ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ ነው:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 8.29% ሊሆን ችሏል:: አማካይ የስህተት ብዛቱ (መጠኑ) 2.69 ሲሆን፣ የስህተት ድግግሞሹ 3.49 ያህል ነው:: የትክክለኛነት ተዛማጅነት ውጤቱ ደግሞ 28.69 ነው::

ተማሪዎቹ ከጻፏቸው ድርሰቶች የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የመስተዋድድ አገባብ ሰህተቶች የተፈጸሙት መሰተዋድድ መግባት በማያስፈልግበት ቦታ መሰተዋድዶችን በመጨመር፣ ትክክልና ተገቢ ያልሆኑ መስተዋድዶችን በመጠቀም እና መስተዋድዶችን በመግደፍ ነው:: እያንዳንዳቸውን አንድ በአንድ በምሳሌ በማስደገፍ እንደሚከተለው ለማየት ተሞክሯል::

1. **መስተዋድዶች በማያስፈልጉበት ቦታ በመግባታቸው የተፈጸሙ ስህተቶች**

ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ምንም አይነት መስተዋድዶቸ በማያስፈልግባቸው ቦታዎች ላይ መሰተዋድዶችን ሲጠቀሙ ተስተውለዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ለአብነት ያህል የሚከተሉት አረፍት ነገሮች ቀርበዋል::

- ሀገራችንን የሚጠብቅ ትውልድ እያለቀ ላይ ነው::
- ከትምህርት ብዙ ጥቅም አለው::
- ትናንትም ሆነ ዛሬ የሁሉንም ቤት እያንኳኳና እያነጋገረ ላይ ያለው ድህነት እና ኤች አይ ቪ ኤድስ ናቸው::
- ትምህርት የሰውን ልጅ ኑሮ ለማሻሻል፣ የሰመረ ህይወት ለመምራት… ለ ወዘተ. ይጠቅማል::

ከላይ በአስረጅነት ከቀረቡት አረፍተ ነገሮች መገንዘብ የሚቻለው የተሰመረባቸው መስተዋድዶች ያለምንም አይነት ሰዋስዋዊ አገልገሎት የገቡ መሆናቸውን ነው:: በመሆኑም ለስህተቶቸ መፈጠር ምክንያቶች ሊሆኑ ችለዋል::ከመጨረሻው አረፍተ ነገር በስተቀርበአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ያለ አግባብ የገቡትን መስተዋድዶች በማውጣትየተስተካከሉ አረፍተ ነገሮችን መገንባት ይቻላል::

2. **ትክክለኛ ያልሆኑ መስተዋድዶችን በመጠቀም የተፈጸሙ ስህተቶች**

በመስተዋድድ አጠቃቀም ላይ የታየው ሌላው ስህተተ ትክክለኛውን መስተዋድድ በትክክለኛው ቦታው አለመጠቀም ወይም የተሳሳተ መስተዋድድ መጠቀም ነው:: ይህ አይነቱ ስህተት ተማሪዎቹ በጻፏቸው የተለያዩ ደርሰቶች ውስጥ በስፋት ይታያል:: ለአብነት ያህል የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች እንመልከት::

- ትምርትከሚሰጣቸው ጥቅሞች ከዚህ በታች ቀርበዋል::
- ጠለፋ የ ጎጂ ባህሎች ውስጥ አንዱ ሆኖ የ ሴት ልጆች ላይ ብዙ ጉዳቶች ያመጣል፡፡ድህነትና ኤች አይ ቪ ኤድስ በሀገራችን በጣም እየተስፋፋና ለ

ሀገራችን እድገትም ሆነ ለ ወጣቶች ወይም ለ አምራች ዜጎች ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት የከፋ ነው::

- … ይህ ማህበራዊ ህይወት ለ አካባቢያችን ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል::
- ቆሎ በካፋ ለምግብነት ብቻ ይጠቅማል ማለት አይደለም::

ከላይ በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው መስተዋድዶች ትክክለኛና ተገቢ ቦታቸውን ጠብቀው ባለመግባታቸው የተነሳ ለተለያዩ ስህተቶች መፈጠር ምክንያት ሆነዋል:: ስለዚህ ከላይ የተሰመረባቸውን የተለያዩ መስተዋድዶቸ በተገቢ መስተዋድዶች በመተካት አረፍተ ነገሮቹ ሊስተካከሉ ይችላሉ:: ተስተካክለው ሲጻፉም የሚከተለውን ይመስላሉ::

"ትምህርት የሚሰጣቸው ጥቅሞች ከዚህ በታች ቀርበዋል::" "ጠለፋ ከጎጅ ባህሎች ውስጥ አንዱ ሆኖ በሴት ልጆች ላይ ብዙ ጉዳቶች ያመጣል::" "ድህነት እና ኤች አይ ቪ ኤድስ በሀገራችን በጣም እየተስፋፋና በሀገራችን እድገትም ሆነ በወጣቶች ወይም በአምራች ዜጎች ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት የከፋ ነው::" "… ይህ ማህበራዊ ህይወት በአካባቢያችን ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል::" " በካፋቆሎ ብቻ ለምግብነት ይውላል ማለት አይደለም::

በዚህ አይነት ሁኔታ መስተዋድዶች በትክክለኛ ቦታቸው መግባት ይገባቸው ነበር:: ይህ ባለመፈጸሙ አረፍተ ነገሮቹ ስህተት ሊሆኑ ችለዋል::ተማሪዎች በፃፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ ተገቢና ትክክለኛ ያልሆኑ መሰተዋድዶችን በመጠቀም፣ አስፈላጊ ያልሆኑ መስተዋድዶችን በመጨመር፣ ከተለመደው የቋንቋ አገባብ ውጭ ሁለት መስተዋድዶችን በአንድ ላይ በማስገባት እና መሰተዋድዶችን መግባት በሚገባቸው ቦታ በመገደፍ ስህተት ፈጽመዋል::

#### 4.2.2.3 የቃላት አወቃቀር ቅደም ተከተልን ባለመጠበቅ የተፈጸሙ ስህተቶች

ድምፆች ተቀናጅተው ምዕላድን ምዕላዶች ደግሞ ቃላትን፣ ቃላትም በሚያደርጉት ቅንጅት ሀረጋትን እና አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ:: አንድ አረፍተ ነገር አንድን የተሟላ መልዕክት ያስተላልፋል:: ይህ ሊሆን የሚችለውም አረፍተ ነገሩን ስዋስዋዊ

ስርዓት አስጠብቀን ማዋቀር ስንችል ነው:: ቃላትን በመሰደር ብቻ ትክክለኛ መልክዕት ሊያስተላልፍ የሚችል አረፍተ ነገር ማግኘት አይቻልም::

በከፍኛ ቋንቋ አፋቸውን በፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ድርሰቶቸ ውስጥ ከተፈጸሙት ስህተቶች አንዱ የቃላት አወቃቀር ቅደም ተከተል ነው:: የአማርኛ ቋንቋ የራሱ የሆነ የቋንቋ አወቃቀር (የቃላት አሰዳደር ቅደም ተከተል) አለው:: ድርሰቶቹ ከዚህ ቅደም ተከተል ባፈነገጠ መልኩ በመጻፋቸው የተነሳ ስህተቶቸ ተፈጽመዋል::

ተጠኚ ተማሪዎቹ ከፈጸሚቸው 9869 አጠቃላይ ስህተቶች መካከል 511 ያህሉ የተቆጠረው በቃላት አሰላለፍ ቅደም ተከተል የስህተት ምድብ ውስጥ ነው:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 5.18% ሲሆን፣ አማካይ የስህተት ብዛቱ ደግሞ 1.85 ሆኖ ተገኝቷል:: የሰህተት ድግግሞሹም 2.18 ሲሆን የትክክለኛነት ተዛማጅነት ውጤቱ ደግሞ 45.93 ይዞተገኝቷል::በቃላት አወቃቀር ወይም አሰላለፍ ስር ተማሪዎች ከፈጸሚቸው ስህተቶች ለአብነት ያህል የሚከተሉት ቀርበዋል::

- ለሀገራችን በጣም ደን በርካታ ጠቀሜታዎችን ይሰጣሉ::
- በካፋ ቆሎ ብቻ ለምግብነት ሳይሆን ለብዙ አገልግሎት ይውላል::

ከላይ የቀረቡት አስረጅዎች ቃላቱ የአማርኛ ቋንቋ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓት ከሚፈቅደው ውጭ የተሰደሩ በመሆናቸው የአረፍተ ነገሮቹ ሀሳብ በእንጥልጥል የቀረ ያህል እንዲስማን ምክንያት ሊሆኑ ችለዋል:: በመሆኑም እነዚህ ከላይ በምሳሌነት የቀረቡት አረፍተ ነገሮች በሚከተለው መንገድ ቢስተካከሉ ተገቢውን መልዕክት ሊያስተላልፉ የሚችሉ መዋቅሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ::

- ደኖች ለሀገራችን በጣም በርካታ ጥቅሞችን ይሰጣሉ::
- በካፋ ቆሎ ለምግብነት ብቻ ሳይሆን ለብዙ አገልግሎት ይውላል::

#### 4.2.2.4 በአያያዦች አገባብ ላይ የታዩ ስህተቶች

በመጨረሻ ደረጃ የታየው ንዑስ የአያያዦች አጠቃቀም ነው:: ተጠኚ ተማሪዎች የአጣማሪዎችን አገባብ በትክክል ካለመጠቀም የተነሳ በርካታ ስህተቶቸን

እንደፈፀሙ የተገኙት መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በአጠቃላይ በአጣማሪዎች ጉድለት የተነሳ የተፈጸሙ ስህተቶች ብዛት ከጠቅላላው 415 ያህሉን ሸፍኗል:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 4.21 ያህል ሆኗል:: አማካይ ስህተቱ 1.50 ሲሆን አማካይ የስህተት ደግግሞሹ ደግሞ 1.77 ነው::ለአብነት ያህል የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች መመልከት ይቻላል::

- ትምህርት ለሰው ልጆች በጣም አስፈላጊ ነው:: ሆኖም አንድ ሰው ትምህርት ካልተማረ አንድን ስራ በአግባቡ ሊሰራ አይችልም::
- በአለማችን ውስጥ የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች መኖራቸው እርግጥ ነው:: ይሁን እንጂከእነዚህ ውስጥ አንዱ ደን በመሆኑ በሁሉም ዜጎች ዘንድ የታወቀ ነው::
- ቆሎ በጣም አስፈላጊነቱ የሚገነው አመት በዓል ሲመጣ ነው:: ይሁን እንጂ ቆሎ በአመት በአል የሚፈለግበት በስጋ ለመብላት በጣም ምቹና ተስማሚ በመሆኑ ነው::
- … ይሁን እንጅሆኖምግን ወደፊት የምመኘው ጥሩ አስተማሪ ለመሆን እፈልጋለሁ::

እነዚህ ከፍ ሲል ለአብነት ያህል የጠቀስናቸው ከመረጃዎች ውስጥ የተወሰዱ ናቸው:: በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የአያያዦች ማሪዎች ትክክለኛና ተገቢ ቦታ አለመያዝ፣ በማያስፈልግበት ቦታ መግባትና መገደፍ በሀሳብ ፍሰቱ ላይ መደናቀፍን አስከትሏል::

ከላይ ለአብነት ያህል የቀረቡ አረፍተ ነገሮች ሰንመለከታቸው አያያዦች በትክክለኛ ቦታቸው የገቡ አይደሉም:: ለምሳሌ በአንደኛው አረፍተ ነገር ትክክለኛውን አያያዥ ቃል ያለመጠቀም ስህተት ይታያል:: በመሆኑም አረፍተ ነገሩ "ትምህርት ለሰው ልጅ በጣም አሰፈላጊ ነው:: ምክንያቱም አንድ ሰው ትምህርት ካልተማረ አንድን ስራ በአግባቡ ሊሰራ አይችልም" ተብሎ ቢስተካከል የተሻለ ይሆን ነበር:: በሁለተኛው አረፍተ ነገር ላይ ደግሞ የማያስፈልግ አያያዥ

ተጨምሯል:: ለምሳሌ "ይሁን እንጂ" የሚለው አያያዥ በማያስፈልግበት ቦታ የገባ ነው::

በሁለተኛ አረፍተ ነገር ተገቢ የሆነ አያያዥ ተጠቅመው አይታዩም:: በመሆኑም አረፍተ ነገሩ "የቆሎ አስፈላጊነቱ በጣም የሚገነው አመት በአል ሲመጣ ነው:: ምክንያቱም ቆሎ በአመት በአል የሚፈለግበት በስጋ ለመብላት በጣም ምቹና ተስማሚ በመሆኑ ነው" ተብሎ ቢፃፍ የተሻለ ይሆን ነበር::

በመጨረሻው አረፍተ ነገር ውስጥ "ይሁን እንጂ"፣ "ሆኖም ግን" የሚሉት አያያዦች በአንድ ላይ በመግባታቸው ለስህተቱ መከሰት ምክንያት ሆነዋል:: ስለዚህ በሚከተለው መልኩ ቢተካከል ሳይሻል አይቀርም:: "... ይሁን እንጅ ወደፊት የምመኘው ጥሩ አስተማሪ መሆን ነው::" ሌሎች አረፍተ ነገሮችም በሚመረመሩበት ጊዜ ችግራቸው ከእነዚህ የተለየ አየደለም:: አጠቃላይ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ተገቢ ያልሆኑ የአያያዦች አገባብ ለሰዋስው ስህተት መከሰት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ነው:: ይህም በአጠቃላዩ የአረፍተ ነገር መዋቅር ላይ ስህተት እንዲፈጠር ምክንያት ከመሆኑም ባሻገር በአረፍተ ነገሮቹ መልዕክትና ፍቺ ላይም አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል::

### 4.2.3 በስርአተ- ነጥቦች አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች

ስርዓተ ነጥብ በጽሁፍ የሚቀርብን ሀሳብ በቃላት፣ በሀረጋት እና በአረፍተ ነገሮች ከፋፍሎ ለማቅረብ፣ የአረፍተ ነገሩ ሀሳብ ማለቁን (መቋጨቱን) ለማመልከት፣ የሚዘረዘሩ ነገሮችን ለመለየት፣ የአረፍተ ነገሩ ሀሳብ ጥያቄያዊ ወይም ሀሳብ ሰጭ መሆኑንና በጽሁፉ ውስጥ የተገለጸው ሀሳብ የራስ አለመሆኑን ለማመልከት ከፍተኛ የሆነ አገልግሎት አለው-ስርዓተ ነጥብ:: ስለዚህ ጸሀፊው በጽሁፍ ያዋቀረውን ሀሳብ ለአንባቢያን ለማድረስ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው መጠቀም ይኖርበታል:: ይህ ካልሆነ ግን የአንባብያን የማንበብ ተነሳስቶና ፍላጎት ሊቀንስ እንደሚችል Day (1984: 137) ይገልፃሉ::

ተማሪዎች ከጻፏቸው ድረሰቶች መረዳት የሚቻለው በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ውስጥ የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ከፍተኛውን ቁጥር ሲይዝ፣ በመቀጠል የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተት ተስተውሏል:: የጥያቄ

ምልክት፣ የትዕምርተ አንክሮ እና የትዕምርተ ጥቅስ አጠቃቀም ስህተቶች በደረጃ ዝቅተኛውን ቁጥር እንደሸፈኑ መረጃው ያሳያል::

ይህ የስርዓተ ነጥብ ስህተት ከጠቅላላው 9869 ስህተት ውስጥ 2035 እንደሆነ በቆጠራው ለማረጋገጥ ተችሏል:: ይህ ቁጥር ከሌሎች ስህተቶች ጋር ተነፃፅሮ 22.03 ሆኗል:: በእያንዳንዱ ድርሰት ያለው አማካይ የስህተት መጠንም 7.86 ነው:: በመቶ ቃላት ውስጥ የተገኘው የስህተት ድግግሞሽ 8.74 ሲሆን በአጠቃላይ  ዝርዝር መረጃውን ከዚህ በታች በተመለከተው ሰንጠረዥ ላይ ለማቅረብ ተሞክሯል::

## ሰንጠረዥ 5:በስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ስር የታዩ ዝርዝር ስህተቶች

| | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስህተቶቹ አይነት | የስህተቶች ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተቶች ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተቶች ብዛት | በመቶኛ ሲሰላ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
| አራት ነጥብ | 617 | 11.70 | 4.47 | 5.42 | 441 | 9.60 | 3.20 | 3.65 | 1058 | 10.72 | 3.83 | 4.51 |
| ነጠላ ሰረዝ | 519 | 9.84 | 3.76 | 4.56 | 413 | 8.99 | 2.99 | 3.42 | 932 | 9.44 | 3.38 | 3.97 |
| ትዕምርተ ጥቅስ | 81 | 1.54 | 0.59 | 0.71 | 59 | 1.28 | 0.43 | 0.49 | 140 | 1.42 | 0.51 | 0.06 |
| ትዕምርተ አንክሮ | 19 | 0.36 | 0.13 | 0.14 | 13 | 0.28 | 0.09 | 0.11 | 32 | 0.32 | 0.12 | 0.14 |
| ጥያቄ ምልክት | 7 | 0.13 | 0.05 | 0.06 | 6 | 0.13 | 0.04 | 0.05 | 13 | 0.13 | 0.05 | 0.06 |
| ጠቅላላ ድምር | 1243 | 23.57 | 8.87 | 10.89 | 932 | 20.28 | 6.75 | 7.72 | 2035 | 22.03 | 7.89 | 8.74 |

#### 4.2.3.1 በአራት ነጥብ አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች

ከፍ ሲል በቀረበው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው የአራት ነጥብ አጠቃቀም በትክክለኛ ቦታው አለመገኘት በተናጠል ሲታይ ከፍተኛውን የስህተት ብዛት ይዞ ታይቷል:: በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ 1058 ስህተቶች ተመዝግበዋል:: ይህም በአጠቃላይ በደርሰቶች ውስጥ ከተስተናገዱት ስህተቶች መካከል 10.72 ሊሸፍን ችሏል:: አማካይ የስህተት ብዛቱ 3.83 ያህሉን የሸፈነ ሲሆን የስህተት ድግግሞሹም 4.51 ሆኖ ተገኝቷል::ይህም የሚያመለክተው የተማሪዎቹ ከፍተኛ ችግር መሆኑን ነው::

በዚህ የነጥብ አጠቃቀም ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ የተዳሰሱት ስህተቶች በርከት ያሉ ናቸው:: ከእነዚህ መካከል በአራት ነጥብ ፈንታ ሁለት ነጥብ በመጠቀም የተፈጸሙ ስህተቶች፣ በአራት ነጥብ ፈንታ ነጠላ ሰረዝን በመጠቀም የተፈጸሙ ስህተቶች፣ በአራት ነጥብ ፈንታ አንድ ነጥብን (የእንግሊዝኛውን ፉልስቶፕ) በመጠቀም የተፈጸሙ ስህተቶች እና አራት ነጥብን በተገቢው ቦታ ባለመጠቀም የተፈጸሙ ስህተቶች በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው:: ዝርዝሩን እንደሚከተለው ተመልክተነዋል::

1. በአራት ነጥብ ፈንታ ሁለት ነጥብን በመጠቀም የተፈጸሙ ስህተቶች

ተማሪዎቹ ከጻፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ በአራት ነጥብ ፈንታ ሁለት ነጥብን በመጠቀም የተለያዩ ስህተቶች የተፈጸሙ መሆኑን ነው:: ለአብነት ያህልም የሚከተሉት ቀርበዋል::

- በቤተሰብ ጥላ ስር መኖር ምንም አያሳስብም :... ሰው ምን ይለኛል ብሎ ማሰብና መጨነቅ የለም: ግን ከቤተሰብ ርቆ መኖር በብዙ መልኩ ያሳስባል: ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች ማድረግ አሳሳቢ ነው(:)
- አንድ ሰው መጻፍና ማንበብ ካልቻለ አንድን ሀገር ሙሉ በሙሉ ማስተዳደር አይችልም(:)
- ጥሩ ተማሪ ታላቆቹ ያዘዙትን ያደርጋል: መምህሩን ያከብራል: በዚህም የተነሳ በቤተሰቡና በጎረቤቱ የተወደደ ይሆናል(:)

- የደን ሀብት ጥቅም ለሰው ልጆች እጅግ በጣም ብዙ ነው(:) ምክንያቱም የሰው ልጅ ያለደን በምድር ላይ መኖር አይቸልም(:) ደን የምንለው የእያንዳንዱ አረንጓዴ ተክል ጥቅም ሆኖ ለሰው ልጆች የሚሰጠው ጥቅም አቻ አይገኝለትም(:)

## 2. በአራት ነጥብ ፈንታ ነጠላ ሰረዝን በመጠቀም የተፈጸሙ ስህተቶች

ተጠኚ ተማሪዎች በጻፏቸው የተለያዩ ደርሰቶች ውስጥ በአራት ነጥብ ፈንታ ነጠላ ሰረዝን በመጠቀማቸው የተነሳ ስህተቶቸ ተፈጽመዋል::* ለአስረጅነት ያህል የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል::

- ጥሩ ተማሪ በሰዓቱ ትምህርት ቤት ይሄዳል፣ በትምህርት ቤት መልስ ደብተሩን ያጠናል፣ የቤት ስራውን ይሰራል፣ ከትምህርት ቤት አይቀርም፣ ከአስተማሪው ጋር አይጣላም፣ መጥፎ ነገሮችንም አያስብም ወዘተ(፣)- ጥሩ ስነ ምግባር ያለው ተማሪ በትምህርቱ ስኬታማ ይሆናል፣ ካሰበበት ይደርሳል፣ አላማውንም ያሳካል(፣)
- አንድ ጓደኛ ነበረችኝ(፣)
- ሸንኩርት ከትፎ መጨመር ነው(፣)

ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ውስጥ ቅንፎቹ ( ) የሚያመለክቱት ተማሪዎቹ በአራት ነጥብ ፈንታ ነጠላ ሰረዝን በመጠቀማቸው የተነሳ ስህተቶች መከሰታቸው ነው:: ስለሆነም በቅንፎቹ ውስጥ የተመለከቱትን ነጠላ ሰረዞች በአራ ነጥብ በመተካት ስህተቶቹ ማቃናት ይቻላል:: ከፍ ሲል በአስረጅነት የቀረቡት አረፍተ ነገሮች በአራት ነጥብ አጠቃቀም ላይ ከታዩት ስህተቶች በተጨማሪ ሌሎች ስህተቶችም እንዳሉባቸው መገንዘብ ይቻላል::

## 3. በአራት ነጥብ ፈንታ "የእንግሊዝኛውን ፉልስቶፕ" በመጠቀም የተፈጸሙ ሰህተቶች

ተማሪዎች በጻፏቸው ድርሰቶቸ ውስጥ በአራት ነጥብ ፈንታ የእንግሊዝኛውን ቋንቋ ስርዓተ ነጥብ ከአማርኛው ጋር በማጋጨት ሲጠቀሙ ተስተውለዋል:: ይህም

ለስህተት የዳረጋቸው መሆኑን መረጃው ያሳያል:: ለአብነት ያህል የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች መመልከት ይቻላል::

- የሽሮ ወጥ የሁሉም ሰው የአሰራር ዘዴ ይለያያል(.) አንድ አንዱ ዝምብሎውሃ አፍልቶየሚሰራ ሲሆን፣ አንድ አንዱ ደግሞ ትክትክ አድርጎ አሳምሮ መስራት ይወዳል:: በደንብ የተሰራው ከስጋ ይበልጣል (.)

- አንድ ሰው በበቂ ሁኔታ ተምሮና ከብዙ ፈተና በትጋት አልፎ ያን ሁሉ ሲያልፍ እንኳንም ተማርኩ በማለት እራሱን ያጽናናል (.)

- ከኤች አይ ቪ ኤድስ ነፃ መሆን አለብን (.) ለወደፊቱም በሀገራችን ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ወጣቶች … እንከላከል (.)

- ጎደሬለምግብነት የሚያገለግል ነው(.) ይሁን እንጂ በአብዛኛው ሰው የማይታወቅ ነው (.)

ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ውስጥ ተማሪዎቹ በአራት ነጥብ ፈንታ የእንግሊዝኛውን ፉልስቶፐ(.) ያለ አግባብ በመጠቀማቸው የተነሳ ስህተቶቸ ተከስተዋል:: ስለዚህ በቅንፎቹ ውስጥ የተጠቆሙትን የእንግሊዝኛውን ስርዓተ ነጥብ በአራት ነጥብ በመተካት ስህተቱን ማስተካከል ይቻላል::

## 4. አራት ነጥብን በመግደፋቸው የተነሳ የተፈጸሙ ስህተቶች

ተማሪዎች በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በአረፍተ ነገሮች መቋጫ ላይ መገኘት የነበረበትን አራት ነጥብ በመግደፋቸው የተነሳ በርካታ ስህተቶቸ እንደተፈጸሙ ለማየተ ተችሏል:: ለአብነት ያህልም የሚከተሉት አንቀጾች እና አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል::

- እኔ በበኩሌ ከቤተሰብ ርቆ መኖርን ሞት አድርጌ ነው የማየው ( ) ተወልጄ ያደኩት ደቻ ወረዳ ሞድዮ ቀበሌ ነው ( ) ሁለት ወንድም ፣ አንድ እህት እና ሀብታም አጎት አለኝ ( ) ሞድዮ በጣም እሩቅ ነው ( ) አሁን እኔ ሳልበላ እየዋልኩና እያደርኩ ብታዩኝ ቋንጣ ሁኜ ቦንጋ እዮኖርኩ ነው ( ) የዚህ ሁሉ ምክንያት ከቤተሰብ ርቆ መኖር ነው ( )

- ትምህርት ብዙ ጥቅሞች ሊያስገኝ ይችላል( ) ያለ ትምህርት ማወቅ የሚቻል አይመስለኝም( ) በእርግጥ በሀገራችን ያልተማረ ሰው ጥቂት ነው በይባልም አሁን አሁን የትምህርት ጥቅም እየታወቀ መሆኑን መገመት አያዳግትም( )
- ትናንት ልጆች አባታቸውን ቀብረዋል( ) ዛሬ ግን የተገላቢጦሽ አባቶች ልጆቻቸውን መቅበር ጀምረዋል( )
- የሴት ልጅ ግርዛት የሚያስከትለው ጉዳት አይታወቅም ነበር ( ) አሁን ግን ጉዳት እንደሚያወጣ ታውቋል( )
- ጓደኛዬ በትምህርቷ ደካማ ነበረች( ) ... እኔ ሚኒስትሪ ተፈትኜ ውጤት መጣልኝ ( ) አልፌ ወደ እዚህ መጣሁ( ) እሷ ግን አላለፈችም ( ) ከእህቴ በላይ እወዳታለሁ ( )

ከፍ ሲል በቀረቡት ምሳሌዎች ውስጥ የሰፈሩት ቅንፎች( ) የሚያመለከቱት በአረፍተ ነገሮቹ መጨረሻ አራት ነጥቦች መግባት ሲገባቸው የተገደፉበትና ከዚህም የተነሳ ስህተቶች የተፈጸሙባቸውን ቦታዎች ነው።*

#### 4.2.3.2 በነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች

ነጠላ ሰረዝ የሚዘረዘሩ ነገሮችን ጥገኛ ሀረጋትን፣ ተጣማሪዎችን እና የመሳሰሉትን ለመለየት አገልግሎት ላይ የሚውል የስርዓተ ነጥብ አይነት ነው። ይሁን እንጅ ተማሪዎቹ በጻፏቸው ደርሰቶች ውስጥ በነጣላ ሰረዝ አጠቃቀም ጉድለት ምክንያት የተለያዩ ስህተቶች ተፈጽመዋል። ተማሪዎቹ ስህተቶችን የፈጸሙት በተሳሳተ መንገድ ሁለት ነጥብን በመጠቀም እና በተገቢው ቦታ መግባት የነበረበትን ነጠላ ሰረዝ በመግደፍ ነው።

በጥናቱ በቀረበው መረጃ መሰረት በአጠቃላይ 932 የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህተቶች ተፈጽመዋል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 9.44% ሲሆን አማካይ ስህተቱም 3.38 ሆኗል። የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 3.97 ሊሆን ችሏል።

ስለሆነም ይህ ንዑስ የስህተት ምድበ ከአራት ነጥብ ቀጥሎ በርካታ የስህተት ብዛት የተመዘገበበት ነው:: ከዚህ በታች የቀረቡት አንቀጾችና አረፍተ ነገሮች በምሳሌነት ቀርበዋል::

- በአካባቢያችን ካሉ ሰፈራ ጣቢያዎች የሚመጡት እንደ ድንች(:) ካሮት(:) ቀይ ስር(:) በርበሬ(:) ቲማቲም(:) ኦቾሎኒ(:)… የመሳሰሉት ናቸው::
- … የተለያዩ የዱር እንስሳት መኖሪያ(:) ለቤት መስሪያ(:) ንፁህ አየር ለማግኚያ(:) ዝናበ ለመሳብ እና ለመሳሰሉት

ከቀረቡት ምሳሌዎች መረዳት የተቻለው በነጠላ ሰረዝ ፈንታ ሁለት ነጥብን በማስገባት (በተሳሳተ መንገድ ሁለት ነጥብን በመጠቀም) ስህተቱ ሊፈጸም እንደቻለ ነው:: ስለዚህ ከላይ በቀረቡት አጠቃቀሞች የተነሳ የተፈጸሙትን ስህተቶች ለማስተካከል ሁለት ነጥቡን አስወገዶ ነጠላ ሰረዝን በመጠቀም ማስተካከል ይቻላል::

#### 4.2.3.3 በጥያቄ ምልክት አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች

የጥያቄ ምልክት አጠቃቀም ስህተት እንደ ሌሎቹ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ቁጥሩ የገዘፈ ባይሆንም ወደ 13 የሚጠጉ ስህተቶቸ ተመዝግበውበታል:: ይህ ቁም ነገር የሚገባ ስህተት ባይሆንም ስህተቱ መኖሩን ግን የሚያመለክት ነው:: ይህም በመቶኛ ሲሳላ 0.13 ሲሆን አማካይ ስህተቱም 0.05 ሆኗል:: የስህተት ድግግሞሹም 0.06 ሊሆን ችሏል:: ለአስረጅነት የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል::

- ገንዘብ ባይኖር የተፈለገው ነገር ከየት ይገኛል( )
- እንዴት መማር መታደል ይሆናል( )
- አውራዳ የት ነው( ) ብሎ አለኝ … አታውቀውም( ) ብዬ ጠየኩት::
- አንተ ወደ የት ነው የምትሄደው( ) አለኝ ጓደኛዬ

ከላይ በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ቅንፎቹ( ) የሚያመለክቱት ጥያቄ ምልክቶች የተገደፉ መሆናቸውን ነው:: በዚህም የተነሳ ስህተቶች ተፈጥረዋል::

#### 4.2.3.4 በትዕምርተ አንክሮ አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች

ተማሪዎች በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በትዕምርተ አንክሮ አጠቃቀም ጉድለት ምክንያት ስህተቶች መፈጸማቸውን ለመረዳት ተችሏል:: በመረጃው መሰረት በጠቅላላ 32 የትዕምርተ አንክሮ አጠቃቀም ስህተቶች ተመዝግበዋል:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 0.32% የሸፈነ ሲሆን አማካይ ስህተቱም 0.12 ሊሆን ችሏል:: አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 0.14 በመሆን ተመዝግቧል:: በድርሰት መልመጃዎቹ የታየው፣ ተማሪዎቹ የትዕምርተ አንክሮ አጠቃቀምም ልምድ የሌላቸው መሆኑን ነው:: ለአብነት ያህልም የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች መመልከት ይቻላል::

- በጣም ይገርማል( ) ዝም ብሎ ተቀምጦ የሰውን ብቻ መመኘት( ) ግን ለምን?
- ·ወይኔ( ) የመንገዱ ርቀት የፀሀዩ ቃጠሎ( )
- እባክሽ ጓደኛዬ( ) ተመልሰሽከእኔ ጋር ኑሪ::
- ምን አለ( ) የልጅነት ትዝታ ተመልሶ ቢመጣ( )
- አቦ( ) እኔ ተመልሼ ልጅ ሆኜ በተጫወትኩት ደስ ይለኛል( )

እነዚህ ከላይ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ተብለው በቅንፍ በተመለከቱት ቦታዎች ላይ ትዕምርተ አንክሮ ቢገባባቸው አረፍተ ነገሮቹ ሊስተካከሉ ይችላሉ::

#### 4.2.3.5 በትዕምርተ ጥቅስ አጠቃቀም ላይ የታዩ ስህተቶች

ትዕምርተ ጥቅስን በተገቢው ቦታ ካለመጠቀም የተነሳ በአጠቃላይ ተማሪዎቹ በጻፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ ከተቆጠሩ 9869 ስህተቶች ውስጥ 140 ያህሉ የተቆጠሩት በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ውስጥ ነው:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 1.42% ነው:: አማካይ የስህተት ብዛቱ 0.51 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 0.06 ሆኗል::

ስለሆነም የትዕምርተ ጥቅስ አጠቃቀም ስህተት ከአራት ነጥብ እና ከነጠላ ሰረዝ የአጠቃቀም ስህተት ቀጥሎ ከፍተኛ ቁጥር የታየበት ነው::

በትዕምርተ ጥቅስ አጠቃቀም ውስጥ የተመዘገቡ ስህተቶችን በሙሉ በአስረጅነት ማቅረብ አስቸጋሪ ነው:: በመሆኑም ስለ ስህተቱ ለመገንዘብ እንዲቻል የሚከተሉት በምሳሌነት ቀርበዋል::

- አንድን ሀገር ለማሳደግም ሆነ የአንድን ማህበረሰብ ችግር ለመቅረፍ ሰፊ እውቀት የሌለው ሰው በጨለማ ውስጥ ገብቶ እንደሚሮጥ ሊሆን ይችላል:: ለእዚህም ሊሆን ይችላል( ) ትምህርት ያስከብራል ሀገርን ያኮራል( ) የሚባለው::
- --- መቼም የልጅ ነገር እንደሚታወቀው( ) ልጅ ያቦካው ለእራት አይበቃም( ) እንደሚባለው ሁሉ እኔና ጓደኞቼ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ያለኝን ቁልፍ ሁሉ በላኝ:: መልስልኝ መጣ::( ) መጀመሪያ ስንጫወት ተስማምተህ አይደለም እንዴ የጀመር ነው?( ) ብሎ አለኝ::
- … ለእንደ እነዚህ አይነቶቹ ደግሞ( ) ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ( ) የሚባለው አባባል ይበልጥ ሊጠቅማቸው ይችላል::
- ( ) መማር መቃጠል ነው( ) የሚሉ ሰዎች አሉ:: ይህ የተሳሳተ አመለካከት ነው::
- ከእለታት አንድ ቀን መንገድ ስሄድ መሽቶብኝ አየኝና እንዳያናግረኝ ጥለኛዬ ነው:: እንዳይተወኝ አብሮ አደጌ ነው:: የፈለገውን ይበለኝ ብሎ( ) አንተ የእኔው ከመሸ በኋላ ወደ የት ነው የምትሄደው( ) አለኝ:: ( ) ማነው ደግሞ የሚያውቀኝ( ) ብዬ ግርም ብሎኝ ዘወር ብዬ ሳየው አብሮ አደጌ እሱ ነው::

ከፍ ሲል በቀረቡት አንቀፆችና አረፍተ ነገሮች ውስጥ በሚገኙት ቅንፎች የትዕምርተ ጥቅስ አጠቃቀም ጉድለት በመፈጠሩ የተነሳ ስህተቶቸ ተፈጽመዋል:: ስለዚህ ትዕምርተ ጥቅሶች በመገደፋቸው ሳቢያ የተፈጸሙትን ስህተቶች ምልክቱን በመጠቀም እንደሚከተለው ማስተካከል ይቻላል::

“ትምህርት ያስከብራል ሀገርን ያኮራል::” “ልጅ ያቦካው ለእራት አይበቃም::” “መጀመሪያ ስንጫወት ተስማምተህ አይደለም እንዴ የጀመርነው?” ብሎ አለኝ:: “ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ” “መማር መቃጠል ነው::” “አንተ የእኔው

ከመሸ በኋላ ወደ የት ነው የምትሄደው?” አለኝ:: “ማነው ደግሞ የሚያውቀኝ?” ብየ ግርሞ ብሎኝ ዞወር ብዬ ሳየው አብሮ አደጌ እሱ ነው::

በአጠቃላይ በትዕምርተ ጥቅስ የተቀመጡት ሀሳቦቸና አባባሎች የተነገሩት በሌሎች ሰዎች ነው:: በመሆኑም እንደነዚህ ያሉ አፃፃፎች በጥቅስ ውስጥ መቀመጥ ሲገባቸው ባለመቀመጣቸው ስህተቶች ተፈጽመዋል::

እነዚህ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ግን ከተጠኚዎች የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪነት ብቻ የሚመነጩ ናቸው ማለት አስቸጋሪ ነው:: ሆኖም በሁለተኛ ቋንቋ የተጻፉ ድርሰቶችን የማንበብና የመጻፍ ልምድ እጥረት በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀማቸው ላይ የተወሰነ ተፅዕኖ እንዳሳደረ መገመት ይቻላል::

### 4.3.1 ለተማሪዎች የቀረቡ መጠይቆች ምላሽ

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች ለስህተት መከሰት መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱትን ነጥቦች መነሻ በማድረግ ተተንትነዋል::

#### 4.3.1.1 ውስጠ ቋንቋ ተፅእኖ

ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶት ውስጥ ለተፈጸሙት ስህተቶች ምንጭ ይሆናሉ ተብለው ከሚገመቱት መላምቶች መካከል የውስጠ ቋንቋ ተፅእኖ አንዱ ነው:: ከተዛማጅ ጽሁፉ ለመገንዘብ እንደተቻለው ውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ ከታላሚው ቋንቋ ውስብስብነት የተነሳ ተማሪዎቹ የቋንቋውን አወቃቀር ስርዓት እና አጠቃቀም በሚገባ ካለማወቃቸው አልያም ደግሞ የቋንቋውን ስርዓት ከለመዱ በኋላ የታላሚውን ቋንቋ አጠቃላይ ህግ በማስፋፋት ለመጠቀም ሲፈልግ ወይም በቋንቋው ህግ ውስጥ አጥርቶ ያልያዘው ህግ ሲኖርና ያንን ህግ ተግባራዊ ለማድረግ ሲሞክር የሚከሰት የሰህተት አይነት ነው (Brown፣ 1994፤ Litlewood፣ 1994)::

ስለሆነም በከፍኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የአማርኛውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት (ህግ) በተገቢው ሁኔታ ባለማወቅ እንዲሁም ከአሁን ቀደም ከሚያውቁት ሰዋስዋዊ ስርዓት በመነሳት በዚያው መንገድ ለመጠቀም ሙከራ ሲያደርጉ የሚፈጸሙ ሰህተቶችን በውስጠ ቋንቋ ተፅእኖ ስር በመመልከት ትንተናው ተካሂዷል::

**ሠንጠረዥ 10:- ውስጠ ቋንቋ ተፅእኖን በተመለከተተፅእኖን በተመለከተ ለተማሪዎች ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾ**

| የመጠየቁ ቁጥር | መጠይቅ | በመለኪያዎች መሰረት የመላሾች ብዛት | | | | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 | |
| 1 | በፅሑፍ ውስጥ የተለያዩ ስህተቶችን የምፈፅምበት ምክንያት የአማርኛ ቋንቋን ሰዋስዋዊ ስርዓት ባለማወቁ ነው:: | 27 | 41 | 42 | 28 | 2.49 |
| 2 | እና፣ ስለሆነም፣ ስለዚህ፣ ነገር ግን ወዘተ. የሚሉትን አያያዥ ቃላት በፅሑፍ ውስጥ በትክክል መጠቀም አልችልም:: | 63 | 43 | 21 | 11 | 3.14 |
| 3 | በአማርኛ ቋንቋ አረፍተ ነገሮችን ስጽፍ በተዳጋጋሚ ስህተት የሚፈፅምባቸውና ለማረም ያልቻልኳቸው ሰዋስዋዊ ጉድለቶች አሉ:: | 61 | 47 | 18 | 12 | 3.12 |
| 4 | በአማርኛ አረፍተ ነገር ውስጥ የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽን (ግስን) ቦታ ለመለየት አልችልም:: | 29 | 45 | 30 | 34 | 2.50 |
| 5 | በፅሁፍ ጊዜ ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን ለይቶ ለመጠቀም እቸገራለሁ:: | 11 | 20 | 31 | 76 | 1.75 |

ከላይ በሰንጠረዡ በተመለከተው የአንደኛ ተራ ቁጥር ጥያቄ መሰረት “በጽሑፌ ውስጥ የተለያዩ ስህተቶችን የምፈጽምበት ምክንያት የአማርኛ ቋንቋን ሰዋስዋዊ ስርዓት ባለማወቁ ነው” ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ በአማካይ ሲሰላ 2.49 ነው:: ከዚህም የምንረዳው ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓትን የሚያውቁ መሆናቸውን ነው:: ይህ ምላሽ የሚያሳየው በቋንቋው ሰዋስዋዊ ስርዓት የተነሳ ስህተት አንፈጽምም ማለታቸውን ነው:: ሆኖም የአማርኛ ቋንቋን ስዋስዋዊ ስርዓት ካለማወቅ የተነሳ የተለያዩ ስህተቶች መኖራቸውን በስህተት አይነቶች ማረጋገጥ ተችሏል:: ስለዚህ ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ ትክክልኛነት የጎደለው ይመስላል::

በተራ ቁጥር 2 ለቀረበው ጥያቄ ማለትም "እና፣ ስለዚህ፣ ስለሆነም፣ ነገር ግን ወዘተ. የሚሉትን ቃላት በፅሑፍ ውስጥ በትክክል መጠቀም አልችልም" ለሚለው ጥያቄ ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ አማካይ 3.14 ሲሆን፣ ይህም በሀሳቡ መስማማታቸውን ያመለክታል:: ወይም አያያዥ ቃላትን በትክክል የመጠቀም ችግር አለባቸው ማለት ነው:: ይህ አይነቱ ስህተት ቀደም ሲል በተካሄደው የድርሰት ስህተት ትንተና የተረጋገጠ ነው:: በዚህ አይነቱ ሁኔታ ከተከሰቱት ስህተቶች ውስጥም "ቆሎ ፀሐይ ዝናብ የሚፈራ ተክል ነው::" "በዓለማችን ውስጥ የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች መኖራቸው እርግጥ ነው:: ይሁን እንጂ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ደን በመሆኑ በሁሉም ዜጎች ዘንድ የታወቀ ነው::" የሚሉት ከብዙ በጥቂቱ ተጠቃሾች ናቸው::

በቀጣይ የቀረበው ጥያቄ "በአማርኛ ቋንቋ አረፍተ ነገሮችን ስጽፍ በተደጋጋሚ ስህተት የምፈጽምባቸውና ለማረም ያልቻልኳቸው ሰዋስዋዊ ጉድለቶች አሉ" ለሚለው 3.12 አማካይ ውጤት ተገኝቷል:: ይህም የሚያሳየው ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ አረፍተ ነገሮችን ሲጽፉ በተደጋጋሚ ስህተት የሚፈጽሙባቸው ሰዋስዋዊ ጉደለቶች እንዳሉ ነው:: ይህንን ሁኔታ ቀደም ሲል በተራ ቁጥር አምስት ላይ በቀረበው ጥያቄ ማረጋገጥ ተችሏል:: ይህ አይነቱ ተደጋጋሚና ለማረም ወይም ለማስተካከል የሚያስቸግር የስህተት አይነት በውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ አማካኝነት የሚከሰት መሆኑን Odlin (1994) ፣ Selinker (1972) ይገልጻሉ:: እነዚህ ምሁራን አክለውም ሲገልጹ በውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ አማካኝነት ከሚከሰቱ ስህተቶች አንዱ ስር ዘላቂ ስህተት ነው:: አያይዘውም ስር ዘላቂ ስህተት ማለት ከተማሪው የቋንቋ ችሎታ አንጻር ሲታይ ቋሚ በሆነ መልኩ የያዘውና በሁለተኛ ቋንቋው ሰዋስዋዊ ስርዓት (መዋቅር) ውስጥ የሌለ ነገር ግን እየተጠቀመበት ያለና ሊያርመው ወይም ሊያስተካክለው የማይችለው የስህተት አይነት ነው ይላሉ:: ይህም በድርሰታቸው ውስጥ በተደጋጋሚ የታየ አንኳር ችግር ነው::

በተራ ቁጥር አራት ማለትም በአማርኛ አረፍተ ነገር ውስጥ የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽን (ግስን) ቦታ ለመለየት አልችልም ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤቱ 2.50 ነው:: ተማሪዎቹ ከሰጡት ምላሽ መረዳት የሚቻለው በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የተለያዩ ስህተቶች እንዲፈጽሙ ምክንያት የሆነባቸው በአማርኛ ቋንቋ አረፍተ ነገር ውስጥ የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ ቦታን በትክክል ለማስቀመጥ የማይቸገሩ መሆኑን ነው::

በመጨረሻ በተራ ቁጥር አምስት ለቀረበላቸው ጥያቄ "በጽሑፍ ጊዜ ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን ለይቶ ለመጠቀም እቸገራለሁ" ለሚለው የሰጡት ምላሽ በአማካይ 1.75 ነው:: ይህ ማለት ደግሞ ነጠላ ስምን ወደ ብዙ የመለወጥ ችግር የለባቸውም ማለት ነው:: ይህ ምላሽ ከጻፏቸው ድርሰቶቸ ከተገኘው ስህተት ጋር በተወሰነ ደረጃ የሚጋጭ ነው:: ምክንያቱም በስህተት ትንተናው ጥቂት

የማይባሉ የቁጥር አለመጣጣም ስህተቶች ተስተውለዋል:: በዚህም የቋንቋ አወቃቀር ቅደም ተከተል በሚለው የስህተት ዓይነቶች ውስጥ 9.32% ተመዝግቧል::

ጠቅለል ባለ መልኩ የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖን ሊያመለክቱ ይችላሉ ተብለው በቀረቡት ጥያቄዎች አማካኝነት ተማሪዎቹ የሰጧቸው ምላሾች ለፈጸሟቸው ስህተቶች ውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ መንስኤ መሆኑን ከተገኙት መረጃዎች ማረጋገጥ ይቻላል::

#### 4.3.1.2 የመማር ማስተማር ሂደት እና የመማሪያ መሳሪያዎች

አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎችን ለስህተት ከሚያጋልጧቸው ምክንያቶች (የስህተት ምንጮች) መካከል ታላሚውን ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጁት የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የመማር ማስተማር ሂደት (የማስተማር ዘዴ) ድክመቶች እንደሆኑ በተዛማጅ ጽሑፉ ቅኝት ለመዳሰስ ተሞክሯል:: ስለሆነም የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ድክመትና የማስተማሪያ መሳሪያዎች በተገቢው ሁኔታ አለመቀረጽ ለስህተት መፈጠር በምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ:: የመማር ማስተማር ሂደት ሲባል ሰፊ ነገርን የሚይዝና ራሱን የቻለ ጥናት የሚጠይቅ ነው:: ሆኖም ይህ ጥናት ለመመርመር ወስኖ የተነሳው የተማሪዎችን ስህተት ከፅህፈት ጋር በማያያዝ በመሆኑ ለስህተቱ መፈጠር የመማር ማስተማር ሂደት መንስኤ መሆኑን ከተለያዩ ምሁራን የተሰነዘሩ ሀሳቦችን በመያዝ መጠይቁ ተዘጋጅቷል:: የመማር ማስተማር ሂደት ሲባል በቋንቋው ትምህርት ተደጋጋሚና ተከታታይነት ያለው ስራ መስራትን የሚጠይቅ ነው:: ይህን ሃሳብ አስመልክተው ምሁራን ሲገልፁ፣ አንድ በሁለተኛ ቋንቋው የሚጽፍ ተማሪ ከቋንቋው አገላለጽ ስልቶች፣ መዋቅሮች እና የመዋቅሮች አደራጃጀት ጋር ያለው የአጠቃቀም ግንኙነት ማነስ በደረጃው ለተለያዩ ስህተቶች መከሰት ምክንያት ይሆኑበታል (Conner & Kaplan፣ 1987፣ Carson፣ 2001) ::

ሠንጠረዥ 11:- የመማር ማስተማር ሂደትንና የማስተማሪያ መሳሪያዎችን በተመለከተ

ለቀረቡ ጥያቄዎች በተማሪዎች የተሰጡ ምላሾች

| የመጠይቁ ቁጥር | መጠይቅ | በእስኬሉ መሰረት የመላሾች ብዛት | | | | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 | |
| 1 | በአማርኛ ቋንቋ ስጽፍም ሆነ ስናገር ለምፈጽማቸው ስህተቶች ከመምህሬ ማስተካከያ (እርማት) ይሰጠኛል:: | 51 | 35 | 26 | 26 | 2.80 |
| 7 | ለጽህፈት ክሂል መዳበር የሚጠቅሙ የተለያዩ ጽሑፎች በየጊዜው አይቀርቡልኝም:: | 78 | 51 | 9 | 0 | 3.50 |
| 16 | የመማሪያ መፅሐፍት መልመጃዎች ጽህፈትን ለማለማመድ የጎላ አስተዋጽኦ የላቸውም:: | 59 | 49 | 18 | 12 | 3.12 |
| 17 | በጽሑፌ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ስህተቶች ደጋግሜ በማንበብ ራሴ ለማረም እሞክራለሁ:: | 38 | 40 | 31 | 29 | 2.63 |
| 18 | በትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኙ የስነ ፅሑፍና የድራማ ክበባት እሳተፋለሁ:: | 41 | 39 | 25 | 33 | 2.63 |
| 19 | 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ከመግባቴ በፊት በቂ የጽህፈት ልምምድ ባለማድረጌ በአሁን ጊዜ ድርሰት ስጽፍ ያሳደረብኝ አሉታዊ ተጽእኖ ከፍተኛ ነው:: | 92 | 36 | 7 | 3 | 3.57 |

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ መሰረት "በአማርኛ ቋንቋ ስጽፍም ሆነ ስናገር ለምፈጽማቸው ስህተቶች ከመምህሬ ማስተካከያ (እርምት) ይሰጠኛል" ለሚለው የተሰጠው ምላሽ አማካይ 2.80 መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል:: ይህ ማለት ተማሪዎቹ በሀሳቡ የማይስማሙ መሆናቸውን ያሳያል:: በዚህም ለስህተታቸው ማስተካከያ ወይም እርማት ከመምህሮቻቸው የማይሰጣቸው መሆኑን ያሳያል:: ስህተትን ለመቀነስ ከሚያስችሉ መፍትሄዎች አንዱ፣ ለስህተት እርማት መስጠት

በመሆኑ ይህ አለመከናወኑ ከመማር ማስተማር ሂደቱ ውስጥ የታየ ደካማ ጎን ነው:: ይህንን መተመለከተ Ferris (1995) እና Lee (1997) እንደሚገልጹት ለተማሪዎች በተናጠልም ሆነ በቡድን ሰዋስዋዊና የይዘት ምጋቤ ምላሽ መስጠት የስህተት ምንጮችን ሊቀንሱ ይችላሉ:: ከምሁራኑ ሀሳብ የምንረዳው በስህተት እርማት ጊዜ ምጋቤ ምላሽ መስጠት የጎላ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ነው::

በሁለተኛ ደረጃ ለተማሪዎቹ የቀረበው "ለፅህፈት ክሂል መዳበር የሚጠቅሙ የተለያዩ ፅሁፎች በየጊዜው አይቀርቡልኝም" የሚል ነው:: የተሰጠውም ምላሽ በአማካይ 3.50 መሆኑን ያመለክታል:: ይህ ማለት ተማሪዎች በሀሳቡ የተስማሙ መሆናቸውን ያሳያል:: ስለዚህ የተለያዩ ጽሑፎች በግብዓትነት የማይቀርቡላቸው ከሆነ ተማሪዎቹ ለተለያዩ ስህተቶች መዳረጋቸው (መጋለጣቸው) የማይቀር ነው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ Myles (2002፣1) እንደገለጹት ተማሪዎች እንዲጽፉ ተገቢ የሆነ የታላሚው ወይም የተተኳሪው ቋንቋ የጽሑፍ ግብዓት ሊቀርብላቸው ይገባል:: ይህን አይነቱን ግብዓት ማቅረብ በተተኳሪው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋትን በትክክል ለመጻፍ መነሻ ሀሳብ ይሆናቸዋል:: ሆኖም ተማሪዎች በቋንቋው አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የሚጠቀሙትን አይነት የተጻፉ ጽሑፎች በግብአትነት የማያገኙ ከሆነና ራሳቸው ብቻ እንዲጽፉ ከተደረገ የሚጽፏቸው ጽሑፎች ከቋንቋው ሰዋስዋዊ ስርዓት ጋር የተፋለሱ መሆኑ አያጠራጥርም ይላሉ:: በዚህ ሀሳብ መሰረት ተማሪዎቹ እንዲጽፉ ማድረግ ብቻውን በቂ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል:: ምክንያቱም በቋንቋው አፋቸውን ከፈቱ ተማሪዎች የተጻፉ ጽሑፎች ከቀረበላቸው እነዚያን በማስመሰል ለመጻፍ ሲሞክሩ ስህተታቸውን እያረሙ ወይም እያስተካከሉ ስለሚሄዱ ነው::

በቀጣይ የቀረበው "የመማሪያ መፅሐፍት መልመጃዎች ጽህፈትን ለማለማመድ የጎላ አስተዋጽኦ የላቸውም" ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በአማካይ 3.12 ነው:: ይህም የሚያሳየው ተማሪዎቹ በሀሳቡ የተስማሙ መሆኑን ነው:: በዚህም መሰረት በመማሪያ መፅሐፍት ውስጥ ያሉ መልመጃዎች ጽህፈትን ለማለማመዴ የጎላ አስተዋጽኦ የላቸውም:: ስለሆነም የመማር ማስተማሩን ሂደት በበጎ ጎኑ እንዳይጠቀስ አድርጎታል::

በመሆኑም የመማሪያ መፅሐፈች የመልመጃ አዘጋጃጀትና የመማር ማስተማር ሂደት ድክመቶች ተጠኚ ተማሪዎችን ለስህተት መዳረጋቸው የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

ሌላው ለተማሪዎቹ የቀረበው ጥያቄ “በፅሑፌ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ስህተቶች ደጋግሜ በማንበብ እራሴ ለማረም እሞክራለሁ” የሚል ነው:: ከላይ ለቀረበው ሀሳብ ከተማሪዎች የተሰጠው ምላሽ በአማካይ 2.63 ሆኗል:: ይህ ማለት ተማሪዎች በራሳቸው ጽሑፍ ላይ የሚገኙ የተለያዩ ስህተቶችን ራሳቸው ለማረም ወይም ለማሰተካከል የተለያዩ ጥረቶች የማያደርጉ መሆናቸውን ነው:: ይህ መሆኑ ደግሞ በፅሑፎቻቸው ላይ ለሚከሰቱ የተለያዩ ስህተቶች መጨመር የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል:: በመሆኑም የራስን ስህተት ራስ ማረም ወይም ማስተካከል ተማሪው በእለት ተእለት የመማር ሂደቱ (የመማር ስልቱ) ውስጥ አንዱ አድርጎ ሊተገበረው የሚገባ መሰረታዊ ነጥብ ነው:: ከላይ የሰፈረውን ሀሳብ በተመለከተ Zamel (1998) እና Cumming (1989) እንደገለጹት ተማሪው በራስ በመተማመንና በእርግጠኝበት ላይ የተመረኮዘ እርማት ወይም ማስተካከያ መስጠት ከሚችልበት ደረጃ መድረሱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: ተማሪው መበረታታት ያለበት ራሱ የሰራውን ስህተት ራሱ መርምሮና መዝኖ ለማስተካከል ከሚችልበት ደረጃ ማድረስ ነው ይላሉ:: በትምህርት ቤት ውስጥበሚገኙ የስነ ፅሑፍና የድራማ ክበቦች እሳተፋለሁ” ለሚለው ሀሳብ ከተማሪዎች የተሰጠው ምላሽ በአማካይ 2.63 መሆኑ ተረጋግጧል:: ይህ ማለት ተማሪዎቹ በኮሌጅ ውስጥ በሚገኙ የስነ ጽሑፍና የድራማ ክበባት የማይሳተፉ መሆናቸውን  የሚያሳይ ነው:: ይሁን እንጂ በስነ ጽሁፍና ድራማ ክበባት መሳተፋቸው ተማሪዎች ከአፍ ፈቶች ጋር የመገናኘት እድላቸው የሰፋ በመሆኑ ከቋንቋው ሰዋስዋዊ ህግ ጋር ይላመዳሉ:: በተጨማሪም በአፍ ፈት ተማሪዎች የተጻፉ ጽሁፎችን የማንበብ እድል ስለሚገጥማቸው በሂደት ስህተቶቻቸውን በራሳቸው እያረሙ ይሄዳሉ:: ይህ መሆኑ ደግሞ የመማር ማስተማር ሂደቱን በበጎ ጎኑ እንዲጠቀስ ያደርገዋል::

በመጨረሻ የቀረበው “ሀሳብ ኮሌጅ ከመግባቴ በፊት በቂ የጽህፈት ልምምድ ባለማድረጌ በአሁኑ ጊዜ ድርሰት ስጽፍ ያሳደረብኝ ተጽእኖ ከፍተኛ ነው::” የሚል ነው:: ለዚህም የሰጡት ምላሽ በአማካይ 3.57 ነው:: ለዚህም ተማሪዎቹ በሀሳቡ የሚስማሙ መሆናቸውን በምላሾቻቸው አረጋግጠዋል:: በመሆኑም ተማሪዎች በቅድመ ኮሌጅ ቆይታቸው በቂ የሆነ የጽህፈት ልምምድ አለማካናወናቸው የስህተታቸውን መጠን ከፍ ሊያደርገው ችሏል ማለት ነው:: ተማሪዎች በተተኳሪው ቋንቋ አዘውትረው በቂ የጽህፈት ልምምድን ካልፈጸሙ ስህተቶቻቸውን ለመቀነስ ያስቸግራል:: የጽህፈት ልምምድን ባዘወተሩ ቁጥር የስህተት መጠናቸው እየቀነሰ ይሄዳል:: ይህ ካልሆነ ግን የስህተት

መጠናቸው እንዳለ ይቀጥላል ወይም እየጨመረ ይሄዳል::  እንደ ሌሎች ክሂሎች ሁሉ የጽህፈት ክሂልም ማደግ የሚችለውና ከሰዋስዋዊ ስህተት ሊጸዳ የሚችለው ሁል ጊዜ በሚከናወን የጽሁፍ ልምምድ አማካኝነት ነው ይላሉ::

ከላይ በሰንጠረዡ ለተማሪዎች ከቀረቡት መጠይቆች የተገኘው አጠቃላይ ውጤት እንደሚያመለክተው የተለያዩ የጽሑፍ ልምምዶች አለማድረግ፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚገኙ የስነ ጽሑፊና የድራማ ክበባት አለመሳተፉ፣ የጽህፈት ልምምድ አለማድረግ እና በመማሪያ መፅሐፍት  ውስጥ የሚገኙ መልመጃዎች ጽህፈትን ለማለማመድ ያላቸው አስተዋጽኦ የጎላ አለመሆኑን የመማር ማስተማር ሂደቱ ለስህተት መከሰቻ ምክንያት እንዲሆን አድርገውታል::

#### 4.3.1.3 ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች

ቀደም ብለው ከተገለጹት ሁለት ንዑሳን ክፍሎች ተማሪዎቹ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው ከታሰቡት የስህተት ምንጮች በተጨማሪ የማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ተጽእኖ ሰልጣኞቹ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች የስህተት መከሰቻ ምንጮች ሊሆኑ እንደሚችሉ ተገምቷል:: በዚህም መሰረት Norish (1992፣18) እንደገለጹት አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ለቋንቋው አሉታዊ አመለካከት የሚኖራቸው ቋንቋውን የመልመድ ፍላጎታቸው ስለሚቀንስ ስህተት የመፈጽም እድላቸው ሊሰፋ ወይም ሊጨምር ይችላል:: ነገር ግን ተማሪዎቹ ለሁለተኛ ቋንቋ አወንታዊ አመለካከት ካላቸው ቋንቋውን የመማርና የማወቅ ፍላጎታቸው ሰለሚጨምር ስህተት የመስራት እድሉ ሊቀነስ ይችላል:: በተጨማሪም የተማሪዎቹ ማህበራዊ መቼት ማለትም በአካባቢው ያለው ማህበረሰብ ለታላሚው ቋንቋ የሚኖረው አመለካከት ተማሪዎቹ ቋንቋውን በመማር ሂደት ላይ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር እንደሚችል ምሁራን ይጠቁማሉ::

ከፍ ሲል ከቀረቡትና መሰል ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ዕንሰ ሀሳቦች አንጻር በከፍኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ለመዳሰስ ተሞክሯል:: በዚሁም መሰረት የማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ተጽእና ተማሪዎቹ ለሚፈጽሟቸው የተለያዩ ስህተቶች ምክንያት መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ለተተኳሪዎች መጠይቆች የቀረበላቸው ሲሆን፣ ውጤቱም የሚከተለውን ይመስላል::

**ሠንጠረዥ 12:- ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች ከተማሪዎቹ የተሰጡ ምላሾች**

| የመጠይቁ ቁጥር | መጠይቅ | በእስኬሉ መሰረት የመላሾች ብዛት | | | | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 | |
| 8 | የአማርኛን ቋንቋ መማር አያስደስተኝም:: | 40 | 34 | 30 | 34 | 2.14 |
| 15 | ከከፍኛ ቋንቋ ይልቅ የአማርኛን ቋንቋ መማር የበለጠ ይጠቅመኛል:: | 26 | 41 | 36 | 35 | 2.42 |
| 20 | ከሰዎች ጋር ለመግባባት ከአማርኛ ቋንቋ ይልቅ የከፍኛ ቋንቋ መጠቀም ይቀናኛል:: | 20 | 7 | 19 | 92 | 1.67 |
| 14 | በአማርኛ ቋንቋ ስጽፍ ትክክል ላልሆን እችላለሁ እያልኩ ሁል ጊዜ እጠራጠራለሁ:: | 59 | 49 | 18 | 12 | 3.12 |

ከላይ በሰንጠረዡ በቀረቡት ጥያቄዎች መሰረት ለመጀመሪያው ማለትም "በአማርኛ ቋንቋ መማር አያስደስተኝም" ለሚለው የሰጡት ምላሽ በአማካይ 2.14 ነው:: ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋን መማር የሚያስደስታቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው:: በዚህም መሰረት ለቋንቋው አሉታዊ አመለካከት የሌላቸው መሆኑን ከሰጡት ምላሽ መረዳት ይቻላል:: ይህ አሉታዊ አመለካከት አለመኖር ደግሞ የስህተት መጠኑን ከሚቀንሱ ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ነው::

በቀጣይ ለተጠቀሰው ሀሳብ ማለትም "ከከፍኛ ቋንቋ ይልቅ የአማርኛ ቋንቋ መማር የበለጠ ይጠቅመኛል" ለሚለው የሰጡት ምላሽ በአማካይ 2.42 ነው:: ይህም የሚያመለክተው ተማሪዎቹ በሀሳቡ የማይስማሙ መሆናቸውን ነው:: ወይም ተማሪዎቹ ከአማርኛ ቋንቋ ይልቅ የከፍኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር የበለጠ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ከሰጡት ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል:: ይህ ሊሆን የቻለው ተማሪዎቹ ከአንደኛ ክፍል እስከ አራተኛ ክፍል ሁሉንም የትምህርት አይነቶች በከፍኛ ቋንቋ ስለሚማሩ በትምህርት መስጫ ቋንቋነቱ አይተውት ሊሆን ይችላል:: በመሆኑም ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን ፍላጎት አሉታዊ እንዲሆን አድርጎታል::

"ከሰዎች ጋር ለመግባባት ከአማርኛ ቋንቋ ይልቅ የከፍኛ ቋንቋ መጠቀም ይቀናኛል" ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በአማካይ 1.67 ነው:: በዚህም ምላሽ ተማሪዎቹ ከከፍኛ ቋንቋ ይልቅ የአማርኛ ቋንቋን ለተግባቦታዊ አገልግሎት የመረጡት መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ይህን ምላሽ እንዲሰጡ ካስቻሏቸው ምክንያቶች መካከል በግንባር ቀደም የሚጠቀሰው የአካባቢው ማህበረሰብ በአብዛኛው የከፍኛ ቋንቋ ተናጋሪ ቢሆንም አማርኛ ቋንቋን ለተግባቦዊ አገልግሎት ማዋል የተለመደ መሆኑ ነው::

በመጨረሻ ለቀረበው ጥያቄ ማለትም "በአማርኛ ቋንቋ ስጽፍ ትክክል ላልሆን እችላለሁ አያልኩ ሁል ጊዜ እጠራጠራለሁ" በሚል ለተሰነዘረላቸው ሀሳብ ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ በአማካይ ሲሰላ 3.12 ነው:: ይህ የሚያሳየው ተማሪዎች ስህተት እሰራለሁ እያሉ የሚጠራጠሩና የሚሰጉ መሆናቸውን ነው:: ሁል ጊዜ ይህ አይነቱ ስጋትና ጥርጣሬ ካለ ደግሞ በቋንቋው መስራት ያለባቸውን ያህል እንዳይሰሩ ይሆናሉ:: ምክንያቱም በፍርሃትና በስጋት በርካታ ስህተቶችን ሊፈጽሙ ይችላሉና:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ምሁራን የሚከተለውን ሀሳብ ይሰነዝራሉ:: ተማሪው በሚማረው የሁለተኛ ቋንቋ አጠቃቀም ላይ ያለው በራስ የመተማመን ብቃት ማነስ ለተለያዩ ስህተቶች ይዳርገዋል ይላሉ (Ferris፣ 1995፣ Edge፣ 1989)::

ጠቅለል ባለ መልኩ ተማሪዎቹ ከሰጧቸው ምላሾች በመነሳት በቂ የጽህፈት ልምምዶች አለማድረጋቸው እና በአማርኛ ቋንቋ ስንጽፍ ትክክል ላንሆን እንችላለን እያሉ መጠራጠራቸው ወዘተ. በጽሑፋቸው ውስጥ የተለያዩ ስህተቶችን ሊያስከትሉ የሚችሉ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ሁኔታዎች መሆናቸው ከሰጧቸው ምላሾች ለማረጋገጥ ተችሏል::

#### 4.3.1.4 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት (ተጽእኖ)

በአፍ መፍቻነት የዳበረ የቋንቋ ልምድ አንድን አዲስ ቋንቋ በመልመድ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በማሳደር ለተለያዩ ስህተቶች መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል:: የሁለቱ ቋንቋዎች ማለትም የቀድሞው ቋንቋ ከታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ጋር በመደባለቅ ተማሪውን ለተለያዩ ስህተቶች ሊዳርገው ይችላል:: ይህን በተመለከተ Norish (1992፣ 22) እንደገለጹት መማር የልምድ ክምችት ውጤት በመሆኑ የተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምድ ታላሚውን (አዲሱን) ቋንቋ በመማር ሂደት ላይ ጣልቃ በመግባት የስህተት ምንጭ ሊሆን ይችላል ይላሉ:: ስለሆነም በከፍኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በፃፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ ለተስተዋሉት ስህተቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት በምንጭነት ሊጠቀስ እንደሚችል ተገምቷል::

በመሆኑም በተማሪዎች ድርሰት (ጽሑፍ) ውስጥ ለተከሰቱት የተለያዩ ስህተቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት የስህተት መንስኤ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ በቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡት ምላሾቸና ከምላሾች በመነሳት የተሰጠው ትንታኔ በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል::

**ሠንጠረዥ 13:- የአፍ መፍቻ ቋንቋን ጣልቃ ገብነትን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተማሪዎቹ ምላሾችየተማሪዎቹ ምላሾች**

| የመጠይቁ ቁጥር | መጠይቅ | በእስኬሉ መሰረት የመላሾች ብዛት | | | | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 | |
| 3 | ድርሰት ስጽፍ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ጣልቃ እየገባ ያስቸግረኛል:: | 19 | 30 | 44 | 45 | 2.17 |
| 2 | ድርሰት ስጽፍ በጣም አሳጥሮ መጻፍ ያስደስተኛል:: | 28 | 46 | 46 | 18 | 2.61 |
| 4 | በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ስጽፍ ሁሉንም ተነባቢ ደምጾች በትክክል ለማስቀመጥ ያስቸግራል:: | 63 | 43 | 21 | 11 | 3.14 |
| 6 | በአማርኛ ቋንቋ ጽሑፌ ውስጥ ሳልስና ሳድስ የተባሉትን ሆሄያት በትክክል እጠቀማለሁ:: | 43 | 41 | 41 | 11 | 2.84 |
| 11 | የአማርኛ ቋንቋ አረፍተ ነገሮችን ስጽፍ የከፍኛ ቋንቋ አረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓትን ወይም ስልትን እጠቀማለሁ | 24 | 27 | 39 | 43 | 2.19 |

ከፍ ሲል በተመለከተው ሰንጠረዥ መሰረት "ድርሰት ስጽፍ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ጣልቃ እየገባ ያስቸግረኛል" ለሚለው ለሶስተኛው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤቱ 2.17 ነው:: ይህ የሚያሳየው ደግሞ እንደ ተማሪዎቹ ምላሽ ድርሰት ሲጽፉ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጣልቃ የማይገባ መሆኑን ነው:: ሆኖም ከጻፏቸው ድርሰቶችና መምህሮቻቸው ከሰጧቸው ምላሾች እንደታየው ግን የከፍኛ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ታይቷል:: ስለዚህ የሰጡት ምላሽ አግባብነት የጎደለው ይመስላል::

ቀጥሎ የቀረበው "ድርሰት ስጽፍ በጣም አሳጥሮ መጻፍ ያስደስተኛል" ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በአማካይ 2.61 ነው:: ይህም በአማርኛ ቋንቋ ጽሑፎቻቸው ውስጥ አህድሮተ ቃልን እንደማይጠቀሙ መግለጻቸውን ያሳያል:: በድርሰቶቻቸው ውስጥ በተካሄደው የስህተት ፍተሻ ግን ይህ አይነት ስህተት በሰፊው ተስተውሏል:: ለምሳሌ ፕ/ም፣ መ/ት፣ ኢ/ያ፣ መ/ሩ፣ ማ/ራዊ የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው::

"በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ስጽፍ ሁሉንም ተነባቢ ድምፆች በትክክል ለማስቀመጥ ያስቸግረኛል" ለሚለው ሀሳብ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤቱ 3.14 ነው:: ይህ ምላሻቸው የሚያረጋግጠው በሀሳቡ የተስማሙ መሆናቸውንና ሁሉንም የአማርኛ ቋንቋ ተነባቢ ድምጾች በትክክል ለመፃፍ እንደሚቸገሩ ነወ:: ለዚህም በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩትን በምሳሌነት ማየት ይቻላል:: ከእነዚህም መካከል ስፈልግ ለማለት ሲፈልግ አስተማሪ ለማለት አስተማር፣ ቲማቲም ትማትም... በመባል የተጻፉት ተጠቃሾች ናቸው::

"በአማርኛ ቋንቋ ጽሑፌ ውስጥ ሳልስና ሳድስ የተባሉትን ሆሄያት በትክክል እጠቀማለሁ" ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በአማካይ 2.84 ነው:: ይህም ሆሄያቱን (ሳልስና ሳድስን) በአማርኛ ቋንቋ ጽሑፎቻቸው ውስጥ በትክክል እንደማይጠቀሙባቸው መግለጻቸውን ያሳያል:: በድርሰቶቻቸው ላይ በተካሄደው የስህተት ፍተሻም ይህ አይነቱ ስህተት በጣም በሰፊው ተከስቶ ታይቷል:: በዚህም ምክንያት ተማሪዎቹ ሳልስን በሳድስ ቦታ ሲጠቀሙ ለተለያዩ ስህተቶች መዳረጋቸውን መረጃዎች ያረጋግጣሉ:: ይህ ስህተት ሊከሰት የቻለውም በከፍኛ ቋንቋ (እ) እና (·) የሚሉት አናባቢዎች ባለመኖራቸው ነው (ዮሐንስ፣1982)::

በከፍኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ በ(·) ቦታ አብዛኛውን ጊዜ (ኤ)ን በመተካት ስህተት እንደፈፀሙ ተስተውሏል:: ለዚህ ስህተት የዳረጋቸው ምናልባትም አፍ የፈቱበት ቋንቋ የ(·) ድምፀ ልሳን ባለመኖሩ ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም ተማሪዎቹ (·)ን ለመጠቀም በሚያደርጉት ሙከራ ስህተት እንደፈፀሙ መገመት ይቻላል::

ለመጨረሻው ጥያቄ ማለትም "በአማርኛ ቋንቋ አረፍተ ነገሮችን ስጽፍ የከፍኛ ቋንቋን የአረፍት ነገር አወቃቀር ስልትን እጠቀማለሁ" ለሚለው 2.19 አማካይ ውጤት ተገኝቷል:: ይህም የሚያሳየው ተማሪዎች በሀሳቡ የማይስማሙበትና የከፍኛ ቋንቋ አረፍተ

ነገር አወቃቀር ስልትን በአማርኛ ጽሑፋቸው ላይ እንደማይጠቀሙ ነው:: ነገር ግን በተቃራኒው የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የሰጡት ምላሽ የሚያረጋግጠው ተማሪዎቹ በጽሑፎቻቸው ውስጥ የከፍኛ ቋንቋ የአረፍተ ነገር አወቃቀር እንደሚጠቀሙ ነው:: በዚህም መሰረት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጽእኖ በአማርኛ ቋንቋ ጽሑፎቻቸው ላይ የተለያዩ ስህተቶችን ሊያስከትል ችሏል::

በሠንጠረዥ አስራ ሶስት ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሊጽፉ ሁሉንም ተነባቢ ድምጾች በትክክል አለማስቀመጥ፣ ሳልስና ሳድስ ሆሄያትን በትክክል አለመጠቀም እና በአማርኛ ቋንቋ ጽሑፍ ውስጥ ያልተለመዱ አህጽርኦተ ጽሑፍን መጠቀም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ለስህተት መከሰቻ ምንጭ እንደሆነ አድርገውታል::

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳብ

በዚህ ምዕራፍ ስር የጥናቱ ግኝት እና ከጥናቱ ጋር የተዛመዱ አስተያየቶች በቅደም ተከተል ይቀርባሉ::

### 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ሁለት መሰረታዊ የጥናት ጥያቄዎችን ለመመለስ የተካሄደ ነው:: የጥናቱ ተተኳሪዎች በከፍኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ በካፋ ዞን በተመረጡ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው:: እነዚህ ተማሪዎችበአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው የስህተት አይነቶች የትኞቹ ናቸው? የስህተት ብዛታቸው ምን ያህል ነው? የስህተት ድግግሞሻቸው ምን ያህል ነው? የሚለው የጥናቱ የመጀመሪያ መሰረታዊ ጥያቄዎች ሲሆኑ ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ ተጠኚ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ለፈጸሟቸው ስህተቶቸ የስህተት ምንጭ (መንስኤ) ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ? የሚል ነው::

#### ሀ. በተማሪዎቹ የተፈፀሙ አበይት የስህተት አይነቶች

ጥናቱ በተጠቀመበት ስሌት መሰረት የስህተት አይነቶች ከብዛት አንፃር በደረጃ ሲመደቡ፣ በቋንቋ አወቃቀር የተከሰቱ ስህተቶች እና በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም የተከሰቱ ስህተቶች ከፍተኛ ቦታ የያዙ ናቸው::በአጠቃላይ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በድርሰቶቹና በመጠየቆቹ አማካይነት ተሰብስበው አስፈላጊው ትንተና ከተካሄደ በኋላ ከዚህ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል::

- በቋንቋ አወቃቀር አቢይ የሰህተት ምድብ ስር የመስተዋድድ አገባብ፣ የአረፍተ ነገር ስሙሙነት፣ የአያያዦች አገባብ፣ የቃላት አወቃቀር ቅደም ተከተል ላይ የተከሰቱ አምስት አይነት ስህተቶች ተመዝገበዋል::

- በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም አቢይ የሰህተት ምድብ ስር የአራት ነጥብ አጠቃቀም፣ የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም፣ የትዕምርተ ጥቀስ አጠቃቀም፣ የትዕምርተ አንክሮአጠቃቀም እና የጥያቄ ምልክት አጠቃቀም የሚሉ አምስት አይነት ስህተቶች ታይተዋል:: ስህተቶቹ የተፈጸሙት ነጥቦችን ከተገቢ ቦታቸው በመግደፍና ሌሎች ስርአት ነጥቦችን በመጠቀም ነው::

➢ እነዚህ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ግን ከተጠኚዎች የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪነት ብቻ የመነጩ ናቸው ማለት አስቸጋሪ ነው:: ሆኖም በሁለተኛ ቋንቋ የተጻፉ ድርሰቶችን የማንበብና የመፃፍ እጥረት በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀማቸው ላይ የተወሰነ ተፅእኖ እንዳሳደረ መገመት ተችሏል::

## ለ. የስህተት ምንጮች

በከፍኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የካፋ ዞን 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችደርሰት ሲጽፉ ለፈጸሚቸው ስህተቶቸ ምንጭ ናቸው ተብለው የታመኑት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅእኖ፣ የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴ ድክመት እና ስነ-ልቦናዊና ማህባራዊ ሁኔታዎች ናቸው::

ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ሁሉንም ተነባቢ ድምፆቸ በትክክል አለማስቀመጥ፣ ሳልስና ሳድስ ሆሄያትን በትክክል አለመጠቀም እና በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፍ ውስጥ ያልተለመዱ አህጽሮኦተ ቃላትን መጠቀም ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ የተነሳ የተፈጸሙ ስህተቶች ለሆኑ እነደሚችሉ ተገምቷል:: ከቋንቋ አወቃቀር ስህተቶቸ መካከልም የመሰተዋድዶች መግደፍ፣ ተገቢ ያልሆኑ መስተዋድዶችን መጠቀም፣በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ተገምቷል:: ተጠኝ ተማሪዎች ከታላሚው ቋንቋ ውስብስብ ባህሪ የተነሳ ስህተት ሊፈፅሙ እንደቻሉም ታውቋል:: ለምሳሌ ያህል በቋንቋ አወቃቀር የስህተት ምደብ ውስጥ የአረፍተ ነገር ተዋቃሪዎች ስሙሙነት ጉድለት፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ቀደም ተከተል ሰህተቶች የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት በሚገባ ባለማወቃቸው ምክንያት የተፈጠሩ ስህተቶች መሆናቸውን ተረጋግጧል::

መገመት ተችሏል:: ይሁን እንጂ እነዚህ ስህተቶች በትክክል በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ የተነሳ የተከሰቱ ናቸው ለማለት አስቸጋሪ ነው:: ምክንያቱም ጥልቅ የሆነ ተጨማሪ ጥናት ይፈለጋለና::

በድርሰቶቹ ውስጥ ለተፈጸሙት ስህተቶች ምንጭ የቋንቋ አጠቃቀምና አወቃቀር ስርአትን አለማወቅ ብቻ ሳይሆን የመማር ማስተማር ሂደትና የማስተማሪያ መሳሪያዎቸ ደክመት እና ተደጋጋሚ የጽህፈት ልምምድ አለማድረግ ተማሪዎቹ ለፈፀሚቸው ልዩ ልዩ ስህተቶች መፈጠር ምንጭ መሆናቸው ተረጋግጧል:: ለምሳሌ ያህል በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ወስጥ ያልተለመዱ (ኢ-መደበኛ) ቃላትንና ሀረጋትን በመጠቀም፣ ያልተለመዱ አህጽሮኦተ ቃላትን በመጠቀም፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ቃላት እንዳለ

በመጠቀም የተፈጸሙ ስህተቶቸ ተማሪዎቹ ጽህፈትን ካለመለማመዳቸው የተነሳ ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚጠቁሙ ናቸው:: የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች እንዲሁ በአብዛኛው ተማሪዎቹ ጽህፈትን በተደጋጋሚ ካለመለማመዳቸውና የስርዓተ ነጥብን አጠቃቀም በሚገባ ካለማወቃቸው የተነሳ የተፈጸሙ ስህተቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ የመረጃዎች ባህርይ ያረጋግጣል:: በጥቅሉ በትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚገኙ የስነ ፅሁፍና የድራማ ክበባት አለመሳተፍ፣ በቂ የጽህፈት ልምምድ አለማድረግ፣ በመማሪያ መፅሐፍት ውስጥ የሚገኙ መልመጃዎች ጽህፈትን ለማለማመድ ያላቸው እገዛ አናሳ መሆን፣ የመማር ማስተማር ሂደቱና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ለስህተት መከሰት ምክንያት መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ናቸው::

ከተማሪዎቹ ድርሰትና የጽሁፍ መጠይቅ ምላሾች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የበለጠ ጠቀሜታ አለው ብለው የሚገምቱ በመሆኑ፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ለመግባባት መፈለጋቸው፣ የአማርኛ ቋንቋ የስራ ቋንቋ ባለመሆኑና በሌሎቹም ምክንያቶች ለመማር ያላቸው ፍላጎት አሉታዊ እንዲሆን ምክንያት ሆነዋል:: ስለሆነም የማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ተጽእኖ ተጠኚ ተማሪዎቹ ለፈጸሟቸው ስህተቶች ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተረጋግጧል::

በቀረበው የስህተት ምንጭ ትንተና እንደተረጋገጠው ወስጠ ቋንቋ ተፅእኖ በተጠኚ ተማሪዎች ለተፈፀሙት ስህተቶች ምክንያት ሊሆን እንደቻለ ነው:: ለዚህም ተማሪዎቹ የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት አንድ ጊዜ ከለመዱ በኋላ በለመዱት መንገድ አስፋፍተው ለመጠቀም ሲሞክሩ ስህተት የፈፀሙ ለመሆናቸው በጥናቱ ትንተና የቀረቡት ያልተለመዱ የምህፃረ ቃላት አጠቃቀሞች ማስረጃዎች ናቸው:: በተጨማሪም የቋንቋውን የአወቃቀር ስርአት አፋልሶ መጠቀም፣ መደበኛ ያልሆኑ ቃላትን መጠቀም የመሳሰሉትን ያካትታል:: ስለሆነም ተማሪዎቹ ድርሰት ሲጽፉ ለፈፀማቸው የተለያዩ ስህተቶች ውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ ምንጭ መሆኑ ተረጋግጧል::

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት የሚያሳየው በካፋ ዞን በተመረጡ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የከፍኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተጠኚ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የሰርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የጽንሰ-ሀሳብ ግንዛቤና ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶቸ መፈጸማቸውን ነው:: ከድርሰቶችና ከጽሁፍ መጠይቅ ምላሾች የተገኙት መረጃዎች የትንተና ውጤትና ከተዛማጅ ጽሁፉ ጋር በማገናዘብ

የተወሰዱ መረጃዎች የሚያመለክቱትም ተማሪዎቹ የፈጸሟቸው የተለያዩ ስህተቶች በውስጠ ቋንቋ፣ በመማር ማስተማር ሂደትና በማስተማሪያ መሳሪያዎች እና በስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ተጽእኖ አማካይነት የተፈጸሙ መሆናቸውን ነው::

## 5.2. የመፍትሄ ሀሳብ

የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ ወደ ፊት ምን እና እንዴት መሰራት እንዳለበት በሚል መነሻ ከዚህ በታች የተመለከቱት የመፍትሄ ሀሳቦች (አስተያየቶች) ቀርበዋል፡፡ተማሪዎቹ አስረኛ ክፍል ለማጠናቀቅ ብሎም ወደ መሰናዶ ት/ቤት ለመግባት የደረሱ ቢሆንም የፊደላት አፃፃፍ ችግር በሰፊው ጎልቶ የታየባቸው መሆኑና ይህ ችግር ደግሞ አሳሳቢ መሆኑን መምህራን ተገንዝበው የቅርብ ክትትል ቢያደርጉ፣ ወቅታዊና ሙያዊ ድጋፍ ቢሰጡ

- በደርሰቶች ውስጥ ከተለቀሙት ስህተቶች መረዳት የሚቻለው ብዙዎቹ ተማሪዎች አንድ አይነት ስህተት የሚፈፅሙ መሆናቸውን ነው:: በመሆኑ መምህራኑ በየጊዜው ከአዳዲስ አሰራሮች(የልምድ ልውውጥ፣አውደ ጥናቶች ወዘተ.) ጋር የሚተዋወቁበት እድል ቢፈጠር፣
- መምህራን ተማሪዎቻቸውን በየጊዜው የተለያዩ ጽሁፎችን እንዲጽፉ በማነሳሳት፣ ሊያስጽፉ የሚችሉ የተለያዩ ርዕሶችን በማቅረብና ተማሪዎች በጻፏቸው ጽሁፎች ውስጥ ያሉትን ስህተቶች ተማሪዎቹ ራሳቸው እንዲያወጡ በማድረግ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ በመስጠት በመማር ማሰተማር ሂደት መንስኤነት ሊከሰቱ የሚችሉ የስህተት አይነቶችን ለመቀነስ ቢሞክሩ፣
- ተማሪዎች የሚከሰቱባቸውን የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም እንዲሁም መለየት ያልተቻሉ ስህተቶቸን ለመቀነስ ይረዳቸው ዘንድ ያለመሰልቸት አዘውትረው የጽህፈት ልምምድ የሚያከናውኑበት እድል ቢፈጠርላቸው፣
- መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን ለታላሚው ቋንቋና ለጽህፈት ክሂል ትምህርት አወንታዊ አመለካከት (ፍላጎት) እንዲያድርባቸው የተለያዩ የማነሳሻ ዘዴዎችን ተግባራዊ ቢያደርጉ፣
- ከታችኞቹ የክፍል ደረጃዎች ጀምሮ ተማሪዎቹ በተደጋጋሚ ጽህፈትን እንዲለማመዱ ቢደረግ፣

- መምህራን ተማሪዎቻቸው በተደጋጋሚ በሚፈጽሟቸው ስህተቶቸ ላይ የሚኖራቸውን ግንዛቤ በይበልጥ ለማሳደግ በስህተት ትንተና ዙሪያ የተሰሩ የተለያዩ የጥናት ስራዎችን በየትምህርት ቤቱ የሚዳረሱበት ሁኔታ ቢመቻች፣
- ተማሪዎች ደጋግመው እንዲጽፉ ቢደረግና ለጽሁፎቻቸውም ተከታታይነት ያላቸው ምጋቤ ምላሾች ቢሰጡ፣

## ዋቢ ጽሁፎች


ህይወት ሎሃ (2009) "በወላይትኛ አፈ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድረሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትንተና" (ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ) ጅማ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)

ምህረት ሳዳም (1998) "በዋቻሞ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሀድይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፡፡ (ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት)፡፡ (ያልታተመ)

ባዬ ይማም(1987) <u>የአማርኛ ሰዋስው፡፡</u> አዲስ አበባ፣የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፡፡

ተስፋዬ ሽዋዬ (1986) <u>አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታን ማዳበር</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ተክሌ አስፋው (1989) "በቡታጅራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በመስቃንኛ ቋንቋ የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና፡፡" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፡፡ (ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት)፡፡ (ያልታተመ)

ትምህርት ሚኒስቴር (1981) "የአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ከ9-12ኛ ክፍል፡፡" አዲስ አበባ፡፡ በአጸደ ህጻናትና መደበኛ ትምህርት ዋና ክፍል በአማርኛ ትምህርት ዋና ቡድን የተዘጋጀ፡፡ (ያልታተመ)

እመቤት በቀለ (2008) "በኦሮምያ ክልል በኢሉባቦር ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኦሮምኛ አፈ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሰዋሰውን ትምህርት ሲማሩ የሚያስተውሉ ተግዳሮቶች ትንተና" (ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ) ጅማ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)

ደብሬ ተሰማ (1990) "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶችና

ምንጮች ትንተና፡፡” የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፡፡ (ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)፡፡ (ያልታተመ)

ያለውእንዳወቅ(2006)የምርምርመሰረታዊመርሆችንአተገባበር፡፡አዲስአበባ፣ንግድማተሚያቤት ፡፡

All Wright, D&k.M. Bailey (1991) Focus on the language class room Research for Language Teachers. Cambridge: Cambridge University press.

Brown. H. Dougals(1994) principle of language learning and teaching (3rd ed, New Jersey: prentice Hall regents.

Byrne, D(1988)Teaching Writing Skills. Hong Kong: Longman Group Ltd.

_________(1997). Teaching Writing Skills. London: Longman Group Ltd.

Corder, S.(1973) Introducing Applied Linguistics. London: Penguin Groups

____________ (1974) “The Significance of Learners Errors.” In J.C.

_________(1981) Error Analysis and Interlanguage. Oxford: Oxford University Press.

Dulay, H .M.Burt,S. Krashen.(1982).Language Two. New York Oxford.Oxford University Press.

Ellis, R.(1989).Understanding Second Language Acquisition. 5thed Oxford: Oxford University Press.

Hammerly, H. (1991) Fluency and Accuracy. Philadelphia: Multi-Lingual Matters Ltd.

Jhonson, k . (1976) “Mistake correction” ELT, 33, 3: 20

Littlewood, W.T. (1986) Foreign and Second Language Acquisition Research And its Implication for the Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Littlewood, W.(1984).Foreign and Second Language Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

Negara, E.A.(1983) "Non-contrastive Errors in African English: Types and Teaching." IRAL. 36, 1:1-7.

Norrish H, J.(1992).Language Learners and Their Errors.London and Basingstoke McMillan Publishers Ltd.

__________(1993).Language Learners and Their Errors. London and Basingstoke McMillan Publishers Ltd. Richards,

Omaggio Hadley, A. (1993) Teaching Language in Context. Boston: Heinle and Heinle.

Raimes, A. (1983) Techniques in Teaching writing. New York: Oxford University press.

Richards, J.C. (1974) Error Analysis: Perspectives on Second Language Analysis. London and New York: Longman Group Uk Ltd.

Tomiana, M. (1980) "Grammatical Errors communication Break down." TESOL Quarterly. 14,1:71-79.

White, R. (1994) The English Teachers Hand book. Hong Kong: Thomas Nelson and sons Ltd.

Widdowson, H. (1979) Teaching Language as Communication. Oxford: Oxford University Press.

_______________ (1990) Aspects of Language Teaching. Oxford: Oxford Universtity

**አባሪ አንድ ሀ**

**ጅማዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍ(አማርኛ) ትምህርት ክፍል**

**በተማሪዎች ለተጻፉ ድርሰቶች የድርሰት አጻጻፍ መመሪያ**

**ክፍል አንድ**

ከዚህ በታች በሚገለፅላችሁ መመሪያ መሰረት አንድ ድርሰት ትጽፋላችሁ:: ይህንን ድርሰት የምትጽፉበት ምክንያትም በድርሰቶቻችሁ ውስጥ የሚከሰቱ ስህተቶችን ለመተንተንና ለመግለጽ በሚደረገው ጥናት ውስጥ በዋና መረጃነት የሚያገለግል በመሆኑ ነው:: ስለሆነም ከቋንቋ አጠቃቀም፣ ከቋንቋ አወቃቀር፣ ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና ከጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ አኳያ ድርሰቶቻችሁ በባለሙያዎች ይታረማሉ:: ይህ እርማት ግን የእናንተን የድርሰት ችሎታና ብቃት የሚመዝን ሳይሆን የመረጃውን አስተማማኝነትና ተአማኒነት ለማረጋገጥ ነው:: ስለዚህ ጽሁፋችሁ አቅም በፈቀደው መጠን ከላይ በተገለጹት ነጥቦች ላይ ትኩረት ሰጥታችሁ እንድትጽፉት አሳስባለሁ::

**ዝርዝር መመሪያ**

1. ድርሰት በሚጻፍበት ወረቀት ላይ ስም አይፃፍም::
2. ድርሰቱ የሚጻፈው በኢልቦለድ ድርሰት ነው::

**አጠቃላይ መመሪያ**

ከዚህ በታች ድርሰት ሊያስጽፉ የሚያስችሉ አምስት ርዕሶች ቀርበዋል:: ከእነዚህ ውስጥም ይቀለኛል፣ ርዕሱ ብዙ ያስጽፈኛል የምትለውን (የምትይውን) አንድ ርዕስ ብቻ በመምረጥ በክፍል ውስጥ ከ100-150 በሚደርሱ ቃላት ድርሰት ጻፍ (ጻፊ):: ይህንንም ለመጻፍ የተፈቀደው ጊዜ 40 ደቂቃ ብቻ ነው::

1. የትምህርት ጥቅም
2. ኤች አይ ቪ ኤድስ
3. የሸሮ ወጥ አሰራር
4. ጓደኛዬ
5. የቆሎ አዘገጃጀት

**አባሪ አንድ ለ**

**ጅማዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍ(አማርኛ) ትምህርት ክፍል**

**በተማሪዎች ለተጻፉ ድርሰቶች የድርሰት አጻጻፍ መመሪያ**

**ክፍል ሁለት**

ከዚህ በታች በሚገለፅላችሁ መመሪያ መሰረት አንድ ድርሰት ትጽፋላችሁ:: ይህንን ድርሰት የምትጽፉበት ምክንያትም በድርሰቶቻችሁ ውስጥ የሚከሰቱ ስህተቶችን ለመተንተንና ለመግለጽ በሚደረገው ጥናት ውስጥ በዋና መረጃነት የሚያገለግል በመሆኑ ነው:: ስለሆነም ከቋንቋ አጠቃቀም፣ ከቋንቋ አወቃቀር፣ ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና ከጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ አኳያ ድርሰቶቻችሁ በባለሙያዎች ይታረማሉ:: ይህ እርማት ግን የእናንተን የድርሰት ችሎታና ብቃት የሚመዝን ሳይሆን የመረጃውን አስተማማኝነትና ተአማኒነት ለማረጋገጥ ነው:: ስለዚህ ጽሁፋችሁ አቅም በፈቀደው መጠን ከላይ በተገለጹት ነጥቦች ላይ ትኩረት ሰጥታችሁ እንድትጽፉት አሳስባለሁ::

**ዝርዝር መመሪያ**

3. ድርሰት በሚጻፍበት ወረቀት ላይ ስም አይፃፍም::
4. ድርሰቱ የሚጻፈው በኢልቦለድ ድርሰት ነው::

**አጠቃላይ መመሪያ**

ከዚህ በታች ድርሰት ሊያስጽፉ የሚያስችሉ አምስት ርዕሶች ቀርበዋል:: ከእነዚህ ውስጥም ይቀለኛል፣ ርዕሱ ብዙ ያስጽፈኛል የምትለውን (የምትይውን) አንድ ርዕስ ብቻ በመምረጥ በክፍል ውስጥ ከ100-150 በሚደርሱ ቃላት ድርሰት ጻፍ (ጻፊ):: ይህንንም ለመጻፍ የተፈቀደው ጊዜ 40 ደቂቃ ብቻ ነው::

| | |
|---|---|
| 1. የወደፊት ምኞቴ | 4.የልጅነት ህይወት |
| 2.የካፉ ባህል | 5.ደን |
| 3. የጎደሬ ጥቅም | |

**አባሪ አንድሐ**

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል**

**በተማሪዎች ለተጻፉ ድርሰቶች የድርሰት እርማት መመሪያ**

የጥናቱ ዓላማ ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ የሚፈጽሟቸውን የስህተት አይነቶች፣ የስህተቶቹን ምንጮች እና ድግግሞሻቸውን መመርመር ነው:: በመሆኑም የአራሚዎች ውሳኔ ለጥናቱ ዋና መሰረት ነው:: በዚህ መሰረት የሚከተሉትን ዝርዝር መመሪያዎች በጥሞና በማንበብ በእርማቱ ወቅት ተግባራዊ ታደርጓቸው ዘንድ አበክሬ በተህትና አሳስባለሁ::

1. እርማት ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች በተፈጸሙ ስህተቶች ላይ የተወሰነ ነው::
2. የእርማቱ ዓላማ ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የተፈጸሙ ስህተቶችን፣ ዓይነታቸውን፣ ድግግሞሻቸውን እና ምንጭቻቸውን ለማወቅ ስለሆነ በእነዚህ ላይ መወሰን ነው::
3. በእያንዳንዱ ስህተት የተለያዩ ቀለሞችንና ቁጥሮችን መጠቀም ትችላላችሁ::
4. እያንዳንዱ ድርሰት የተጻፉበትን የቃላት ብዛት ማስቀመጥ::
5. የእያንዳንዱ ድርሰት የስህተት ብዛት በመቁጠር ማስቀመጥ::
6. በእየ ስህተት ምድቦች ውስጥ የተገኙትን ስህተቶች ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ግርጌ ማስቀመጥ አትዘንጉ::
7. እርማቱ የሚመለከታቸው የስህተት ምድቦች የመከተሉት ናቸው:: እነዚህም:-
    - የቋንቋ አጠቃቀም (የፊደላት አፃፃፍ፣ የቃላት አመራረጥ፣ አላስፈላጊ ድግግሞሽ፣ ግደፈት፣ ጭመራ፣ ኢ-መደበኛ ቃላት)
    - የቋንቋ አወቃቀር (የመስተዋድድ አገባብ፣ የአረፍተ ነገር ስሙሙነት፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ቅደም ተከተል፣ የአጣማሪዎች አገባብ)
    - የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም (የአራት ነጥብ፣ የነጠላ ሰረዝ፣ የትዕምርተ አንክሮ፣ የትዕምርተ ጥቅስ፣ የጥያቄ ምልክት)
    - የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ እና ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶች የሚሉት እርማቱ ይመለከታቸዋል::


## አባሪ አንድ መ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

## በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች ናሙና


ድርሰት
ተራኪ ድርሰት
የታሪኩ ርዕስ

ለማገሬ

ቁጥር 17 ጽፋለዓሬ

እክርዳር (ዓላማ) ድርሰት

የድርሰት ርዕስ ደን

~~ደን ሕይወት ላለው ነገር በሙሉ ጠቃሚነት ያለው ደን-~~

ደን ሕይወት ላለው ነገር በሙሉ (ጠቃሚነቱ) የላቀ ነው-
እንደዚሁም ደግሞ ደን (ከለላ) ንዲት የከፋና የበዛ ጎርፍ
እንዳ (እንጠበቅ) ባይ ደን ምንም የማይደረግበት ከሆነ በእሳ
(ጋበው) ያለ እንስሳት ቶች፤ወንዞች፤ ወዘተ በሙሉ ወደ
ይጠፋሉ። ስለዚህ የደን ጠቃሚ ወተው ለእንስሳት ቶም
ጠቃ ሳይደርስ በሌላ ወገም ደን (ከለላ) (ሆኖ) እየጠፋ
ማለት ይቻላል። ምሳሌ ደን ከለለበው ወገም የ-
ምጠቀው (ወሃዎች) ይደርቃሉ፤ እንጨቱም ለበርካታ
ይለውጣል፤ ንፁህ አየር ማግኘት እንችላለን ስለዚህ
ሰውም በዚህ (አጠቃም) (ለገና) ይቻላል።

~~Husen~~ 69

Section 9thF

የካ የዘመን መለወጫ በአል

በካፋዎች ዘንድ የመስቀል በአል በተለየ ሁኔታ ይከበራል:: ልዩ ከሚያደርጉት ውስጥ ዋንኞቹ :- በመቻቻልና በመከባበር ሃይማኖትንና: ባህልን: ዘርንና: ብሔርን... ወዘተ ሣይለይ በመቻቻልና በመከባበር/ በመፈቃቀር የሚያካሂዱት በአል ነው:: ይሁን እንጂ የመስቀል በአል በካፋዎች ዘንድ በጋሞዎች በተለየ (በሠፊው) ተሠብስበው በካፋዎች ዘንድ የዘመን መለወጫ በዓል በመባል ይታወቃል:: በአንድነት ሃይማኖትን ዘርን: ባህልን ሣይለዩ በአብሮነት ከሁለት እስከ ሶስት ቀናት ይከበራል::

መስቀል በዓለ የመስቀል በአል ለካፋዎች ትልቅ ቦታ አላቸው:: ምክንያቱም በአሉን (የሚያከብሩ) መቅረብ ከ ዘመድ ጋር ሚሄድ የተመለሰ የሚሩጥበት የሆነ ልዩ ጊዜ: ባህል የባህል እቃ: የባህል ዘፈን: የባህል ፋሽን/ልብስ.... ወዘተ በመያዝ በዐሉ ወደ (የሚከበርበት) ስፍራ ይመጣሉ ለዘፈኑም በጋራ ሆነው በመባል ይታወቃል:: ለዘፈኑም የካፋ (ሙዚቃ) የሆነው በጋራ ከዝማ አይጠፋም ወደ ሰማይን በማለት ናቸው::

በካፋ የባሕል ቅዳሜ በዓለም በንፋስ ቀጠለበት:: በርጆ ቀጠመቃል እሬሳ ጋር ቅዳሜ ቀዘጋጃል:: ቅዳሜ በጽንጉ ተዘጋጅቶ ቀጥርጋል:: በካፋም ሽማግሌ ! በርጋ ቀበካል ቅዳሜውን በእቁጥ በመሥርጋጅ ፃው:

## አባሪ 2
## በጅማ ዩኒቨርሲቲ
## ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

### በተማሪዎች ለተጻፉ ድርሰቶች የስህተት ትንተና መመሪያ

በሁለተኛቋንቋ ተማሪዎች የሚፈፀሙ የስህተት አይነቶችንየስህተቶችን ብዛት ድግግሞሽ እና አማካይ ለማወቅ የNoriSh(1992፣103-104) የአተናተን ስልት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

- ስህተቶች በአይነት ተለይተው እንዲቀመጡ ከተደረገ በኋላ በየምድብ አይነታቸው ተቆጥረዋል፡፡ ስህተቶቹም በሚከተለው ቅደም ተከተል ተተንትዋል፡
- በእያንዳንዱ ድርሰት ውስጥ ያሉትን ቃላት በመቁጠርና ሁሉም ድርሰቶች የተፃፉባቸውን ቃላት በመደመር ድርሰቶቹ የተፃፉበትን ቃላት ብዛት ማወቅ፣
- የተገኙትን የቃላት ብዛት ተጠኚ ተማሪዎቹ ለጻፏቸው የድርስቶች ቁጥር ማካፈልና እያንዳንዱ ድርሰት የተጻፈበትን አማካይ የቃላት ብዛት ማወቅ፣
- $\text{አማካይ የቃላት ብዛት} = \dfrac{\text{የሁሉም ድርሰቶች ቃላት (ሐረጋት) ብዛት}}{\text{የድርሰት ብዛት}}$

- $\text{አማካይ ስህተት} = \dfrac{\text{አጠቃላይ የስህተት ቁጥር ( ብዛት)}}{\text{ተማሪዎች የጻፉት አጠቃላይ የድርሰት ብዛት}}$

- $\text{አማካይ የስህተት ድግግሞሽ} = \dfrac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100$

**አባሪ ሐ**

**በጅማ ዩኒቨርስቲ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት**

በቦንጋ ከተማ አስተዳደር 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

**የተከበርክ /ሺ ተማሪ፡-**

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው በቦንጋ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በከፍኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች፣ የስህተት አይነቶች፣ የስህተቶቹን ምንጮች እና ድግግሞሻቸውን ለመመርመር ለተጀመረው ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡

ከዚህ ጥናት የሚገኘው ውጤትም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ጽሕፈትን በሚለማመዱበት ጊዜ እንቅፋት የሚሆኑባቸውን ነገሮች ለማስወገድ እገዛ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድም ትክክለኛ መረጃ ማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ መጠይቁን በጥንቃቄ አንብበህ/ሽ መልስ በመስጠት እንድትተባበር/ሪ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ውድ የትምህርት ጊዜህን/ሽን መስዋዕት በማድረግ ላደረከው/ሽው ትብብር በቅድሚያ እመሰግናለሁ፡፡

**ማሳሳቢያ፡-**

1. በመጠየቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም
2. መጠይቁን ከሌላ ሰው ጋር ወይም ከጓደኛ አይቶ መሙላት የጥናቱን ውጤት ሊያዛባው ስለሚችል አይፈቀድም፡፡

## ክፍል አንድ

### አጠቃላይ መረጃዎች

1. ጾታ ———
2. ዕድሜ ———
3. አፍ ከፈታህበት /ሽበት ሌላ የምትናገረው/ሪው /የምትናገራቸው/ ሪያቸው ቋንቋ/ ቋንቋዎች ካለ/ ካሉ ————————————————————
4. የአማርኛ ቋንቋን መጠቀም የጀምርከ/ሽው ትምህርት ቤት ከመግባትህ/ሽ በፊት ነው ወይስ መደበኛ ትምህርት ቤት ከገባህ/ሽ በኋላ? ————————————

## ክፍል ሁለት

**መመሪያ፡-** ከዚህ በታች ከቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ አማራጮች ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዱን ጥያቄ በጥንቃቄ ካነበብክ/ሽ በኋላ ለጥያቄው መልስ ይሆናል ያልከውን/ሽውን መርጠህ /ሺ ፊደሉን ክብበው/ቢው፡፡

1. ጽህፈትን በምትለማመድበት /ጂበት/ ጊዜ ለሚፈጠሩ ስህተቶች ምንጭ ናቸው ብለህ/ሽ የምትገምተው/ቺው ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው/የትኞቹ/ ነው/ ናቸው?

   ሀ. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት

   ለ. የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት አስቸጋሪነት

   ሐ. የመምህራን የማስተማር ጉድለት

   መ. የመማሪያ መጽሐፍ ጽህፈትን ለማስተማር አመቺ አለመሆን

   ሠ. የመምህራን የአስተራረም ጉድለት

2. አንተ/አንቺ ተደጋጋሚ ስህተቶችን የምትፈጽመው/ሚው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ውሰጥ በየትኛው/ በየትኞቹ ላይ ነው?

   ሀ. በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ

ለ. በጽንሰ ሀሳብ ቅንብር ላይ

ሐ. በዐረፍተ ነገር አመስራረት ላይ

መ. በቃላት አጠቃቀም ላይ

ሠ. በሆሂያት አጻጻፍ ላይ

3. የአማርኛ መምህራችሁ በትምህርት ቤታችሁ በተቋቋሙት የስነ ጽሑፍ የድራማ ክበባት በመሳተፍ የተለያዩ ስነ ጽሑፎችን (ግጥሞችን፣ መጣጥፎችን፣ አጭር ልቦለዶችን) ጽፋችሁ እንድታቀርቡ ያበረታቷችኋል?

ሀ. ዘወትር ያበረታቱናል መ. አልፎ አልፎ ያበረታቱናል

ለ. በመጠኑ ያበረታቱናል ሠ. አበረታተውን አያውቁምሐ.

ሐ.አብዛኛውን ጊዜ አያበረታቱንም

4. ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከመግባትህ/ሽ/ በፊት በተለይ የአማርኛ መምህርህ/ሽ/ ጽህፈትን እንድትለማመድ /ጂ/ ያደርጉት የነበረው ጥረት ምን ይመስላል?

ሀ. ሁልጊዜ ጽህፈትን እንድንለማመድ ጥረት ያደርጉ ነበር

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ጽህፈትን እንድንለማመድ ያበረታቱን ነበር

ሐ. ጽህፈትን እንድንለማመድ የሚያደርጉት ጥረት መጠነኛ ነበር

መ. አልፎ አልፎ የጽህፈት /የድርሰት መልመጃዎችን ይሰጡን ነበር

ሠ. ጽህፈትን እንድንለማመድ አስተምረውንና ጥረት አድርገው አያውቁም

5. የአማረኛ መምህራችሁ የጽሑፍ ክሂላችሁ እንዲዳብር ለማድረግ የሚጠቀሙበት ዘዴ የትኛው ነው?

ሀ. ከተለያዩ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ መጻህፍት ወዘተ ያነበቡላችሁን አስጥራችሁ እንድትጽፉ ማድረግ

ለ. ርዕስ በመስጠት ወይም ርዕስ መርጣችሁ እንድትጽፉ ማድረግ

ሐ. በስርዓተ ነጥቦች እና በቃላት አጠቃቀም ዙሪያ ትምህርት መስጠት

መ. በፀረፍተ ነገር ግንባታ እና በአስተዋጽኦ አነዳደፍ ዙሪያ ትምህርት መስጠት

ሠ. ሁሉንም ዘዴዎች ይጠቀማሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

**መመሪያ፡-** ከዚህ በታች በቀረቡት ዝርዝር መጠይቆች ትይዩ ከአራት እስከ አንድ ቁጥሮች ድረስ በሰንጠረዥ ውስጥ ቀርበዋል፡፡ ከሰንጠረዡ በላይ በተሰጠው መግለጫ መሰረት ለእያንዳንዱ መጠይቅ በምትመርጠው/ጪው ቁጥር ትይዩ በሰንጠረዡ ውስጥ የ "X" ምልክት አስቀምጥ/ጪ፡፡

4= በጣም እስማማለሁ

3= እስማማለሁ

2= እልስማማም

1= ጨርሶ አልስማማም የሚሉት ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | መመዘኛዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | በአማርኛ ቋንቋ ስጽፍም ሆነ ስናገር ለምፈጽማቸው ስህተቶች ከመምህሬ ማስተካከያ (እርማት) ይሰጠኛል፡፡ | | | | |
| 2 | ድርሰት ስፅፍ በጣም አሳጥሮ መፃፍ ያስደስተኛል፡፡ | | | | |
| 3 | ድርሰት ስጽፍ የአፍ መፍቻ ቋንቋየ ጣልቃ እየገባ ያስቸግረኛል፡፡ | | | | |
| 4 | በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ስጽፍ ሁሉንም ተነባቢ ድምጾች በትክክል ለማስቀምጥ ያስቸግረኛል፡፡ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | በጽሑፌ ውስጥ የተለያዩ ስህቶችን የምፈጽምበት ምክንያት የአማርኛ ቋንቋን ሰዋስዋዊ ስርዓት (ህግ) ባለማወቄ ነው፡፡ | | | | |
| 6 | በአማርኛ ቋንቋ ጽሑፌ ውስጥ ሳልስና የሳድስ የተባሉትን ሆሄያት በትክክል እጠቀማለሁ፡፡ | | | | |
| 7 | ለጽህፈት ክሂል መዳበር የሚጠቅሙ የተለያዩ ጽሑፎች በየጊዜው አይቀርቡልኝም፡፡ | | | | |
| 8 | የአማርኛን ቋንቋ መማር አያስደስተኝም፡፡ | | | | |
| 9 | እና፣ ስለሆነም፣ ስለዚህ፣ ነገር ግን፣ ወዘተ. የሚሉትን አያያዥ ቃላት በፅሁፌ ውስጥ በትክክል መጠቀም አልችልም፡፡ | | | | |
| 10 | በአማርኛ ቋንቋ ዐረፍተነገሮችን ስጽፍ በተደጋጋሚ ስህተት የምፈጽምባቸውና ለማረም ያልቻልኳቸው ሰዋስዋዊ ጉድለቶች አሉ፡፡ | | | | |
| 11 | የአማርኛ ቋንቋ አረፍተ ነገሮችን ስፅፍ የከፍኛ ቋንቋ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓትን ወይም ስልትን እጠቀማለሁ፡፡ | | | | |
| 12 | በአማርኛ አረፍተ ነገር ውስጥ የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽን (ግስን) ቦታ ለመለየት አልችልም፡፡ | | | | |
| 13 | በጽሑፍ ጊዜ ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን ለይቶ ለመጠቀም እቸገራለሁ፡፡ | | | | |

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | መመዘኛዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 14 | በአማርኛ ቋንቋ ስፅፍ ትክክል ላልሆን እችላለሁ እያልኩ ሁል ጊዜ እጠራጠራለሁ፡፡ | | | | |
| 15 | ከከፍኛ ቋንቋ ይልቅ የአማርኛን ቋንቋ መማር የበለጠ ይጠቅመኛል፡፡ | | | | |
| 16 | የመማሪያ መፅሐፍት መልመጃዎች ፅህፈትን ለማለማመድ የጎላ አስተዋፅኦ የላቸውም፡፡ | | | | |
| 17 | በጽሑፌ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ስህተቶች ደጋግሜ በማንበብ ራሴ ለማረም እሞክራለሁ፡፡ | | | | |
| 18 | በት/ቤት ውስጥ በሚገኙ የስነ-ጽሁፍና የድራማ ክበቦች እሳተፋለሁ፡፡ | | | | |
| 19 | 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ከመግባቴ በፊት በቂ የጽህፈት ልምምድ ባለማድረጌ በአሁኑ ጊዜ ድርሰት ስጽፍ ያሳድርብኝ ተጽኖ ከፍተኛ ነው፡፡ | | | | |
| 20 | ከሰዎች ጋር ለመግባባት ከአማርኛ ይልቅ የከፍኛ ቋንቋ መጠቀም ይቀናኛል፡፡ | | | | |

## ስለትብብርህ (ሽ) በድጋሚ አመሰግና